ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሑፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በመቱ ከተማ በሚገኙ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የጽህፈት ክሂል ትምህርት አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት

በ

አበበች ባየ

መስከረም፣ 2014

ጅማ፣ ኢትዮጲያ

# በመቱ ከተማ በሚገኙ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የጽህፈት ክሂል ትምህርት አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት

በአማርኛ ቋንቋና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት

የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

በ

አበበች ባየ

አማካሪዎች

ዋና አማካሪ፡- ምህረት ሳዳም (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ፡- አብዱራህማን ፋንታሁን

መስከረም 2014 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

# ጅማ ዩኒቨርስቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

### የኢትየጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ አማርኛ ቋንቋትምህርት ክፍል

### የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

በመቱ ከተማ በሚገኙ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የጽህፈት ክሂል ትምህርት አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

አበበች ባየ

የፈተና ቦርድ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| አማካሪ | ቀን | ፊርማ |
| ____________________ | ____________________ | ____________ |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |
| ____________________ | ____________________ | ____________ |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |
| ____________________ | ____________________ | ____________ |

መስከረም 2014 ዓ.ም
ጅማ ኢትዮጵያ

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በመቱ ከተማ በሚገኙ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የጽህፈት ክሂል ትምህርት አተገባባር ንጽጽራዊ ጥናት በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ በሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ  ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ በአማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንናየተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና ጅማ ዩቨርስቲም የጥናቱ ህጋዊ  የባለቤትነት  መብት  ያለው መሆኑን  በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ----------------------------------

ፊርማ ------------------------------

ቀን -----------------------------------

# ምስጋና

በቅድሚያ ሁሉንም በጊዜዉ ለሚያከናዉን ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይግባዉ፡፡ ጥናቱን ቅርፅ ከማስያዝ ጀምሮ እስከ መጨረሻዉ ድረስ ደጋግመዉ በማስተካከል ለጥናቱ የሚያስፈልገኝን ሙያዊ አስተያየትና ፈጣን ግብረመልስ በመስጠት ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶክተር ምህረት ሳዳም ከልብ የመነጨ ምስጋና ከታላቅ አክብሮት ጋር አቀርባለሁ፡፡በመቀጠልምጥናቱን ለመስራት መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ለጥናቱ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አስተዋጽኦ ላደረጉልኝ፤ በሀሳብም ሆነ በቁሳቁስ ድጋፍ በመስጠት ለተባበሩኝ ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ እንዲሁም ይህንን ጥናት ሳካሄድ ቀንና ሌሊት ከጎኔ ሳይለይ የረዳኝ ዉድ ባለቤቴ መምህር ግርማ ጥበቡን ከልቤ ላመስግን እወዳለሁ፡፡እንዲሁም መረጃ በምስበስብበት ወቅት ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ መምህራኖችና ተማሪዎች ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለዉ፡፡ በመጨረሻም ይህንን የትምህርት ዕድል ላመቻቹልኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛቋንቋና ትምህርት ክፍል መምህራኖች ረጅም ዕድሜና ጤና እንዲሰጥልኝ እየተመኘሁ ከፍያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር በማነጻጸር መፈተሽ ነዉ፡፡አጥኚዋ ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ የተጠቀመችዉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የክፍል ዉስጥ ምልከታ፤የጽሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ሲሆኑ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ከሁለት የግልና ከሁለት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ነዉ፡፡የተመረጡትምትምህርትቤቶች በዕጣ የናሙና ዘዴን በመከተል ሲሆን በመቱ ከተማ በሚገኙ የግልና የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አራቱንበዕ ጣ የ ና ሙና አ ሜሩረ ጥዘዴ በመጠቀም ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ በእነዚህ አራት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራን አራቱን በጠቅላይ የናሙና ዘዴ በመምረጥ የጥናቱ ተተኳሪዎች በማድረግ ጥናቱን ለማካሄድ ተሞክሯል፡፡ በነዚህ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ከሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በደረጃ የወጡ ወይም ከ1-5 የወጡ ከየ ክፍሉ አምስት አምስት ተማሪዎችን በመዉሰድ በአጠቃላይ 60 ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቁን እንድሞሉ ተደርጓል፡፤ ሶስት ሶስት ጊዜ በተደረገዉ የክፍል ምልከታና ከቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆች የተገኘዉ ዉጤት በአይነታዊና በመጠናዊ የትንተና ዘዴ ትንታኔ የተደረገበት ሲሆን በዚህ ጥናት የተደረሰበት ዉጤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂል ትምህርትን እንደ ሌሎች የቋንቋ ትምህርቶች ትኩረት ሰጥተዉ የማያስተምሩ መሆኑ ነዉ፡፡ በመሆኑም የሁለቱን ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ሲናነጻጽር የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ተጠኚ መምህራን የመጻፍ ትምህርት አተገባበር ከመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ተጠኚ መምህራን የመጻፍ ክሂል አተገባበር የተሻለ ነዉ በሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡ምክንያቱም የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የፅህፈት ክሂል ትምህረት አተገባበር በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራንየተሻለ አተገባበር እንዳለ ለማየት ተችሏል፡፡በአጠቃላይ የግልና የመንግስት ትምህርትቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የእርስበርስ የልምድ ልዉዉጥ ቢያካሄዱ የመፃፍ ትምህርቱ ሊከናወን እንደሚችል አስተያየት ተጠቁሟል፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ............ i
አጠቃሎ ............ ii
ማውጫ ............ iii
የሰንጠረዥማውጫ ............ v
ምዕራፍአንድ፤ መግቢያ ............ 1
1.1 የጥናቱዳራ ............ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ 3
1.3 የጥናቱመሪጥያቂዎች ............ 4
1.4 የጥናቱአላማ ............ 4
1.4.1 የጥናቱዝርዝርአላማ ............ 5
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ............ 5
1.6.የጥናቱወሰን ............ 5
1.7.የጥናቱ ውስንነት ------------ 6
ምዕራፍሁለት፤ ክለሳድርሳናት ............ 7
2.1.ንድፈ-ሀሳዊ ቅኝቶች ............ 7
2.1.1.የጽህፈት ክሂል ምንነት ............ 7
2.1.2 የጽህፈትን ክሂል ማስተማር የሚያስገኘው ጥቅም ............ 8
2.1.3 የጽህፈት ትምህርትን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ተለውጦዎች ............ 9
2.1.4.የመጻፍ ክሂልን የማስተማር ትኩረት ............ 10
2.1.5 የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ............ 12
2.1.6 የፅህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረቦች ............ 15
2.1.7 የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደቶች ............ 18
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ............ 20
ምዕራፍሶስት፤የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ............ 23
3.1.የጥናቱንድፍ ............ 23
3.2 የጥናቱአካላይ ............ 23
3.3 የናሙናአመራረጥ ............ 24
3 3.1 የትምህርትቤቶችናሙናአመራረጥ ............ 24

3.3.2. የክፍልደረጃናሙናአመራረጥ ........................................................................ 24
3.3.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........................................................................ 24
3.3.4. የመምህራንናሙናአመራረጥ ........................................................................ 25
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........................................................................ 26
3.4.1. የክፍልውስጥምልከታ ........................................................................ 27
3.4.2. የፅሁፍመጠይቅ ........................................................................ 28
3.4.3. ቃለ-መጠይቅ ........................................................................ 29
3.5 የመረጃመተንተኛዘዴዎች ........................................................................ 29
ምዕራፍአራት፤የመረጃትንተናናየዉጤትማብራሪያ ........................................................................ 30
4.1 የመረጃትንተና ........................................................................ 30
4.1.1 ከተጠኚመምህራንምልከታየተገኙመረጃዎችትንተና ........................................................................ 30
4.1.2 አጠቃላይየመምህራንየመፃፍክሒልአተገባበርደረጃ-------------------------------------31
4.1.3. ከተማሪዎችየጽሑፍመጠይቅየተገኙመረጃዎችትንተና ........................................................................ 41
4.1.4. ከመምህራንቃለመጠይቅየተገኙመረጃዎችትንተና ........................................................................ 64
4.1.5 ለመምህራንየቀረቡቃለመጠይቆችናየተገኙምላሾች ........................................................................ 65
4.2 የዉጤትማብራሪያ ........................................................................ 67
ምዕራፍአምስት፤ማጠቃለያ ፣ መደምደሚያናአስተያየት ........................................................................ 75
5.1 ማጠቃለያ ........................................................................ 75
5.2 መደምደሚያ ---------------------------------------------------------------------------------------77
5.3. አስተያየት ........................................................................ 77
ዋቢጽሑፎች ........................................................................ 79
አባሪዎች ........................................................................ 81

# የሰንጠረዥማውጫ

ሰንጠረዥ ገጽ

ሠንጠረዥ 1 የተጠኚ መምህራን ዳራዊ መግለጫ................................................................. 26

ሰንጠረዥ 2 የመምህራን የመጻፍ ክሂል አተገባበር ደረጃ ---------------------------------------31

ሠንጠረዠ 3፡ የተጠኚ መምህራን የቅደመ መጻፍ ትምህርት አተገባበር በክፍል ምልከታ የተገኘዉ-ዉጤት በቁጥርና በፐርሰንት........................................................................................ 37

ሠንጠረዥ 4፡ የተጠኚ መምህራን የመጻፍ ጊዜ ትምህርት አተገባበር በክፍል ምልከታ የተገኘዉ ዉጤት በቁጥርና በፐርሰንት........................................................................................ 39

ሠንጠረዥ 5፡ የተጠኚ መምህራን የድህረ መጻፍ ትምህርት አተገባበር በክፍል ምልከታ የተገኘዉ ዉጤት በቁጥርና በፐርሰንት........................................................................................ 40

ሠንጠረዥ 6፡ የጽሑፍ መጠይቅ የሞሉ ተማሪዎች ዳራዊ መግለጫ ............................................... 41

ሠንጠረዥ 7፡በቅድመ መፃፍ ጊዜ ከውጤታዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር አኳያ ለተማሪዎች ከቀረቡ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ትንተና........................................................................ 42

ሠንጠረዥ 8፡ በመፃፍ ጊዜ ከሂደታዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር አኳያ ለተማሪዎች ከቀረቡ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................................................................ 45

ሠንጠረዥ 9፡ በድህረ መፃፍ ጊዜ ከሂደታዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር አኳያ ለተማሪዎች ከቀረቡ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ትንተና........................................................................ 50

ሠንጠረዥ 10 ፡የቅድመ መፃፍ ጊዜ የተማሪዎች ግምገማ በፐርሰንት............................................ 52

ሠንጠረዥ 11፡በመጻፍ ጊዜ ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ግምገማ በፐርሰንት .......................... 54

ሠንጠረዥ12፧ የድህረ መጻፍ ጊዜ ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ግምገማ በፐርሰንት ................. 56

ሠንጠረዥ13፡ በቅድመ መፃፍ ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ግምገማ በመቶኛ (በፐርሰንት) ........ 58

ሠንጠረዥ 14፡ በመፃፍ ጊዜ ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ግምገማ በመቶኛ (በፐርሰንት)........... 60

ሠንጠረዠ 15፡ የድህረ መፃፍ ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ግምገማ በመቶኛ (በፐርሰንት) ........ 62

# ምዕራፍአንድ፤ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱዳራ

ቋንቋን ማስተማር ሲባል በዋናነት የቋንቋ ክሂሎችንና ዘርፎችን ማስተማር ሲሆን ከነዚህ ክህሎችም አንዱ የመፃፍ ክሂል ነዉ፡፡ መፃፍ የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ትዕምርቶችን ተጠቅሞ መልዕክትን በወረቀት ላይ ማስፈር ነዉ፡፡ ንግግር ድምፅ ከማመንጨት በላይ እንደሆነ ሁሉ የመፃፍ ክሂል ትዕምርቶችን በመጠቀም ቃላትን፤ዐረፍተ-ነገሮችንና አንቀፆችን ወዘተ በቋንቋዉ ስርዓት መሰረት አቀናብሮ የሚያቀርብ ነዉ፡፡ መፃፍ ሀሳብን፤እምነትን፤ አድስ ግኝትን በፊደል ምልክትነት ለማስተላለፍ የሚያስችል የቋንቋ ወኪል ነዉ፡፡

የመፃፍ ክሂል ለሌሎች ክሂሎች መዳበር ወሳኝ በመሆኑ ሌሎች የቋንቋ ክህሎችን ለማዳበር ያስችላል ፡፡ ተማሪዎች በፅሁፍ ሃሳባቸውን በተሻለ መንገድ ለመግለፅ የሚያስችሏቸውን ቃላትና የአረፍተነገር መዋቅር ለመምረጥ የሚያደርጉት ልምምድ የንግግር ክሂላቸው እንዲዳብር ያደርጋል በድሉ(1996፡52) ፡፡ በተጨማሪም የማንበብና የማዳመጥ ክሂላቸውን ያዳብራል፡፡ የክሂሎች የተቀናጀ እድገት በፋንታው የመማርን ሂደት አስቸጋሪ እንዳይሆን ያደርጋል ፡፡ የፈጠራ ሃይል መስፋትና የችግር መፍታት ልምድን ከመፃፍ ክሂል መዳበር ጋር ተያይዘው ይዳብራሉ በማለት በድሉ(1996፤52)ገልፀዋል፡፡

ሌላዉ የመፃፍን አስፈላጊነትን በተመለከተkiros (2006፤2) Aplebin ጠቅሰው እንደገለፁት አዘውትሮ ለሚፅፍ ተማሪ የሚፅፈውን ነገር እያካለለ ይመረምራል ፤ያደራጃል፡፡ ከቃላት ጋር ስለሚጫወት የተለያዩ ፍቺዎቻቸውን ያውቃል፡፡ ያገላለፅ ስልቱን ያዳብራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፅሁፋቸው በሌላ መነበቡ ስለራሳቸው ያላቸውን ግምት ከፍ ያደርገዋል፡፡ ለሌላው አስፈላጊ እንደሆኑ አድርገው አራሳቸውን ይገምታሉ፡፡ይህም ትልቅ የሆነ አገልግሎት ያለውን ክሂል ደግሞ በትምህርት ሂደት ላይ መምህራን እንዴት ትምህርቱን መስጠት እዳለባቸው በድሉ (1996፤53) የፅህፈት ትምህርት የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት የደረገ መሆን አለበት፡፡ መምህራን ደስ ያላቸውን ርዕስ ለተማሪዎች በመስጠት ጽህፈት የሚያስተምሩበት ሂደት ማብቃት ያሻዋል፡፡ ስለሚያውቁት ነገር እዲፅፉ ማድረግ ፅፈትን እጅግ አስቸጋሪ ተግባር አድረገው እዲያስቡት የደረጋቸዋል፡፡ስለሚፈልጉት ርዕስ ፤በራሳቸው ቃላትና የአገላለፅችሎታ ተጠቅመው እየፃፉ መለማመድ አለባቸው፡፡ መምህራን ፅህፈት በአንድ ቅፅበት የሚከናወን ሳይሆን የተለያዩ ደረጃዎች በውስጡ የያዘ ሂደት መሆኑን በመግለፅ ተማሪዎች እነዚያን

ደረጃዎች ተከትለው የመፃፍ ልምድ እንዲያዳብሩ ሊረዷቸው ይገባል በማለት አስረድተዋል ፡፡ የፅኀፈት ክሂልን መማር ለተማሪዎች ከፍተኛ ችግር ከመሆኑም በላይ ከመካከላቸው የክሂሉ ባለቤት ለመሆን የሚበቁት በጣም ጥቂቶች እንደሆኑ ይነገራል፡፡ በርግጥም ጥሩ ድርሰትን መፃፍ መቻል ከባድ አዝጋሚ፤ሂደት የሚታይበት ብዙ ተማሪዎችን የሚያስጨንቅና ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው በማለት Richards (1990) Davies እናወንደሰን (1974) አብራርተዋል፡፡

የአማርኛ ቋንቋየመፃፍ ክሂልን አስመልክቶ ተማሪዎችም ሆኑ ሙያቸው አስገድደዷቸው የሚፅፉ ጸሃፍት ፅሁፎች ደካማ እንደሆኑ ብዙ ጥናቶች አመልክተዋል ፡፡ ከነዚህም ጥናቶች ውስጥ ሰይድ (1993)፤ጌታቸው (2001)፤ ኢሳያስ(2002)፤ሰለሞን (1991)እና ስዩም(1988)ተጠቃሽ ናቸው፡፡ አጥኚዎቹ በጥናታቸው እንዳሰፈሩት በግልም ሆነ በመንግስት ፤በአንደኛ ደረጃም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች የፅህፈት ችሎታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡የዚህ ችግር ምክንያት የቋንቋትምህርት በሃገራችን የትምህርት መርሃ ግብር ወይም ስርአተ ትምህርት ካለመካተቱ አይደለም፡፡ ችግሩ ቋንቋው በትምህርትነት ቢቀርብም የክሂሉ አሰጣጥ የተዳከመ እና በተለይም ከአንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ድረስ ትኩረት የተነፈገው እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡

የመፃፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት የተለያዩ አቀራረቦች አሉ፡፡ይሁን እንጂ አንድ ወጥ የሆነና ትክክለኛ ወይም ጥሩ የሚባል የማስተማር ዘዴ የለም፡፡ጥህ የሆነበት ምክንያት የትምህርቱ ይዘት እንደ መምህሩ የማስተማር ሁኔታ፤ የተማሪ ብዛት፤ የመማር ስልት፤ ችሎታና ዳራ ወዘተ አንፃር የሚወሰን ነዉ፡፡ በመሆኑም የአንድ ፅሁፍ አላማ ተገቢ የሆነዉን የአቀራረብ ዘዴ መርጦ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ "ሰለሞን (1991) የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጂናየመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ"በሚል በአዋሳ መምህራን ትምህርት ኮልጅ በአንድ መምህር ላይ ጥናት አካሂደዋል፡፡የጥናቱ ግኝትም መምህሩ የሚከተላቸዉ የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች በአብዛኛዉ ተማሪዎች በተፈጥሮ ያላቸዉን የመፃፍ ስትራቴጂ የሚያሳድጉ እንደሆኑ ነዉ፡፡ (ኡር 1996 እና ራይምስ 1983)በክፍል ዉስጥ የሚከነወን የመፃፍክሂል ትምህርት ከግብ የሚደርሰዉ መምህራን በመማሪያ መፀሀፍ ለይ የሰፈረዉን ይዘት ተገቢ የማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም ማቅረብ ሲችሉ እንደሆነ ምሁራኑ ያስረዳሉ፡፡

የመፃፍ ክሂል ትምህርትን ለማስተማር ከምንጠቀምባቸዉ የአቀራረብ መንገዶች መካከል ዉጤታዊ፤ሂደታዊ እና ዘዉግ ተኮር የሚባሉት ይግኙበታል፡፡የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር

የሚዘጋጅ መፀሀፍ ደግሞ እዉነተኛ፣ግለፅ፣ማራኪ፣አበረታች ፣ተጣጣሚ፣ጥልቅ፣ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡በዚህ ጥናትም የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር በመቱ ከተማ በሚገኙ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍል በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተተኳሪነት ይህ ጥናት ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የመፃፍ ክሂል ትምህርት ከታች ጀምሮ እየዳበረ የሚሄድክሂል ነው፡፡ አንድ የተሟላ ሀሳብ የያዘ ፅሁፍ ለመፃፍም ሆነ የሠላምታ ወይም ትምህርታዊ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ምን ጊዜም ቢሆን የሚጀምረው ከንግግርድምጾች ነው፡፡ እነዚህ ትምህርቶች ውስጣዊ ስርዓታቸውን ጠብቀው በመቀናጀት ቃላትን፣ቃላት እንደዚሁ ተቀነባብረው ሀረጋትን ሀረጋት ደግሞ ዐረፍተ-ነገሮችን ያስገኛሉ፡፡ አንቀጾችም ተቀናጅተው ምንባቦችን ልቦለድና ኢ-ልቦለዶችን የመመስረት ሂደትም አላቸው፡፡

በመሆኑምበክፍል ውስጥ የሚከናወን የመፃፍ ክሂል ትምህርት ከግብ የሚደርሰው መምህራን በመማሪያ መፃሀፉ ላይ የሰፈረውን ይዘት ተገቢ የማስተማሪያ ዘዴ በመጠቀም ማቅረብ ሲችሉ እንደሆነ Bayner (1988) ይገልፃሉ፡፡

የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶችን በማነፃፀር በሌሎች አጥኚዎች ከተሰሩ ጥናቶች መካከል አለማሁ (1998) “በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሁለት የመንግስትና ሁለት የግል ትምህርት ቤት ዉስጥ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የፅሀፈት ክሂል ችሎታ ንፅፅራዊ ጥናት” በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዉጤትም የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻለ የፅሀፈት ክሂል ችሎታ እንዳላቸዉ በመግለፅ ፣መምህራንም ቢሆን ከመንግስት ትምህርት ቤቶች በተሻለ መልኩ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ለክሂሉ ትኩረት እንደሚስጡት ገልፀዋል፡፡ ግርማይ (2009)”በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ አራት የግልና የመንግስት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሰዋሰዉ ትምህርት አቀራረብ ንፅፅራዊ ትንተና” በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዉጤትም በሰዋሰዉ ትምህርት አቀራረብ ዙሪያ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ከመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን የተሻሉ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡ ከላይ የቀረቡት ሁለቱም ጥናቶች የሚያመላክቱት የፅሀፈትክሂልና ሰዋሰዉ ትምህርት አቀራረብ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን የሚሰጧቸዉ ትኩረት ከግል

ትምህርት ቤቶች ያነሰ መሆኑን አመላክተዋል፤ማለትም በፅህፈት ክሂልም ሆነ በሰዋሰዉ ትምህርት አቀራረብ የግል ትምህርት ቤቶች የተሻሉ እንደሆኑ በጥናቶቹ ተገልፀዋል፡፡

በመሆኑም አጥኚዋ ይህንን ጥናት እንድታካሄድ ያነሳሳት ምክንያት በኢሉባቦር ዞን በመቱ ወረዳና አከባቢዋ የሚገኙ ተማሪዎች ትምህርታቸዉን ከጨረሱ በኃላ እንኳን ቢሆን በአማርኛ ቋንቋ ሀሳባቸዉን በጽሑፍ ለመግለጽ በጣም ይቸገራሉ፡፡ አጥኚዋም በሞያዊ ገጠመኟ በአካባቢዉ በመምህርነት በሰራችባቸዉ ተከታታይ ዓመታት ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ሀሳባቸዉን ለመግለጽ ያላቸዉ ችሎታ በጣም ዝቅተኛና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰና እየጠፋ መምጣቱን አስተዉላለች፡፡ ስለዚህ ይህ ነገር ለምን ሆነ ከመምህራኑ የክፍል ዉስጥ የሚከናወን የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር የተነሳ ይሆን የሚል ጥያቄ ስላጫረባት ይህንን ጥናት ለማካሄድ ተነሳስታለች፡፡ በተጨማሪም ይህ የመፃፍ ትምህርት ችግር በመንግስት ትምህርት ቤቶች ብቻ ነዉ ችግሩ የሚታየው? ወይስ በግል ትህርት ቤቶችም የሚታይ ነዉ? የሚለዉን ለመመለስ ነዉ፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

የጥናቱን አላማ መነሻ በማድረግ ጥናቱከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሞክሯል፡፡

1. የግል እና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል መምህራን በመፃፍ ክሂልየመማር ማስተማር ሂደት ያላቸው የክፍል ዉስጥ የትምህርት አተገባበር ምን ይመስላል?
2. የግል እና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል መምህራን የመጻፍ ክሂል ትምህርትን የሚያቀርቡባቸው ዘዴዎች ወይም ስልቶች ምን ምን ናቸው?

## 1.4 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማየግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል መምህራንየፅህፈት ክሂል ትምህርትአተገባበር በንፅፅር መፈተሽ ሲሆን የትኞቹ የተሻለ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር እንዳላቸው በመፈተሽ በሂደቱ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉየመፍተኤ ሀሳቦችን መጠቆም ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ በመነሳት የሚከተሉትን ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፡፡

### 1.4.1 የጥናቱ ዝርዝር አላማ

1. የመንግስት እና የግል ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ዉስጥ የፅህፈት ክሂልትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ፤

2. የመንግስት እና የግል ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል ትምህርትን የሚያቀርብባቸው ስልቶች / ዘዴዎች ምን ምን እንደሆኑ መመርመር።

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በርካታ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ይታመናል ።

- የመፃፍ ክሂልን ለሚያስተምሩ መምህራን አሰፈላጊ የሆነ ጥቆማ ሊሰጥ ይችላል።
- የመፃፍ ክሂልን ትምህርት ለሚያዘጋጁ የትምህርት ባለሞያዎች የተለያዩ አካላት እና የመንግስትተቋማት የበኩሉን ድርሻ ሊያበረክት ይችላል።
- በዚህ ርዕስ ዙሪያ ወደፊት ሰፊ ጥናት ለሚካሄዱ አጥኚዎች እንደመነሻ ሀሳብ በመሆን ሊያገለግል ይችላል።

## 1.6.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በኢሉባቦር ዞን  በመቱ ወረዳ በመቱ ከተማዉስጥ በሚገኙ የግል እና የመንግስት ትምህርት ቤቶች አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍል በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ትኩረቱን አድርጓል።ጥናቱም  በግል እና በመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል መምህራን የትኞቹ የተሻለ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር እንደሚተገብሩ በንጽጽር መፈተሽ እንጂ ስለ መፃፍ ክሂል ትምህርት ሌሎች ይዘቶች የሚመዝን እና የሚገመግም አይደለም።ስለሆነም ጥናቱ በመቱ ከተማ በሚገኙ በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ  የ2013 የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን  ላይ ያተኮረ ንጽጽራዊ ጥናት ነዉ።

## 1.7 የጥናቱ ዉስንነት

ይህ ጥናት በመቱ ከተማ በሚገኙ ሁለት የግልና ሁለት የመንግስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ተወስኖ የቀረበ ነዉ።ይሁን እንጂ በከተማዉ የሚገኙ ሌሎች ትምህርት ቤቶችን አለማካተቱ ፤በተወሰኑ ናሙናዎች ላይ የተከናወነ በመሆኑና በአጭር ጊዜ መከናወኑ ጥናቱ ዉስንነት ይታይበታል።

# ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት

## 2.1.ንድፈ-ሀሳባዊ ቅኝቶች

### 2.1.1.የጽህፈት ክሂል ምንነት

ጽህፈት ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከልአንዱ ነው። ይህ ክሂል በትምህርት አማካኝነት የሚቀሰምና ደረጃውን ጠብቆ ከሚፈፀም ተከታታይ ልምምድ የሚገኝ ችሎታ ነው። “ጽህፈትአካልንና አእምሮን በማቀናጀት በርካታ ባህሪያቱን በአንድ ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ውስብስብ የአእምሮ ስራ ነው” በማለት Nunan (1989, 36) ያብራራሉ።

ጽህፈት በትዕምርቶች አማካኝነት ሀሳብን በወረቀት ላይ ማስፈር መሆኑን የተለያዩ ምሁራን በጥናታቸው አብራርተዋል። ከነዚህም መካከል Byrne (1991, 1) "ጽህፈት የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ትዕምርቶችን ተጠቅመን ሀሳብን በወረቀት ላይ የምናሰፍርበት ሂደት ነው"ብለዋል። ይህን ሀሳብ በማጠናከር Harmer (1991) እና Zamel (1985) ንግግር ድምፅ ከማመንጨት በላይ እንደሆነሁሉ ጽህፈትም ትዕምርቶችን አቀናብሮ የሚያቀርብ ነው በማለት በጥናታቸው አብራርተዋል። ከላይ ምሁራኑ ለማብራራት የፈለጉት የአንድ ቋንቋ ድምፆች ከሚወክሏቸው ምልክቶች ጋር እየተዛመዱ በወረቀት ላይ በማስፈር መልዕክት የሚተላለፍበት ክሂል መሆኑን ነው።ጽህፈትአንዱ የመግባቢያ መሳሪያ እንደመሆኑ መጠን መልዕክት ተቀባዩና መልዕክት ላኪው በወረቀትና በብዕር አማካኝነት መልዕክት ይለዋወጣሉ።እንዲሁም በድምጽ ምልክቶች አማካኝነት ሀሳብን በወረቀት ላይ በማስፈርከሌላአካል ጋር ለመግባባትያስችላል። በተጨማሪም ከንግግር ጋር የቀረበ ግንኙነት አለው።

በአጠቃላይ የጽህፈትክሂልአካልና አዕምሮን በማስተባበር ድምፆችን በምልክቶች በመወከል ሀሳብን ለአንባቢ የምናቀርብበት ክሂል ነው። በጽሐፍ የሚቀርበው ሀሳብ ሊያግባባ የሚችለውየቋንቋውን ስርዓትየጠበቀ ከሆነ ብቻ ነዉ፡በዚህመንገድሀሳብን ማስተላለፍእንዲቻልስሬ ልምድማድረግ ያስፈልጋል።ጽሁፍ ከተግባር ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በተደጋጋሚበሚደረጉ ሙከራዎች ያድጋል፣ ይዳብራል፣ ይበለጽጋል፣ እንዱሁም ጥሩ ፀሐፍት እንዲፈጠሩ ያደርጋል።

### 2.1.2 የጽህፈትን ክሂል ማስተማር የሚያስገኘው ጥቅም

የጽህፈት ትምህርት ከንባብ ትምህርት ጋር በጣም የተቆራኘ ግንኙነት አለው፡፡ ከነዚህ ሁለትክሂሎች ቀዳሚ ተግባር ፊደል ከማስለየትይጀምራል፡፡ የምናነበው በፊደል የተገነባ ነገር ነው፡፡ የምንጽፈውበፊደል አማካኝነት ነው፡፡ ስለዚህ የጽህፈት ትምህርት የሚያስገኘው ጥቅም በቋንቋው ውስጥ ያሉድምፆች የሚወክሏቸውን ምልክቶች ማስለየት ነው፡፡ ምንም እንኳንፊደልን የማስለየት ተግባር የመጀመሪያው የጽህፈት ትምህርት አላማ ቢሆንም እንደ ተማሪዎቹ እድሜ፣ የትምህርት ደረጃናፍላጎት መሠረት በተለያዩደረጃዎች የጽህፈት ትምህርት አላማ ሊለያይይችላል፡፡

የጽህፈት ትምህርት አላማዎች ትግበራ በተማሪዎች እድሜ፣ የትምህርት ደረጃ እናፍላጎት፣ባላቸው ችሎታና ልምድላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ እነዚህ ነገሮች ግምት ውስጥ ካልገቡ ወደ ግብ ለመድረስመሰናክልሊሆኑ እንደሚችሉ Pincas (1982) ያስረዳሉ፡፡ በየክፍልደረጃው የሚሰጠው የጽህፈት ትምህርት ዓላማና የሚያስገኘው ጥቅም የተለያየ ነው፡፡ በዝቅተኛ ደረጃያሉ ተማሪዎች የፊደላትን ቅርጽ በመለየትቃላትን መመስረት፣ የቃላትን ምርጫና አጠቃቀም በማወቅ ሀሳባቸውን በተገቢ ቃላትና አረፍተ-ነገሮች መግለጽየሚችሉበትን የተግባቦት ስርዓት እንዲያውቁ የጽህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ የጽህፈት ትምህርት ከዚህም ሌላ ከፍተኛ ደረጃላይ ላሉ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግና ስርዓት ጠብቀው ሀሳባቸውን በተገቢው መንገድእንዲገልጹ ያስችላል፡፡ እንዲሁም ለማስተላለፍ የፈለጉትንምመልዕክት እነሱ እንዳሰቡትና እንደተረዱትበትክክል የሚያቀርቡለትንአካል ተገቢ ቃላት፣ አረፍተ-ነገሮችና የተዋጣለት አንቀጽ በመጠቀም /በማዋቀር/ በተገቢው መንገድለመግለጽ የጽህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ በመሆኑም Heaton (1990) የጽህፈት ትምህርትን በመማር የሚከተሉትን ችሎታዎች ማዳበር እንደሚቻል ዘርዝረዋል፡፡

1. **የሰዋስው ክሂሎች፡-** የቋንቋውን ህግና ስርዓት የጠበቁ አረፍተ-ነገሮችን መስርቶ ለአንባቢ.ግልጽና ትክክለኛመልዕክት ለማስተላለፍየሚያስችል ብቃት እንድኖር የጽህፈት ትምህርት ትልቅ ፊይዳ አለው፡፡

2. **የስልታዊነት ክሂሎች**፡- ስልታዊነት ማለትአንድፀሐፊ የሚከተለውን የአፃፃፍ ዘዴ የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የተሰማውን ውስጣዊ ስሜት ለመግለፅየሚያስችሉቃላትን አመንጭቶ የመፃፍ ችሎታ እንዲኖረው የጽህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

3.**የአፃፃፍ ስርዓት ክሂሎች፡-** የቋንቋውን የአፃፃፍ ስርዓት በመጠቀም በተገቢው ሁኔታ የመጠቀም ችሎታ እንዲኖር የጽህፈት ትምህርት ያግዛል፡፡

4. **የአጠቃቀምክሂሎች፡-** ተገቢውን ቃላት በተገቢው ቦታ መምረጥ ለሚቀረብለትአካል የማቅረብ ችሎታና ሀሳብን በትክክል በማቀናጀት የመፃፍ ብቃት እንዲኖር የጽህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ ይህም ማለትየቃላት አጠቃቀማችን የተደራሲያንንእድሜ፣ ፍላጎት፣ ባህል፣ የኑሮ ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃናየመሳሰሉትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡የጽህፈት ትምህርት የተለያዩ የመማር ስልቶችንና ፍላጎቶችንለማስገኘት እንደሚረዳ፤ የተለያዩክሂሎች በማቀናጀት መማርእንደሚያስችልና በመደበኛና መደበኛያልሆኑ ፈተናዎችንለማቅረብ እንደሚያገለግልተብራርቷል፡፡ እንዲሁም የጽህፈት ትምህርት በአንዱቋንቋ ውስጥ ያሉድምፆችን የሚወክሉ የተለያዩምልክቶችን ከማሳየት አንስቶ ሀሳብን ተጠየቃዊና ቅደምተከተላዊ በሆነ መንገድለማስተላለፍየሚያስችል ብቃትን ያጎናጽፋል፡፡በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት የጽህፈት ትምህርት የማስተማር ጥቅሞችን መሠረት በማድረግ ተጠኚ ተማሪዎች እምን ደረጃላይ እንደሚገኙለመመርመርለጥናቱትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ በመሆኑም ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያላቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

### 2.1.3 የጽህፈትትምህርትንአስቸጋሪየሚያደርጉተለውጦዎች

የጽህፈትክሂል ዓላማዉ ተማሪዎች በጽህፈት ተግባቦት መገልገል እንዲችሉ የሚያስፈልጋቸውንክሂሎች ሁሉአዳብረው ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለፅችሎታ እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ ይህን ችሎታ ለማስገኘት በሚደረግ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ በርካታ መሰናክሎች ይኖራሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት በዋናነት ሊጠቀሱ እንደሚችሉ Nunan (1989), Hedge (1988), Norrish (1990) እና Richards (1990) ገልጸዋል፡፡

#### 2.1.3.1 የጽህፈት ባህርይ ውስብስብ መሆን

የጽህፈትክሂልበቀላሉ የሚጨበጥ ክሂል አይደለም፡፡ክሂሉ ውስብስብና ረቂቅ የሆነ ክሂል ነው፡፡ በተለይደግሞ አስቸጋሪነቱን የሚያጎላው እንደማዳመጥና መናገር በልምድ ሳይሆን በትምህርት ብቻ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ የጽህፈት ስራ ሀሳብን ከማደራጀት ጋር በጣም የተቆራኘ ነው፡፡ አዕምሯዊ እና አካላዊ ስራ የሚጠይቅ ነው፡፡ ሀሳብን በጽሐፍ ለማስፈር ጊዜ ይወስዳል፡፡ እነዚህ ሁሉ ባህሪያቱ ውስብስብነቱንና አስቸጋሪነቱን ያሳያሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ወስዶ ተጽፎም በመጨረሻ ውጤቱ የታሰበውን ያህል የተፈለገውንመልዕክት ላያስተላልፍናላያረካ ይችላል፡፡

የጽህፈትክሂልምልክቶችን በወረቀት ላይ ከማስፈር ያለፈ ነገር ነው። አንድ የተዋጣለትጽሑፍ አጠናቅሮ ለማቅረብ ብዙ ነገሮችን ማወቅ ይጠይቃል። ከነዚህ ችሎታዎች መካከልየሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

1. ሀሳብና መረጃዎችን አቀናጅቶና አጠናቅሮ ማቅረብ፣
2. ከአሻሚነት ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ማቅረብ፣
3. ለአጽንኦትሲባል ውስብስብ ያሉ ሰዋስዋዊ ሰርዓቶችን አለመጠቀም፣
4. ጥንቃቄ የተሞላበት የቃላት ምርጫና አጠቃቀምን መከተል፣
5. ተገቢውን የሰዋስው አጠቃቀም መከተልና የአረፍተነገር መጠን መወሰንን ማወቅ።

ከላይ የቀረቡት የጽህፈትን ውስብስብነት የሚያሳዩ ነጥቦችና ጽህፈትን አጠናቅሮ ለማቅረብየሚረዱ ነጥቦች ተጠኝ ተማሪዎች በፃፉት ድርሰት ከተነሱት አምስት ነጥቦች የትኛው ላይ የተሻለ ትኩረት እንዳላቸው ለማወቅ ያስችላል።

### 2.1.3.2 ስነ ልቦናዊ፣ስነ ልሳናዊ እና አዕምሯዊ ባህሪያት

በጽህፈት ትምህርት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩት ተላውጦዎች መካከልስነ-ልቦናዊ፣ ስነ-ልሳናዊና ስነ-አዕምሯዊ ሁኔታዎች እንደሆኑ Byrne (1991), Richards (1990) እና Norrish (1990) ያስረዳሉ። በመሆኑም ቀጥለን የተወሰኑትን በዝርዝር እንመልከት።

ሀ. **ስነልቦናዊ ባህሪ፦** ጽህፈት የማፍለቅ ተግባር የሚከናወንበት ክሂል እንደመሆኑ መጠን አንባቢን እያሰቡ መፃፍ የማይቀር ነው። ፀሐፊውም መልዕክቱን ለአንባቢግልጽና ሳቢ በሆነ መንገድለማድረስሲልከወዲሁ በሀሳብና በጭንቀት የሚሞላበት ሁኔታ ይኖራል። ይህም የጽህፈትክሂልን አስቸጋሪ ያደርገዋል። በንግግር ጊዜ ግን ተናጋሪው ወዲያውኑ ከአድማጩ ግብረ-መልስ ስለሚያገኝመልዕክቱን ማስተካከልይችላል። በጽህፈት ጊዜ ግን የአንባቢው ግብረመልስ የዘገየ ነው በማለት Byrne (1991) ያብራራሉ።

**ለ. ስነልሳናዊ ባህሪ፦** በጽህፈት አማካኝነት ሀሳብን በሚገባ ለማስተላፍም ሆነ በታላሚው ቋንቋ አማካኝነት ተጽፎ ወይም ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን መልዕክት ለመረዳት የቋንቋውን ውስጣዊ ባህሪ ማወቅ ወሳኝ ነው። በንግግር ሂደት ውስጥ ጠቃሚነት የሌላቸውንና የምንተዋቸዉን ሁሉ ደግመን በማለት ወይም እንደገና አስተካክለንለመናገርእድልስላለንልናስተካክለውእንችላለን። ይህ ሁኔታ በጽህፈት ጊዜ የተለየ ነው። ምክንያቱም ስንጽፍ በጣም ተጠንቅቀን፣ አስበንና ጊዜ

ወስደንእያንዳንዷን ቅንጣት አስተካክለን ማቅረብ ይኖርብናል በማለት Byrne (1991) እና Norrish (1990) ያስረዳሉ።

**ሐ. ስነአዕምሯዊ ባህሪ፦** ጽህፈትበልምድ ሳይሆን በትምህርት ሂደት የሚገኝና የአዕምሮን ዉስጣዊ ረቂቅ ተግባር የሚጠይቅ ዉስብሱብ ክሂል ነዉ። እንዱሁም እንደየደረጃችንፈተናንለማለፍ አልያም ለክሂልነት ብቻ የምንማረው ጥበብ አይደለም።ይልቁንም ትምህርቱ ሌሎችክሂሎችን ለመማርና ተጨማሪ እውቀቶች ለመቅሰሚያነት ያገለግላል።የጽህፈትክሂል እጅን፣ ዓይንና አዕምሮን በማጣመር ተግባቦትን ለማፋጠንና ገጠመኞችን ለማካፈል የሚያገለግል ስለሆነ ውስብስብ የሆነ አዕምሮዊ ባህሪ አለው።ክሂሉንም ለማዳበርሰፊ ጊዜና በቂ ልምምድ የሚጠይቅ ጊዜ ወሳጅ ክሂል ነው። ስለዚህ አዕምሮን በማሰራት ሀሳብን በጽሐፍ መግለጽ አለመቻልየፅህፈት ትምህርት አስቸጋሪነት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች አንዱ ነው።

በአጠቃላይ የጽህፈት ትምህርት ክሂልን ለማዳበርሰፊ ጊዜና በቂ ልምምድማድረግን የሚጠይቅ ሲሆን ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የተለያዩጉዳዮች (ተላውጦዎች) ጎልተው ይታያሉ። በመሆኑም መምህራን ለተማሪዎቻቸውክሂሉን ለማስጨበጥሲያቅዱ ትኩረት በማደረግ የተማሪዎቹን የስነልሳን ሁኔታ በቋንቋው ያላቸውን የዕውቀት ደረጃና የአዕምሮ ብስለታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለክሂሉመዳበር ያለሰለሰ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም "ጽህፈት ሀሳብን ከአዕምሮ አመንጭቶ በወረቀት ላይ አስተካክሎ ማስፈርከባድና አዕምሮን ሊፈትንይችላል" በማለት Byrne (1991, 4) ያስረዳሉ።

### 2.1.4.የመጻፍ ክሂልን የማስተማር ትኩረት

Ur (1996፣163) በመርህ ደረጃ የመጻፍ ክሂል ጠቀሜታ ሃሳብን ወይም መልዕክትን ለማስተላለፍ ጽሕፈት በጣም አስፈላጊ ነው። በሌላ በኩል አንድ ጸሐፊ በእጅ ጽሕፈት ትክክለኛ ፊደል፣ ስርዓተ-ነጥብ እንዲሁም ተቀባይነት ላለው ሰዋሰውና ጥንቃቄ ለተሞላበት የቃላት መረጣ ትኩረት መስጠት አለበት። ምክንያቱም ከንግግር የበለጠ በጽሕፈት ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የመደበኛ ቋንቋ አጠቃቀም ይስተዋላልና በማለት ገልጸዋል።

የጽሕፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች byren (1991) አንድን ክሂል ማወቅ የሚቻለው ክሂሉን በተከታታይ በተግባር ለማሻሻል ጥረት ማድረግ ተገቢ መሆኑን ይገልጻሉ። ይህም ሁኔታ የሚያስገነዝበን ማንኛውም ክሂል ለማስተማር ተማሪዎች ተግባራዊ ክንውን እንዲተገብሩ

በማድረግ ወይም በማለማመድ ችሎታቸውን ወይም ብቃታቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም የጽሕፈት ክሂልን የማስተማሪያ ዘዴዎች ተማሪዎች የተለያዩ ጽሑፎችን እየጻፉ እንዲለማመዱ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ Raimas, (1991) የጽሕፈትን ክሂል በምናስተምርበት ጊዜ የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ማተኮር እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡

### 1. ትክክለኛነት ላይ ማተኮር

በዚህ ዘዴ ማተኮር በጽሑፍ ስራዎች ላይ ስህተቶች በብዛት ይገኛሉ፡፡ ምክንያቱም በከፍተኛ ደረጃ እርማት ላይ ትኩረት ስለሚሰጥ ነው፡፡ በዚህ ስልት ተማሪዎች የሚፈልጉትን ሁሉ እንዲጽፉ የሚፈቀድላቸው ከሆነ ስህተት ይሰራሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ ይህ የማስተማሪያ ዘዴ የቁጥጥርን አስፈላጊነት ያሰምርበታል፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ የዐረፍተነገር ዓይነቶችና መልመጃዎችን እንዲጽፉና እንዲያቀናጁ ይማራሉ፤ ጥሩ ምክርም ይሰጣቸዋል፡፡ በመጨረሻ የቁጥጥሩ መጠን እየቀነሰ በመሄድ ተማሪዎች ስህተት የሌለበት ዐረፍተነገር ይጽፋሉ፡፡

### 2. ቀናነት ላይ ማተኮር

በተቃራኒ ይህ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ስህተት እንሰራለን ብለው ሳይጨነቁ በፍጥነት እስከቻሉ ድረስ እንዲጽፉ የሚደረግበት ነው፡፡ አስፈላጊው ነገር ሀሳባቸውን በወረቀት ላይ ማስፈራቸው ነው፡፡ በዚህ መንገድ ተማሪዎች እየጻፉ መሆናቸውን ራሳቸው ይረዳሉ፡፡ መጻፍ የፈለጉትን ነገርም ይጽፋሉ፡፡ በመጨረሻ ጽህፈት አስደሳች የህይወት ተሞክሮ ይሆናል፡፡

### 3. በውህድ አሃድ ላይ ማተኮር

ተማሪዎች አረፍተ-ነገር ዘለል ጽሑፎችን በብቃት እንዲጽፉ የሚያደርግ ነው፡፡ ለዚህም የተዘበራረቁ አረፍተ-ነገሮችን አስተካክለው አንቀጽ እንዲመሠርቱ ከኃይለ-ቃል በመነሳት አንቀጽ እንዲጽፉ የሚያደርግ ስልትን ይጠቀማሉ፡፡

### 4. በዓላማ ላይ ማተኮር

ተማሪዎች በተወሰነ ዓላማ ላይ ተመርኩዘው እንዲጽፉ የሚያደርጉ አጋጣሚዎችን የማመቻቸት ዘዴን የሚያመለክት ነው፡፡ ተማሪዎች በየትኛውም ዘዴ ላይ ትኩረት አድርገው ሲጽፉ ሂደታዊ

ስልትን እንዲጠቀሙ በማለት አብራርተዋል፡፡ ስልቱም የሚከተሉትን የአጻጻፍ ቅደም ተከተላዊ ሂደቶች የያዘ ነው፡፡

ለመጻፍ ስለተመረጠው ርዕስ ያለውን ሀሳብ በዝርዝር ማስፈር አንዱን ሀሳብ ብቻ መርጦ መጻፍ  ቢ.ጋር ማዘጋጀት ረቂቅ መጻፍ ረቂቁን ማስተካከልና ማሻሻል የመጨረሻውን ቅጂ መጻፍ፡፡ በተጨማሪም የጽሕፈትን ክሂል በምናስተምርበት ጊዜ የተማሪዎችን ፍላጎት ከግምት ማስገባት ተገቢ መሆኑን በመግለጽ ሲያብራሩ ተማሪዎች በቂ የጽሕፈት ልምምድ እንዲያደርጉ መርዳት የጽሑፋዊ ቋንቋን መግባቢያነት በተጨባጭ ማሳየት ተአማኒነት ያላቸውንና የተማሪዎችን ፍላጎት የሚቀሰቅሱ ክንውኖችን ማዘጋጀት  የጽሕፈትን ክሂል ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማስተማር ለተማሪዎች ተገቢውን እገዛ በማድረግ ሀሳባቸውን መካፈል የጽሕፈት ክሂልን የማስተማሪያ ዘዴዎችን ስኬታማ ለማድረግ ያግዛሉ፡፡

### 2.1.5 የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር

ይህ ዘዴ ከመፃፍ ክሂል አተገባበር ዘዴዎች የመጀመሪያው እንደሆነ Nunan(1989፣36) ይገልፃሉ ፡፡ አያይዘውም በውጤት ላይ ያተኮረ የመፃፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴ የሚያተኩረው ተማሪዎች በፃፉት የመጨረሻ ስራ ላይ ነው፡፡ዓላማው ተማሪዎች በሚያከናውኗቸው የጽህፈት ትምህርት ተግባራት ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የጻፏቸው ዓረፍተ ነገሮች ከሰዋሰው ፣ ከዓረፍተ ነገር አወቃቀር ፣ ከሀሳብ ቅንጅትና ከስርዓተ ነጥብ ወ.ዘ.ተ ይገመገማሉ ፡፡ በሌላ በኩል Richards (1990 ፣106) በውጤት ላይ ያተኮረ የመፃፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴ በተለያዩ አንቀፆችና ጽሁፎች የመዋቅር ቅንብር ስልት ላይ ተማሪዎች ልምምድ እንዲያደርጉ ይመራቸዋል ይላሉ፡፤ ምክንያቱንም ሲገልፁ የዘዴው ትኩረት ተማሪዎች ስህተት የሌለበት ጽሁፍ እንዲጽፉ ማስቻል ስለሆነ የተፈለገውን የጽሁፍ ቅርፅ እንዲያጠኑ በማድረግ ወደ ፊት ታዘው በሚፅፉት ነገር ላይ ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ ያደርጋቸዋ በማለትይገልፃሉ፡፡ ብዙ ምሁራን በክፍል ዉስጥ የሚከናወኑትን የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ስልቶችን በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመድቡታል፡፡

### ሀ. ውስን ጽሕፈት (controlled writing)

የውስን ጽህፈት መልመጃ በአብዛኛው ለጀማሪ ተማሪዎች ለሚካሄድ የጽህፈት ትምህርት የሚቀርብናተማሪዎች ወደመርጽህፈት ከመሸጋገራቸው በፊት የሚለማመዱበት የመጀመሪያው መልመጃ ነው፡፡ በውስን ጽህፈት ደረጃ ተማሪዎች ሥራቸውን የሚሰሩት የተሰጣቸውን ትዕዛዝ

በአግባቡ በመከተል ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ተማሪዎች ስህተት እንዳይሰሩ ለመቆጣጠር ነው፡፡ የክንውኑ ዓላማም ከስህተት የጸዳ ዐረፍተ-ነገርን ወይም አነስተኛ ጽሑፍን እንዲጽፉ ለተማሪዎች ዕድል መስጠት ነው፡፡ በሌላ በኩል Raimas(1983፣95) እንደሚገልጹት ውስን የጽህፈት መልመጃ ተማሪዎች የጽሑፍ ቅርጽና ይዘት ተሰጥቷቸው የሚያከናውኑበት በመሆኑ ተማሪዎች የራሳቸውን ሃሳብ የማፍለቅ ዕድል የላቸውም ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ በመምህር ቁጥጥር ሥር ናቸው፡፡ እነሱም ማሟላት የሚገባቸው ነገር በጣም የተወሰነ በመሆኑ ስህተት ለመስራትም ሆነ የራሳቸውን ቅርጽና ይዘት ለመከተል ዕድሉ የላቸውም፡፡ በውጤት ላይ ያተኮረ አቀራብ ውስን የጽህፈት መልመጃ ዓላማው ስህተትን በማስወገድ ላይ መሆኑንና በመማር ማስተማር የሚቀርቡ መልመጃዎችን ማሰብንና ፈጠራን የማይጠይቁ ናቸው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ (Mc Domough and Shaw 1993,178) እና (Harmer 1991,109) በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን፣ ባዶ ቦታዎችን መሙላት፣ ሞዴል ዐረፍተነገሮችን አስመስለው እንዲጽፉ ማለማመድ፣ ዐረፍተነገሮችን ማያያዝ፣ በሰንጠረዥ መልመጃ የቀረቡ ቃላትን በማቀናጀት ዐረፍተ-ነገር መስራት፣ ቅደም ተከተላቸው የተዛባ ቃላትን በማስተካከል ዐረፍተነገሮችን መገንባት፣ ዐረፍተነገሮችን ማያያዝና ሌሎችም ይገኙባቸዋል Raimas (1983፣17)፡፡

### ለ. መር ጽሕፈት (guided writing)

ይህ የጽህፈት ደረጃ ተማሪዎችን ከውስን ወደ ነጻ ጽህፈት የሚያሸጋግር ድልድይ ነው፡፡ በመር የጽህፈት መልመጃ ተማሪዎች የራሳቸውን አንዳንድ ሃሳቦች የመጨመር ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም ከውስን የጽህፈት መልመጃ ይልቅ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የተሻለ ነጻነት እንዳላቸው ምሁራኑ ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ pincas (1982፣126) መር ጽህፈት ከውስን ጽህፈት በተሻለ ለተማሪች ነጻት ይሰጣል፡፡ ነጻነቱ ግን በነጻ ጽህፈት ጊዜ ከሚያገኙት ያነሰ ነው፡፡ ምክንያቱም በመር የጽህፈት መልመጃ ጊዜ ተማሪዎች ሊከተሉት የሚገባ ሞዴል ይሰጣቸዋልና በማለት ያስረዳሉ፡፡ በሌላ በኩል Raimas (1983፣103) መር የጽህፈት መልመጃ ቁጥጥር ከውስን ጽህፈት ያነሰ የሚሆነው የሚሰጣቸው ጽሑፎች ቅርፅና ይዘት ሙሉ በሙሉ ለተማሪዎች ስለማይቀርብላቸው ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለውም በመር ጽህፈት ጊዜ ተማሪዎች አንድ የተጀመረን ውጥን ታሪክ፣ ደብዳቤ፣ አንቀጽ … እንዲያሟሉ የሚታዘዙ መሆኑን ነው፡፡ የሚጨምሩት ሃሳብ ግን በጅምር ከቀረው አንቀጽ ሃሳብ ጋር የሚስማማ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ የጽህፈት ተግባር ለተማሪዎቹ መነሻ የሚሆን ፍንጭ በመስጠት የራሳቸውን

ሃሳብ አክለው በጽሑፍ እንዲያቀርቡ የሚያለማምድ ነው። የሚቀርቡት ተግባራትም፡- በሰንጠረዥ የቀረቡ ሃሳቦችን ውደ ጽሑፍ መቀየር፣ በጅምር የቀሩ ጽሑፎችን ወይም ውጥን ታሪኮችን፣ ደብዳቤዎችንና ቅፆችን ወዘተ መጨረስ፣ የተዘጋጀ ቢጋርን ተጠቅሞ አንቀጽ መጻፍ፣ የቀረቡትን ነገሮች በማወዳደርና በማነጻጸር በጽሑፍ መግለጽና ተከታታይ ጥያቄዎችን በማቅረብ በጥያቄዎቹ የቀረቡትን ምላሾች መነሻ አድርጎ አጭር ታሪክ መጻፍ የሚሉት ይገኙባቸዋል Raimas (1983፣103)።

## ሐ. ነጻ ጽሕፈት (free writing)

ነጻ የጽህፈት መልመጃ ከመር የጽህፈት መልመጃ ቀጥሎ የሚመጣ በውጤት ላይ ያተኮረ አቀራረብ ዘዴ የመጨረሻ ደረጃ ነው። ይህ የጽህፈት መልመጃ ከመርም ይሁን ከውስን መልመጃዎች የበለጠ ለተማሪዎች ሰፊ ነጻነትን ይሰጣል።pincas(1982፣106) እደሚገልጹት ነጻ የጽህፈት መልመጃ ተማሪዎች በሚሰጣቸው ርዕስ ወይም በመረጡት ሃሳብ በራሳቸው የሚያከናውኑት መልመጃ ነው። ተማሪዎች ጽሑፉን የሚጽፉት ከራሳቸው አፍለቀው ሲሆን በሚጽፉት ነገር ላይም የሚደረገው ቁጥጥር የላላ ነው። pincas (1982፣110) በተጨማሪ ሲያብራሩ የነጻ ጽህፈት መልመጃ ትኩረት የሚሰጠው ሁሉንም ነገር እንዲጽፉ ሳይሆን የተማሩትን ለመጻፍ ብቻ ነው። ተማሪዎች በውስንና በመር የጽህፈት መልመጃ ያገኙትን ዕውቀትና ልምድ በማቀናት ራሳቸውን ችለው መጻፍ ይኖርባቸዋል። በነጻ የጽህፈት ትምህርት መልመጃ ምንም እንኳ ተማሪዎች በውስንና በመር የጽህፈት መልመጃዎች የተማሩትን እዲከተሉ ቢደረግም ሃሳቡን የሚያቀናጁት በራሳቸው ስለሆነ ሰፊ ነጻነት አላቸው። እንደ Raimas (1983፣7) ገለጻ ደግሞ ነጻ ጽህፈት ለሰዋሰዋዊ አጠቃቀምና ለስርዓተ-ነጥብ አጻጻፍ እንዲሁም ለትክክለኛነቱ ትኩረት የሚሰጥ ቢሆንም ተማሪዎች የራሳቸውን ሃሳብ የመግለጽ ዕድል አላቸው። Byren (1988) እንደሚሉት ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል አስፈላጊውን የባህርይ ለውጥ እንዲያሳዩ በማድረግ ረገድ መምህራን የሚጠቀሙበት የትምህርት አቀራረብ የላቀ ድርሻ አለው። የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት የተለያዩ አቀራረቦች አሉ። ይሁን እንጂ አንድ ወጥ የሆነና ትክክል ወይም ጥሩ የሚባል የማስተማሪያ ዘዴ የለም። ይህ የሆነበት ምክንያት የትምህርቱ ይዘት እንደየመምህራን የስልጠና ሁኔታ፣ የተማሪ ብዛት፣ የመማር ስልት፣ ችሎታ፣ ዳራ ወዘተ አንጻር ስለሚወሰን ነው። በመሆኑም እንደጽሁፉ ዓላማ ተገቢ የሆነውን የአቀራረብ ዘዴ መርጦ መጠቀም ያስፈልጋል (Raimas 1983፣ Ur 1996)።

### 2.1.6 የፅሁፈት ክሂል ትምህርት አቀራረቦች

በአሁኑ ጊዜ እየተሰራባቸዉ ያሉት የፅሁፈት ክሂል አቀራረብን ዉጤት ተኮር አቀራረብ፣ ሂደታዊ አቀራረብና ዘወግ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ናቸዉ በማለት Nunan (1989) እና Richards (1990) በሦስት እንደሚመደቡ ያስረዳሉ፡፡

#### 2.1.6.1 ውጤታዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ

ውጤታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የሚባለው ትኩረቱ በጽሁፉ የመጨረሻ ውጤት ላይ ማለትም ተማሪዎች ሰዋሰዋዊ ህግጋትን የተከተለ ጽሑፍ ማቅረባቸው፣ ስርዓተ-ነጥቦችን በተገቢው ቦታ መጠቀማቸውን፣ ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ አዲስ ነገር ለመፍጠር ሳይጨነቁ የተሰጣቸውን ሞዴል በመጠቀም ተመሳሳይ የሆነ ነገር ጽፈው ማቅረብ መቻላቸውን፣ መምህራን የሚሰጧቸውን ርዕስ መሠረት በማድረግ ተገቢ የሆነ ጽ ሁፍ ማዘጋጀታቸውን፣ የሚጽፉት ጽ ሁፍ ቅርፅ የተስተካከለ መሆኑን እንዲሁም ምንም ስህተት የሌለበት ጽ ሁፍ መጻፋቸውን የሚመለከት አቀራረብ ነው (Raimas፣ 1983)፡፡

ውጤታዊ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ እይታ መጻፍ ከአንድ ቦታ ተጀምሮ ከሆነ በአንድ ቦታ ደግሞ የሚቆም ወይም ቀጥተኛ አካሄድን የሚከተል ነው፡፡ ስለሆነም ጸሐፊው ጥሩ ጽሑፍ ለማቅረብ በርካታ ልምምዶችን ማድረግና የተለያዩ የመጻፍ ደረጃዎችን ማለፍ ይኖርበታል የሚለውን አይደግፍም፡፡

#### 2.1.6.2 ሂደታዊ የመፃፍ ክሂልት ምህርት አቀራረብ

ሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ቃሉ እንደሚያመለክተው ዋነኛ ትኩረቱ በውጤቱ ላይ ሳይሆን በአሰራር ሂደቱ ላይ ነው፡፡ ለሂደታዊ አቀራረብ መከሰት ምክንያት የሆነው በተለይ በ1960ዎቹ አጋማሽ ላይ የተነሱት የሂደት ተኮር አራማጆች ትምህርት አቀራረብ ላይ ጉልህ የሆነ ድክመት እንዳለበት በመግለጻቸውና ይህንንም በማመልከታቸው ነው፡፡ በሂደታዊ አቀራረብ ስልት ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዴት እንደሚያፈልቁ ከማሳየት ጀምሮ የጽሑፍ ረቂቃቸውን መላልሰው በማረም እንዴት የተሻለና ተቀባይነት ያለው ድርሰት መጻፍ እንደሚችሉ ማሳየት ላይ ያተኩራል፡፡ ይህም በመሆኑ ባሁኑ ጊዜ ሂደታዊ አቀራረብ ሰፊ ተቀባይነት አለው፡፡

በሂደታዊ አቀራረብ አካሄድ ተማሪዎች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ ቢነሱ የሚጽፉትን ጽሑፍ በጣም በተፋጠነ ሁኔታና ተለክቶ በተሰጠ ጊዜ ውስጥ ሰርተው ለመምህራቸው እንዲያስረክቡ አይጠበቅባቸውም፡፡ ከዚህ ይልቅ አቀራረቡ ተማሪዎች በጽሕፈት መማር ማስተማር ክፍለ-ጊዜ በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሰፊ የሃሳብ ልውውጥ እንዲያደርጉ፣

እንዲወያዩ ከርዕሰ ጉዳያቸው ጋር ግንኙነት ያላቸውን መፃሕፍትና ጽሑፎች እንዲያነቡ፤ አንብበውም ሀሳብ እንዲያፈልቁና በማስታወሻ እንዲያሰፍሩ እንዲሁም የመጀመሪያ ረቂቃቸውን በማዘጋጀት እርማት እንዲለዋወጡ ከዚያም በመጨረሻ እንዲጽፉ የሚያደርግ ነው፡፡

በሂደታዊ የጽሕፈት ትምህርት አተገባበር የሚከተሉትን ደረጃዎች በቅደም ተከተል ተግባራዊ እያደረጉ ማለፍ እንደሚያስፈልግ በመስኩ ተሰማርተው ጥናት ያደረጉ በርካታ ምሁራን የሚስማሙበት ሀሳብ ነው፡፡ እነርሱም፤

ሀ. ቅድመ ጽሕፈት ደረጃ (የማሰላሰልና የማብላላት)

ለ. የጽሕፈት ጊዜ ደረጃ (የማርቀቅ)

ሐ. ድህረ ጽሕፈት ደረጃ (የተፈጻውን መልሶ የማረም) ናቸው፡፡

## 2.1.6.2.1 የቅድ መጽሕፈት ደረጃ (የማሰላስልና የማብላላት)

በቅድመ ጽሕፈት ደረጃ ተማሪዎች (ጸሐፊዎች) ሀሳብ የሚያሰባስቡበት፣ አንባቢዎችን በዐይነ ህሊናቸው የሚያስቡበት፣ ጊዜያዊ ዕቅዳቸውን የሚነድፉበት፣ የሚጽፉባቸውን ርዕሰ-ጉዳዮች የሚመረምሩበት፣ ሀሳባቸውን እያቀናጁ የሚያዳብሩበትና ስለሚጽፏቸው ጽሑፎች ዓላማዎች ረጋ ብለው የሚያስቡበት ጊዜ ነው ማለት እንችላለን፡፡ከላይ እንደተገለጸው የቅድመ ጽሕፈት ጊዜ ደረጃ ተማሪዎች በመደበኛም ይሁን በኢ-መደበኛ ሁኔታ የቀሰሟቸውን ልዩ ልዩ ዕውቀቶች በጽሁፍ መልክ ለመግለጽ (አውጥቶ ለማሳየት) የሚዘጋጅበት ጊዜ ነው ብለናል፤ በመሆኑም በቅድመ ጽሑፍ ተማሪዎች፤

- ቀዳሚ ዕውቀታቸውን የሚገመገሙበት
- ልምዶቻቸውን የሚመረምሩበት
- ውስጣዊ እነሱነታቸውን የሚዳስሱበት
- አስከፊም ይሁኑ ደጋግ ገጠመኞቻቸውን የሚመረምሩበት ወቅት ነው፡፡

በመሆኑም ለረጅም ጊዜ በአዕምሮአቸው ሲመዘግቡ (ሲያከማቹ) የኖሩትን ልዩ ልዩ ዕውቀቶቻቸውን በጽሑፍ መልክ አቀናብሮ ለመግለጽ በቅድሚያ ወደ ውጭ ሳይሆን ወደ ራሳቸው ውስጣዊ ማንነታቸው ማሰብ ያለባቸው ጊዜም እንደሆነ መረዳት እንችላለን፡፡ ተማሪዎች በአእምሮአቸው የሚመላለሱትን የተለያዩ ጉዳዮችና ሁኔታዎች በሙሉ በዝርዝር በወረቀት ላይ እንዲያሰፍሩ በተለይ በሀሳብ ፈንጣቂ ዘዴ መጠቀም የተሻለ ሊሆን ይችላል፡፡

የዚህ ዘዴ ዓይነተኛ ዓላማም ለጽሑፉ ማዳበሪያ የሚሆኑ ዝርዝር ሀሳቦችን ማግኘት እንዲችል ለማድረግ ነው፡፡

### 2.1.6.2..2 የመጻፍ ጊዜ ደረጃ (ማርቀቅ)

ጊዜ መጻፍ የማርቀቅ ደረጃ ሲሆን በዚህ ደረጃ ሃሳብ በማፍለቅ ጊዜ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የማመቻቸትና የመጀመሪያ ረቀቅ መጻፍ የተጻፈውን የማንበብና የመከለስ፣ ጽሑፉ የሚዳብርበትን ሃሳብ የመፈለግ ተግባር ይከናወናል፡፡ ተማሪዎች በዚህ ጊዜ ለሰዋሰዋዊ ስህተቶች አይጨነቁም፤ ሃሳብ እንደመጠላቸው ይጽፋሉ፤ የማይፈልጉትን ሃሳብ አስወጥተው አዲስ ሃሳብ መተካት ይችላሉ፡፡ በመጻፍ ጊዜ ቅድሚያ የሚሰጠው ለይዘት ትክክለኛነት ሲሆን በቀጣይ ለሚጽፉት የድርሰት ረቂቅ ላይ ከይዘት ባሻገር ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸውን ስርዓተ-ነጥቦች፣ ሰዋሰውን፣ የፊደላት አጣጣልን ወዘተ የመመርመርና የማስተካከልተግባርን ያከናውናሉ፡፡Hedge (1991) በዚህ ደረጃ ጸሐፊ ያረቀቀውን ሃሳብ መግቢያ፣ ዋና አካልና መደምደሚያ በማለት ይከፋፍላሉ፡፡

### 2.1.6.2.3 ድኅረ መጻፍ ጊዜ ደረጃ (የተጻፈውን መልሶማረም)

ድኅረ መጻፍ የክለሳ ደረጃ ሲሆን ጸሐፊው የጽሑፉን መልዕክት ቅርፅንና ተደራሲ ደግሞ የሚያስብበት የመልዕክቱን ግልጽነት የሚገመግምበትና የመጨረሻ ማስተካከያ የሚያደርግበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ጸሐፊው በጽሑፍ ውስጥ ለአንባቢያን ያስቸግራሉ የሚላቸውን የተለያዩ ቃላት ለይቶ በማውጣት ማስተካከያ ይሰጣል፡፡ የተጻፈወን ጽሑፍ ከሰዋሰው፣ ከስርዓተነጥቦችና ከሃሳብ አደረጃጀት አኳያ የሚመረምርበት ደረጃ ነው፡፡ በመሆኑም የጸሐፊው ተግባር እንደተደራሲው አንባቢ በመሆን ጽሑፉን ማንበብ ነው፡፡ ንባቡም ግልጽ በሆነ መንገድ አንባቢዎቼ ለማለት የፈለግሁትን ሊረዱት ይችላሉ ወይ? የሚለውን ለመገምገም ነው፡፡ በተጨማሪም ለጽሑፉ ቅርጽና ይዘት ትኩረት በመስጠት እርማት ያደርጋል፡፡ የተዛቡ ሀሳቦች ካሉ ይስተካከላሉ፤ እርማቶችም የሚካሄዱት በተማሪዎች፣ በጓደኞቻቸውና በመምህራን አማካኝነት ይሆናል፡፡

### 2.1.6.3 ዘውግ ተኮር ትምህርት አቀራረብ

ዘውግተኮር አቀራረብ መጻፍን ማስተማር የተጀመረው 1980ዎቹ ገደማ ሲሆን ሀሳቡ የመነጨው በአውስትራሊያ ሀገር እንደሆነ Hylald (2010) ዋቢ በማድረግ እንደገለጹት ጀነር ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የሚያተኩረው አንድን ሁነት መሠረት በማድረግ የተለየ

ዓላማ ለማሳካት በማሰብ የሚቀርብ ሲሆን በቋንቋው ውስጥ ያለን የዲስኩር ገጽታ እንዲሁም አውድን መሠረት በማድረግ ጽሑፍን መጻፍን ይመለከታል፡፡ የጀነር ተኮር አቀራረብ መሠረታዊ መርህ ቋንቋ የራሱ የሆነ ተግባር አለው፡፡ ስለሆነም ቋንቋ የሆነ ግብን ለማሳካትና አውድን መሠረት ባደረገ መልኩ ለተግባቦት ዓላማ የምንገለገልበት መሳሪያ ነው Hylald (2010)፡፡ Hylald(2004)ን በመጥቀስ እንደሚያስረዱት ጀነር ተኮር በሆነው እይታ ሰዎች መጻፍ ስላለባቸው ብቻ የሚጽፉ መሆን የለባቸውም፤ አንድ ሰው አንድን ነገር የሚጽፈው ለተለየ ዓላማ መሆን አለበት በማለት ያብራራሉ፡፡

### 2.1.7 የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደቶች

በ1960ዎቹ መጨረሻ የመጻፍ ክሂል ትኩረት እየተሰጠበት መጣ፡፡ ወደ መደበኛ የድርሰት ጽሕፈት ሂደት ተገብቶበታል፡፡ ይህም /Chomsky's (1957, 1965)/ የአዕምሮአዊያን ፍልስፍና መምጣት ጋር ተያይዞ የመጣትምህርት ነው፡፡ የስነ-ልቦናና የሰነ-ልሳን ባለሙያዎች እደሚሉትም ህጻናት ንቁ እንጂ ፍዝ የቋንቋ መማር ሂደትን አይከተሉም፡፡ /Braddock, Lioyd-Zonas and Schoes (1963)/ የተባሉት ተመራማሪዎችም የሰዋሰው ትምህርት የተማሪዎችን ጽሕፈት ያሻሽላል በማለት ያጠኑ የመጀመሪያዎች ናቸው፡፡ /Emig's 1971/ ጥናት የጽሕፈት ሞዴል ብቅ ያለበት ጊዜ ነበር፡፡ ይህ ሞዴልም ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡

1. የማቀድ ደረጃ - ሀሳብ ማፍለቅ ነው
2. የመተርጎም ደረጃ - የመነጨውን ሀሳብ መጻፍ ነው
3. የክለሳ ደረጃ - ጸሐፊ ጽሑፉን የሚገመግምበትና የሚከልስበት ደረጃ ነው፡፡ /Flower and Haymes, 1981/

የዚህ ሞዴል ጠንካራ ነገር መምህራን ጽሕፈትን እንዴት እንደሚያስተምሩ አቅጣጫ የጠቆመ ነበር፡፡ ጥናቶች እየበዙና ትኩረት እየሰጡት ሲመጡም በርካታ ውጤቶች ተስተውለዋል፡፡ እንደ ጥናቶች ጽህፈት ውጤት ሳይሆን ሂደት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሰዋሰውና የፊደል ትኩረት እንደቀነሰ ተስተውሏል፡፡ ጽሕፈት ውስብስብ ፈጠራዊ ሂደት ነው፡፡ይህ አቀራረብ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ከነበረበት ውድቀት /መረሳት/ ወጥቶ ትኩረት እንዲያገኝ ሽግግር የፈጠረ ነበር፡፡ በተለይም ከቅርፁ ይልቅ በሂደቱ ላይ ማተኮር እንዳለበትም ያሳየ አቀራረብ ነው፡፡ ለ1960ዎቹ መጨረሻ ወይም በ1980ዎቹ መጀመሪያ የጽሕፈት ክሂል ወደ አዲስ ምዕራፍ የተሸጋገረበት ነበር፡፡ ይኸውም ትኩረቱ ማኅበረ-ባህላዊ አውድ እንዲሆን አሳይቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የዲስኩር ትንተናን አመላክቷል፡፡ ጥናቶችም እንዳመከለቱት የቋንቋ ጥናት ከአረፍተ ነገር በላይ

መሆን እንዳለበት አመላክተዋል፡፡አቀራረቡም በርካታ የቋንቋ ዲስኩር ጥናቶች እንዳሉ ያመለከተሲሆን የፅሕፈት አደረጃጀት ሦስት ዋና ዋና አካሄዶችን እንደሚከተልም አሳይተዋል፡፡የጥያቄ-መፍትሄ አደረጃጀት የመላምት-እውነታ አደረጃጀት የአጠቃላይውሱን አደረጃጀት ናቸው /Haliday, 1978/፡፡እንደአቀራረቡ ደጋፊዎች አባባል ለጽሕፈት ወሳኝ መሠረት ነው፡፡ ጽሕፈት በራሱም ተለዋዋጭ፣ ፈጠራዊ፣ አውዳዊ ሂደት ያለውና በጽሑፈ (በምንባብ) የመግባባት ሂደት ነው፡፡

የተግባቦታዊ ብቃቶች ማዕቀፍ ውስጥ ጽሕፈትን ማስተማር በተግባቦታዊ ብቃት ውስጥ የሰዋሰው ብቃትና የቋንቋ አጠቃቀም ብቃቶች በ Chomsky ስራ ውስጥ የተዘነጉ (ከብቃቱ ውጭ የሆኑ ነበሩ)፡፡ ከ1980ዎቹ ጀምሮ ግን ተግባቦታዊ ብቃት ብያኔው እየተሻሻለና በቋንቋ ማስተማር ረገድም ትኩረት ያገኘበት ጊዜ ነበር፡፡ የተግባቦት ብቃትን ከማጎልበት አንጻር የጽሕፈት ክሂል የጎላ ሚና ይጫወታል፡፡መጻፍ የአንባቢውን ማንነት ባገናዘበ መልኩ መልዕክትን በጽሕፈት የማስተላለፍና ውስጣዊ ስሜትን የመግለጽ ሂደት ነው Byren፣1988/፡፡ በተመሳሳይ /፣ Maino1993/ የመጻፍ ክሂል ሲነሳ መልዕክት አስተላላፊነቱ ቀዳሚው ነገር እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ከእነዚህ ሀሳቦች የመጻፍ ክሂል ዋናው ቁምነገር መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡መጻፍ የማሰብ ሂደት ነው፡፡ ይህም ሰዎች ቃላትን ገጣጥመው ሀሳባቸውንና ስሜታቸውን በሚገልጹበት ጊዜ የሚከሰት ነው፡፡ መጻፍ ማለት የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ፊደላትን በጽሑፍ ከመግለጽ የራቀ አንድምታ ያለው ክሂል ነው /Byren፣ 1988/፡፡

Hrmischer (1979) hyit (1985) ጠቅሰው phil (2013) የመጻፍ ክሂልን በበርካታ የማሰብ ሂደቶች ውስጥ የሚያልፍ ሰፊና ውስብስብ ክሂል እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ይህም አንድ ሰው በአእምሮው ውስጥ ያለውን ሃሳብ ሲጽፍ፣ ሲተረጉም፣ ሲገመግም፣ ረቂቁን ሲከልስ በተግባር የሚታይ ሲሆን ማሰብን፣ ማቀድን፣ መጻፍን ማንበብን፣ እንደገና መጻፍን፣ መከለስንና ማስተካከልን የሚያልፍ ብዙ ውስብስብ ሂደቶችን የሚሻገር ክሂል እንደሆነ phil (2013) ጨምረው ያስረዳሉ፡፡ ማረው (1998) በበኩላቸው ከላይ ከቀረቡ ሀሳቦች ጋር የሚስማማ አተያይ አላቸው፤ መጻፍ አብዝቶ ተግባራዊ ልምድን የሚሻ ክሂል ነው፡፡ ሊዳብርና ሊያድግ የሚችለውም በዚሁ ተግባራዊ ልምምድ ነው፡፡ ተማሪዎች ወደ መጻፍ ከመግባታቸው በፊትም ሆነ በሚጽፉበት ጊዜ በቅደም ተከተል የሚያልፏቸው በርካታ ሂደቶች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

አጥኝዋ ይህ ጥናት ከመጠናቱ በፊት ስለፅህፈት ክሂል አተገባበር የተሰሩ የተለያዩ ሀገራዊ ጥናቶችን ዳሳለች፡፡ አጥኝዋ ይዛው የተነሳችው ርዕሰ ጉዳይ በግልና በመንግስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽህፈት ክሂል ትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመስል በንፅፅር ማጥናት ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ቀደምት ጥናቶች ተዳሰዋል፡፡

ሰይድ (1993) "በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን የጽህፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ትግበራ" በሚል ርዕስ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጥናት ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ጽህፈትን በተግባር እየተለማመዱ እንደማይማሩና የቢጤ እርማትም ተግባራዊ እንደማይሆን የገለጹ ሲሆን በጥናታቸው ውጤት ማጠቃለያላይ የጽህፈት ትምህርት ተግባር ዝቅተኛ ደረጃላይ እንደሚገኝአመላክተዋል፡፡ በመሆኑም የተመራማሪው ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የጽህፈት ትምህርት አተገባበር ላይ ስያተኩርየኔ ጥናት ደግሞ የሚያተኩረው የጽህፈትክሂልን ትምህርት አተገባበር በንጽጽር በመፈተሽ ችግሮችን ለይቶ የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ ላይ ስለሆነ፤እንዲሁም በክፍልደረጃ፣ ጊዜና ቦታ ስለማይገኝ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡

ጌታቸው (2001) "በደብረማርቆስ ከተማ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት"በሚል ርዕስ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸውን ያቀረቡ ሲሆን በደብረ ማርቆስ ከተማ በሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚማሩ የ8ኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል በጹሑፍ ክሂል ችሎታ የትኞቹ እንደሚሻሉ ለማጥናት ሞክረዋል፡፡በመሆኑም ተማሪዎችን በተራ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በመምረጥ ድርሰት እንዲጽፉ በማድርግ ና ተማሪዎችና መምህራን የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ በማድረግ በ100 ወንድ ተማሪዎች ላይ በተደረገው ጥናት የተገኘው ውጤት አንጻራዊ በሆነ መልኩ ወንድ ተማሪዎች  በጽህፈት ክሂል የተሻሉ መሆኑን በጥናታቸው አመልክተዋል፡፡

ኢሳያስ (2002) "የጽሐፍ ክሂልን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የትምህርት አደረጃጀታቸው 10+2 የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ደብዳቤለመፃፍያላቸው ብቃት በጎባና ሮቤ መሰናዶ ትምህርት ቤት ናሙናነት" በሚል ርዕስ የማስተርስ ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ያቀረቡ ሲሆን ጥናቱን ለማካሄድ አይነታዊና መጠናዊ የአጠናን ዘዴዎችን በመጠቀም  አመቺ የናሙና አመራረጥ

ዘዴን በመጠቀምና ተማሪዎችን ደብዳቤ በማስፃፍ፣ መምህራንና ተማሪዎችን የጽሑፍ መጠይቅ በማስሞላት መረጃዎችን አሰባስበዋል፡፡ ከጥናቱም የተገኘው ውጤት በጽህፈት ትምህርት ሂደት ውስጥ የመሰናዶ ተማሪዎች መገንዘብ የሚገባቸውን የደብዳቤ አፃፃፍ እውቀት በተገቢው መንገድያልጨበጡና በትምህርት ቤት ሕይወታቸው ውስጥ የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያዎችንና ስልቶችን በትክክልያልተረዱ መሆናቸውን በጥናት ውጤታቸው አመልክተዋል፡፡

ስዩም ከበደ(1988) ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ለ9ኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት በሚል ርዕስ በአካሄዱት ጥናት የፅህፈት አቀራረብን (ስነ ዘዴን) ተጠቅሞ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፅህፈትን ማስተማር ከሂሉን ለማዳበር ውጤታማ ሆኖ መገኘቱን ማረጋገጣቸውን ገልፀዋል፡፡ የደረሱበት ማጠቃለያም ተጠኝዎቹ በቡድን ሲረዳዱ የቢጤ እርማት ሲያካሄዱ ከሚፈጠረው ጫጫታና ከአንዳንድ ተማሪዎች መቅረት የተነሳ ከሚከሰተው የቡድን ስራ መዛባት በስተቀር ሂደታዊ ዘዴ በተግባር ላይ ቢውል ከፍተኛ ጠቀሜታን እነደሚያስገኝ በጥናታቸው ገልፀዋል ፡፡

ሰለሞን ዮሐንስ (1991) የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጂ እና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ በሚልርዕስ ባደረጉት ጥናት የተማሪዎች ልምድ ሳይጠበቅ መምህራን በራሳቸው ምርጫ ብቻ በፈለጉት መንገድ ተማሪዎች ድርሰት እንዲፅፉ ለማድረግ መሞከር እንደሌለባቸው ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ ባተኮረበት በሀዋሳ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሲያስተምሩ የነበሩት መምህር ህግን መሰረት አድርገው በተማሪዎች ድርሰቶች ውስጥ ስህተትን በመፈለግ ላይ ሲያተኩሩ በመገኘታቸው ይህ መምህር ተኮር የሆነ የማስተማሪያ ዘዴ ድርሰትን በማስተማርና በተማሪዎች ድርሰትን የመፃፍ ስትራቴጂ መካከል ክፍተት ስለፈጠረ የድርሰት ትምህርት አላማ የተማሪዎችን የመፃፍ ስትራቴጂ በማሳደግ ላይ ሊያተኩር እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡትየጥናት ስራዎች በጽህፈት ክሂል ላይትኩረት ከማድረጋቸው አንፃር ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ዝምድና ቢኖርም ይዘውት ከተነሱት የጥናት ዓላማ፣ ከክልላቸው /ከጥናቱ ቦታ/ ጊዜ ልዩነት ፣በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣በናሙና አመራረጥ፣ከጠናቱ አካሄድ ወዘተ አንፃር ከኔ ጥናት ይለያል፡፡ ምክንያቱም የኔ ጥናት የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽህፈት ክሂል አተገባበር ላይ አተኩሮ እያነፃፀረ የሚያቀርብ ነዉ፡፡

በተጨማሪም እነዚህ ጥናቶች በመፃፍ ክሂል ትምህርት በአማርኛ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች አደረጃጀት የመምህራን የማስተማር ስነ ዘዴና ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጂ፣ በግልና በቡድን የሚፃፉ ድርሰቶች  ንፅፅራዊ ጥናት ፣ እንዲሁም ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ማስተማር ባለውተግባራዊነት ላይ በመመስረት የቀረቡ ናቸው፡፡ ስለዚህየኔ ጥናት በመፃፍ ክሂል አተገባበር ላይ በማተኮር የግል እና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበርን በማነፃፀር የሚፈትሽበመሆኑ ከእነዚህ ሥራዎች የተለየ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፤የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

## 3.1.የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ገላጭየምርምር ስልትን የተከተለ ነው።ጥናቱ ትኩረት የሚያደርገውም በመቱ ከተማ በሚገኙ የመንግስት እና የግል ትምህርት ቤቶችበሚያስተምሩየ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ በማተኮር በክፍል ውስጥ በሚሰጠው የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ላይ የትኞቹ እንደሚሻሉ በንጽጽር ለመግለፅ ሞክሯል። ጥናቱም ከዓይነታዊ የምርምር ዘዴ በተጨማሪ በመጠናዊ የምርምር ዘዴ የሚገኙትን መረጃዎች ለመተንተን በረዳትነት በስራላይ ዉሏል።

## 3.2 የጥናቱአካላይ

ይህ ጥናት የሚካሄደዉ በኦሮሚያ ክልል በኢሉባቦር ዞን በመቱ ወረዳ ዉስጥ በሚገኙ ሁለት የግልና ሁለት የመንግስት ትምህርት ቤቶችን የሚያካልል ነዉ። በመቱ ከተማ ከሚገኙ ሦስት የግል ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ሁለቱን እንዲሁም በመቱ ከተማ ከሚገኙ ስድስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ሁለቱን በእጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በመጠቀም ተመርጠዋል። ስለዚህ ይህ ጥናት የሚያካልለዉ በመቱ ከተማ በሚገኙ ሁለት የመንግስት ትምህርት ቤቶችና ሁለት የግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የ8ኛ ክፍል መምህራን ላይ በማተኮር የሚያጠና ነዉ።በመቱ ከተማ ከሚገኙ የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ፈተንሳ ኢሉ እና ፈለገ ጥበብ የግል ትምህርት ቤቶች እና ቱሉቤና ቢሻሪ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በእጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል።በናሙናነት የተመረጡት ሁለት የግል እና ሁለት የመንግስት በድምሩ አራትየመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸዉ። ጥናቱ በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር በማነፃፀር የሚያቀርብ በመሆኑ በሁለት የግል እና በሁለትየመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል፡

### 3.3 የናሙና አመራረጥ

#### 3 3.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

በመቱ ከተማከሚገኙ ሶስት የግል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ስድስት የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በዕጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ሁለት የግልናሁለትየመንግስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡ በነዚህ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ላይ በማተኮር የመምህራንን የፅህፈት ክሂል አተገባበር ምን እንደሚመስል እና የትኞች እንደሚሻሉ በንጽጽር ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡

በመቱ ከተማ በሚገኙ ፊተንሳኢሉና ፊለገ ጥበብ የግል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እናቱሉቤና ቢሻሪ የመጀመሪያ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በእጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል ፡፡ በናሙናነት የተመረጡት ሁለት የግልና ሁለት የመንግስት በድምሩ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ጥናቱ በግልና በመንግስት ትምህርትቤቶች የሚገኙ 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ትምህርት አተገባበር የሚያነፃፅር በመሆኑ በሁለት የግልና በሁለት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል ፡፡

#### 3.3.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው የክፍል ደረጃ የ8ኛ ክፍል ነው፡፡ የክፍል ደረጃዉ የተመረጠውም በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ሲሆን በክፍል ደረጃው ያሉት ተማሪዎች የተመረጡት የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዉ ወደ ሁለተኛ ደረጃ የሚገቡበት የክፍል ደረጃ ስለሆነየመምህራኖቻቸዉን የመፃፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ መርምረዉ በንፅፅር ለማቅረብና ለመገምገምይችላሉተብሎ ስለታመነ ነው፡፡በተጨማሪም አጥኝዋም የምታስተምረው የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን ስለሆነም ጭምር ነዉ፡፡

#### 3.3.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በተተኳሪዎቹ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ የተመረጡት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት የመንግስት30፤የግል 30 በድምሩ 60 ናቸው፡፡ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች በእያንዳንዱ ክፍል የሚገኙት ተማሪዎች ቁጥርም በመንግስት ከ 55-56፤ ከግል ደግሞ 28-33 ይደርሳል፡፡ ይንንም የስም መቆጣጠሪያ መዝገብ በማየት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ዉስጥ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን ለመጥቀስ ያህል ከግል ትምህርት ቤትፊተንሳ ኢሉ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት 97 ሲሆኑ 45 ወንዶች እና 52 ሴቶች ተማሪዎች

ሲገኙ በሶስት ክፍሎች ተከፍለው ይማራሉ ። 8ኛ A 15 ወንድ ተማሪዎችና 17 ሴት ተማሪዎች በአጠቃላይ 32 ተማሪዎች ሲሆኑ 8ኛ B የሚማሩ ተማሪዎችም 14 ወንድ አና 18 ሴት ተማሪዎች በጥቅሉ 32 ተማሪዎች እንዲሁም 8ኛC የሚማሩ ተማሪዎች ደግሞ16 ወንድ አና 17 ሴት ተማሪዎች በአጠቃይ 33 ተማሪዎች ናቸው።በፊለገ ጥበብ የግል ትምህርት ቤት የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችንም ብናይ ቁጥራቸው 84 ሲሆን 40 ሴት ተመሪዎችና 44 ወንድ ተመሪዎች ሲገኙ እነዚህም በሶስት ክፍል ተከፍለው ይማራሉ ። የ8ኛA ክፍል ተማሪዎች 28 ሲሆኑ 13 ሴትና 15 ወንድ ተማሪዎች ፣ 8ኛB ብዛታቸው 28 ሲሆን 14 ወንዶች ና 14 ሴቶች ፣በተመሳሳይ መልኩ 8ኛC የሚማሩትም ቁጥራቸው 28 ሲሆን 13 ሴትና 15 ወንድ ተማሪዎች ይገኛሉ፡፤

የመንግስት ትምህርት ቤቶችንም ብናይ ቱሉቤ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 8ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር 222 ሲሆን 122 ሴቶችና 100 ወንዶች ተማሪዎች ይገኛሉ፡፤ እነዚህ ተማሪዎች የሚማሩት በ4 ክፍል ተከፍለው ሲሆን በያንዳንዱ ክፍል 55-56 ተማሪዎች ይገኛሉ።ቢሻሪ 1ኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤትንም ብናይ አጠቃላይ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት 155 ሲሆን 75 ወንዶችና 80 ሴት ተመሪዎች በትምህርት ቤቱ ይገኛሉ። እነዚህ ተማሪዎች በሶስት ክፍል ተከፍለው የሚማሩ ሲሆን በእያንዳንዱ ክፍል ከ 50-55 የሚደርሱ ተማሪዎች ይገኛሉ።

በአጠቃላይ ከላይ ከጠቀስናቸው ከግል ትምህርት ቤቶች በደረጃ የወጡ 30 ተማሪዎችን እንዲሁም ከመንግስት ትምህርት ቤትም እንደዚሁ በደረጃ የወጡ 30 ተማሪዎችን ባአጠቃላይ የተመረጡ 60 ተማሪዎችን የጽሁፍ መጠይቁን በማስሞላት መረጃ ተሰብስቦ ጥናቱ ተካሂዷል።

### 3.3.4. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በተተኳሪዎቹ ትምህርት ቤቶች በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ ከሚያስተምሩ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋመምህራን መካከል ከግል ሁለት ከመንግስት ሁለት በድምሩ አራትመምህራን ለዚህ ጥናት ተመርጠዋል። እነዚህም መምህራን የተመረጡት በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ሲሆን ከአራቱም የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች አራት መምህራን ተመርጠው ለአራቱም መምህራን ሦስት ሦስት ጊዜ ምልከታ ተደርጎባቸዋል። ምልከታውም የተደረገው የአማርኛ ቋንቋ በሳምንት አንድ ክፍለ ጊዜ ብቻ ስለሆነ ከተህሳስ እስከ ጥር መጨረሻ በአራቱም ትምህርት ቤቶች በመዘዋወር ምልከታው ተከናውኗል።ምልከታውም ለእያንዳንዱ መምህር

ሶስት ሶስት ጊዜ በመግባት በአጠቃላይ አስራ ሁለት ጊዜ በየክፍሉ ምልከታ በማድረግ መረጃውን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ1የተጠኚ መምህራን ዳራዊ መግለጫ**

| ትምህርትቤት | የተጠኝ መምህራን ኮድ | ፆታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | የሰለጠኑበት የትምህርትዓይነት | የሥራ ልምድ (ዓመት) | በሳምንት የሚያስተምሩት የክፍለ ጊዜ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የግል | 01 | ወ | 49 | ዲግሪ | አማርኛ | 25 | 10 |
| | 02 | ሴ | 36 | ዲግሪ | አማርኛ | 16 | 8 |
| የመንግስት | 03 | ሴ | 33 | ዲግሪ | አማርኛ | 13 | 12 |
| | 04 | ወ | 40 | ዲግሪ | አማርኛ | 20 | 15 |

ከላይ ከቀረበው የመምህራን ዳራዊ መግለጫ ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው በግልም ሆነ በመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመረጡ ተጠኝ መምህራን ብዛት 2 ወንድና 2 ሴት ናቸው፡፡ የተጠኝዎችን ዕድሜ ስንመለከትም የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህራን 49 ና 36ሲሆኑ፤ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህራን ደግሞ 33 ና 40ናቸዉ፡፡ በአጠቃላይ ከመምህራን ዳራዊ መግለጫ እንደምንረዳው በግል ትምህርት ቤቶች የሚገኙት መምህራን ፆታ፣ ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት፣ የሥራ ልምድና በሳምንት የሚያስተምሩት የክፍለጊዜ ብዛት በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር በምናነፃፅርበት ጊዜ የጎላ ልዩነት አይታይም፡፡ ስለዚህ ከመምህራን ዳራ አንጻር በመምህራን የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ላይ ይህ ጥናት ተፅዕኖ እንደማያመጣ መረዳት ይቻላል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሚባሉት ጥናቱ እውን እንዲሆን ተገቢ መረጃዎች በአግባቡ የሚሰበሰብባቸው መንገዶች የሚያብራራ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ ለጥናቷአስፈላጊና ተገቢ

ናቸው ያለቻቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተከትላለች። እነሱም ፡-ምልከታ የፅሁፍ መጠይቅ እና፤ ቃለ መጠይቅ ናቸው ።

### 3.4.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ

ለዚህ ጥናት ተገቢናቸው ተብለው ከተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ የክፍል ውስጥ ምልከታ አንዱ ነው። የምልከታ ዘዴ መረጃ ሰብሳቢው ሰው መረጃ ለማሰባሰብ የሚፈልግባቸው ተጠኚዎች የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ፤የሚፅፉትን በመገንዘብና በቅርበት ሆኖ እያየና እየሰማ ትክክለኛ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው። በመሆኑም አጥኚዋ የጥናቷ ተተኳሪዎች በሆኑት ሁለት የመንግስትና ሁለት የግል ትምህርት ቤቶች በመገኘት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት ክሂል ትምህርትን ሲተገብሩ ምልከታ በማድረግ ጥናቷን አካሄዳለች።

በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የሚያገለግሉ የምልከታ አይነቶች ካንድ በላይ ቢሆኑም ለዚህ ጥናት አላማውን ያሳካል ተብሎ የተመረጠው የምልከታ አይነት ውስን ምልከታ ብቻ ነዉ።ይህ የምልከታ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት አጥኝዋ በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት በክፍል ውስጥ በመምህራን ከሚተገበሩ ክንውኖች መካከል የምትፈልጋቸውን መረጃዎች ለማግኘት የመምህራንን የመፃፍ ክሂል አተገባበር የሚያሳይ የማመሳከሪያ ቅፅ በማዘጋጀት በቅጹ አማካኝነት የመምህራንን የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱን ተከትላ ለመገምገም ብሎም ለማነፃፀር የሚያስችል ሆኖ በመገኘቱ ነው።በተጨማሪም ከዚህ በፊት በተለያዩ ምሁራን የተሰሩ ጥናቶችም የምልከታን ዘዴ አሰተማማኝ መሆን ሰለሚገልፁ ምልከታን ተመራጭ ያደርገዋል።

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው Fallick and Brown (1983: 29) እንዳስቀመጡት ፣በክፍል ውስጥ የሚታዩ ክንውኖች በሚገልፁ፡- በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ በሚሉት የመረጃ መለኪያዎች የሚቀርብ ነዉ። በዚህ መሰረት የተዘጋጀው የማመሳከሪያ ቅፅ በአማካሪ ከተገመገመ በኋላበተሰጠው አስተያየት መሰረት ማሻሻያ ተደርጎበታል።በመጨረሻም በናሙናነት የተመረጡት ትምህርት ቤቶች ክፍልውስጥ በመገኘትበነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በእያንዳዱ ትምህርት ቤት በእያንዳዱ ክፍል ሶስት ሶስት ጊዜ ምልከታ የተደረገ ሲሆን 12 ጊዜምልከታ ተደርጎ መረጃ ተሰብስቧል።

### 3.4.2. የፅሁፍ መጠይቅ

ለተማሪዎች የሚቀርበው የፅሁፍ መጠይቅ በምህራፍ ሁለት ውስጥ የተነሱትን ንድፈ -ሃሳቦች መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ መጠይቁ በምልከታ የተገኘውን መረጃ የበለጠ ለማረጋጋጥ፣ለማጠናከርና ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት ታስቦ ተግባራዊ የሆነ ነው ፡፡ የጽሑፍ መጠይቆች ጊዜን ፣ወጭንና ድካምን በሚቀንስ መልኩ መረጃዎችን በስፋት እና በጥልቀት ለመሰብሰብ የሚያስችል በመሆኑ ከሌሎች መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በበለጠ አጥኚዎች ተመራጭ እንደሚያደርጉት Kumar (2005:142) ፣David (2005:194) እና Lingren (1983:390) ይገልፃሉ፡፡

የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ተዘጋጅቶ እንዲሞላ የሚደረግበት ምክንያት ተማሪዎች ከመምህራን ጋር ያላቸው የትምህርት ቆይታ ረዘም ያለ ጊዜ በመሆኑ የመምህራንን የክፍል ውስጥ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ገምግሞ መረጃ በመስጠት እና የክፍል ምልከታውን ውጤት አስተማማኝ በማድረግ ረገድ እገዛ ያደርጋሉ በሚል ነው፡፤

የፅሁፍ መጠይቁም ሦስት ክፍሎች አሉት፡፡የመጀመሪያው ክፍል ስለመጠይቁ መግለጫ ፣የሁለተኛው ክፍል መጠይቁን ስለሚሞላ ግለሰብ አስፈላጊ የሆኑ አጠቃላይ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል ሲሆን ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የፅህፈት ትምህርትን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን የሚይዝ ነው፡፡ጥያቄዎችም የመምህራንን የክፍል ውስጥ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ለመፈተሽ ከተዘጋጀው የክፍል ውስጥ ማመሳከሪያ ቅጽ ጋር ተመሳሳይነት እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡በተጨማሪም ይህ ክፍል ተማሪዎች የሚያዉቁትን እንዲመልሱ እድል የሚሰጡ የክፍል ጥያቄዎችን እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

### 3.4.3. ቃለ-መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ መረጃ የሚሰበሰብበት ሌላው መሳሪያ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከቃለ መጠይቅ አይነቶች ውስጥ ነፃ ቃለ መጠይቅ ስራ ላይ ዉሏል፡፡ምክንያቱም ቃለ መጠይቁን የሚደርጉት መምህራን ነፃ ሆነው እንዲናገሩ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡ተሳታፊዎችም ከሁለቱ ትምህርት ቤቶች የተመረጡ አራት መምህራንናቸዉ፡፡

## 3.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በክፍል ውስጥ ምልከታዎች ፣ በተማሪዎች የሚሞሉየፅሁፍ መጠይቆች፣ ቃለ መጠይቆች እና ከተለያዩ ተዛማች ፅሁፎች ቅኝት አማካኝነት መረጃዎችን ለማሰባሰብ

ጥረት አድርጓል። በዚህ ዘዴ የተገኘዉ ውጤትም የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንዲቻል ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም እና በረዳትነት ደግሞ መጠናዊዉን በመጠቀምትንተና ተካሄዷል። በመሆኑም ከክፍል ምልከታው፣ ከተለያዩ ተዛማች ፅሁፎች ቅኝት ፣ከቃለ መጠይቁ እና ከፅሁፍ መጠይቁ የተገኙት መረጃዎች በገለፃ እንዲሁም በዓሀዝ ተተንትነዋል።በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ የሚተነተኑት መረጃዎች በገለፃ መልክ የሚቀርቡት እና ገላጭ የሆኑት ሲሆኑ ፤በመጠናዊ የምርምር ዘዴ የሚተነተኑት ደግሞ በቁጥር የሚሰሉ ወይም ምን ያህል ይሆናሉ የሚሉት መረጃዎች የሚቀርቡበት እና በስራ ላይ የሚውሉ ናቸዉ።

# ምዕራፍ አራት፤የመረጃ ትንተናና የዉጤት ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በመቱ ከተማ በሚገኙ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበርን በማስመልከት የትኞቹ የተሻለ አተገባበር እዳላቸው መፈተሽ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ይህ ጥናት የሚፈትሻቸው ንዑሳን ዓላማዎች

- የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል አተገባበር ምን ይመስላል
- የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል አተገባበር ምን ይመስላል
- በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የመጻፍ ክሂል ትምህርትን የሚተገብሩባቸው ስልቶች ምን ምን እንደሆኑ መመርመር የሚሉት ጉዳዮች ናቸው፡፡

በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ በጥናቱ ዓላማ ለተነሱት ነጥቦች ምላሽ ለማግኘት በክፍል ምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

### 4.1.1 ከተጠኚ መምህራን ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ጥናት ዉስጥ ለተጠኚ መምህራን ምልከታ በማድርግ መረጃ መሰብሰብ በዋንኛነት የተመረጠዉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነዉ፡፡ ምልከታ የተዘጋጀዉም ለተጠኚ መምህራን ነዉ፡፡ ምልከታዉም መምህራን የመፃፍ ክሂል ትምህርትን በክፍል ዉስጥ ሲተገብሩበመመርመር በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከናወኑትን ተግባራት ለማወቅየሚካሄድ ምልከታ ነዉ፡፡ስለዚህ ከምልከታዉ ተገኘዉ መረጃ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

#### 4.1.2.አጠቃላይየመምህራንየመፃፍክሒልአተገባበርደረጃ

የመምህራን የክፍል ውስጥ የመፃፍ ክሒል ትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመሥል ለመገምገም የሚያስችሉ Fallick and Brown (1983:29) ያስቀመጧቸው የደረጃ መለኪያ ማዕቀፎች አሉ፡፡ ማዕቀፎችም ከ1.00-1.80 ያሉት በጣም ዝቅተኛ፤ከ1.81-2.61 ዝቅተኛ ፤ከ2.62-3.42 መካከለኛ፤ከ3.43-4.23 ከፍተኛ እና ከ 4.24-5.00 ያሉት ደግሞ በጣም ከፍተኛ በሚል ደረጃ የተከፋፈሉ ናቸዉ፡፡

እነዚህ ማዕቀፎችን በመቀጠልም በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያሥተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አጠቃላይ የግምገማ ውጤታቸው መሠረት በየትኛው ደረጃ እንዳሉ ለማረጋገጥ ከክፍል ምልከታውና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው አማካይ ውጤት በሚከተለው ሠንጠረዥ ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

የመገምገሚያ ነጥቦች 1 = በጣም ዝቅተኛ 2 = ዝቅተኛ 3 = መካከለኛ

4 =ከፍተኛ 5 = በጣም ከፍተኛ

**ሠንጠረዥ 2፡ የመምህራን የመጻፍ ክሂል አተገባበር ደረጃ**

| ተ.ቁ | መምህሩ/ሯ በክፍል ዉስጥ ፅህፈትን በሚያስተምሩበት ወቅት የሚያከናዉኗቸዉ ተግባራት | የመምህራን የክፍል ምልከታ ግምገማ ድምር ዉጤት በአማካይ ና ደረጃቸዉ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የግል ትምህርት ቤት | የተሰጣቸ ዉ ደረጃ | የመንግስት ትምህርት ቤት | የተሰጣቸ ዉ ደረጃ |
| | I. **የቅድመ መፃፍ ትምህርት ተግባር** | | | | |
| 1. | የእለቱን ትምህርት ርዕስ ማስተዋወቅ | 5 | በጣም ከፍተኛ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ |
| 2. | የእለቱን ትምህርት አላማ ማስተዋወቅ | 5 | በጣም ከፍተኛ | 3.5 | ከፍተኛ |
| 3. | ተማሪዎች የመፃፍ ፍላጎት እንዲኖራቸዉ የቀደመ እዉቀታቸዉን በመቀስቀስና በማነሳሳት ወደ ፅሁፍ እነዲገቡ ማድረግ | 4 | ከፍተኛ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ |
| 4. | ተማሪዎች ለምን እነደሚጽፉና እንዴት መፃፍ እንዳለበት ተገቢ የሆነ ፍንጭ መስጠት | 4 | ከፍተኛ | 2.5 | ዝቅተኛ |
| 5. | ተማሪዎች ከርዕሱ ተነስተዉ የፅሁፉን ይዘት እነዲተነቢዩ ማድረግ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ | 3.5 | ከፍተኛ |
| 6. | በርዕሳቸዉ ላይ ቢጋር/አስተዋፅኦ | 4.5 | በጣም | 2.5 | ዝቅተኛ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | እነዲያዘጋጁ ማድረግ | | ከፍተኛ | | |
| 7. | የፅሁፉ ይዘት/ርዕስ ከተማሪዎች የክፍል ደረጃና የቀደመ እዉቀት ጋር አዛምዶ ማቅረብ | 5 | በጣም ከፍተኛ | 4 | ከፍተኛ |
| 8. | ተማሪዎች ለሚፅፉት ፅሁፍ የጊዜ ገደብ መስጠት | 5 | በጣም ከፍተኛ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ |
| | **II የፅሁፍ ጊዜ ትምህርት ተግባራት** | | | | |
| 9. | ተማሪዎች በቅድመ ፅህፈት ጊዜ ከተረዱት ሃሳብ በመነሳት በየግላቸዉ በቢጋር ዉስጥ መካተት ያለባቸዉን ጉዳዮች እንዲያሰላስሉ ማድረግ | 4 | ከፍተኛ | 3 | መካከለኛ |
| 10. | ተማሪዎች በግል ያመነጩትን ሃሳብ በጥንድ ካወያዩ በኋላ ቢጋር እንዲያዘጋጁ ማድረግ | 4 | ከፍተኛ | 3.5 | ከፍተኛ |
| 11. | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ረቂቅ ከሌላዉ ጥንድ ጋር ተወያይተዉ ሀሳብ ወይም አስተያየት እንዲለዋወጡበት ማድረግ | 3.5 | ከፍተኛ | 3.5 | ከፍተኛ |
| 12. | ከሌሎች ጥንድ ተማሪዎች ከተሰጣቸዉ አስተያየት በመነሳት ረቂቁን በድጋሚ እንዲፅፉ ማድረግ | 4 | ከፍተኛ | 3 | መካከለኛ |
| 13. | እንደየ ፅሁፉዓላማ የተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች እንዲጠቀሙ ማድረግ | 5 | በጣም ከፍተኛ | 3 | መካከለኛ |
| 14. | ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር እንዲያገናዝቡ ማድረግ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ | 4 | ከፍተኛ |
| 15. | ተማሪዎች የፃፉትን ፅሁፍ/ድርሰት በማየትና አስተያየት በመስጠት እንደገና አሻሽለዉ እንዲፅፉ ማድረግ | 4 | ከፍተኛ | 3.5 | ከፍተኛ |
| 16. | ሲፅፉ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይተዉ እንዲፅፉ ማድረግ | 4 | ከፍተኛ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 17. | ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት በድጋሚ በማየት ማበረታታትና ማድነቅ | 4 | ከፍተኛ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ |
| | **III የድህረ ፅህፈት ትምህርት ተግባራት** | | | | |
| 18. | ተማሪዎች የፃፉትን ፅሁፍ መሰረት በማድረግ ሀሳብ እንዲሰጡ (በፃፉት ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ እንዲወያዩና እንዲከራከሩ) ማድረግ | 5 | በጣም ከፍተኛ | 4 | ከፍተኛ |
| 19 | ተማሪዎች ሲፅፉ ያስቸገራቸዉን ቃላትና ሀረጋት ማስረዳት | 4.5 | በጣም ከፍተኛ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ |
| 20 | የፃፉትን ፅሁፍ ፍሬ ሀሳብ እነዲናገሩ ማድረግ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ | 4 | ከፍተኛ |
| 21 | መምህሯ/ሩ ፅህፈትን የተመለከቱ ይዘቶችን ከክፍል ዉጪ ሰርተዉና ተለማምደዉ እነዲመጡ ማገዝ | 4 | ከፍተኛ | 4 | ከፍተኛ |
| 22 | ፅሁፉ ካለቀ በኋላ ተማሪዎች ተጠይቀዉ ሲመልሱ ገንቢ የሆነ አስተያየት መስጠትና ተሳትፎዋቸዉን ማበረታታት | 5 | በጣመረ ከፍተኛ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ |
| 23 | ከፅሁፉ በፊትና በኋላ ተማሪዎች ፅሁፉን በግልፅ እነዲረዱ ግልፅ መመሪያዎችን መስጠት | 4.5 | በጣም ከፍተኛ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ |
| 24 | መምህሯ/ሩ ተማሪዎች በፃፉት ፅሁፍ ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን እንዴት ማዉጣት እንዳለባቸዉ ማለማመድ | 4.5 | በጣም ከፍተኛ | 4 | ከፍተኛ |
| 25 | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ፅሁፍ በንግግር ወይም በንባብ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያቀርቡ ዕድል መስጠት | 4.5 | በጣም ከፍተኛ | 4 | ከፍተኝ |

መረጃው እንደሚያመለክተው መምህራኑ የመፃፍ ክሒል ትምህርትን ሒደት ስኬታማ ለማድረግ የሚጠቀሙት አተገባበር ምን እንደሚመሥል ያሣያል:: ከምልከታውግምገማ ውጤት መረዳት የሚቻለው የክፍል ውስጥ አላባውያን የሆኑት መሠረት በማድረግ በግል ትምህርት ቤት የሚያሥተምሩ መምህራን መፃፍን ለመማር የሚያሥችሉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ውጤት ተኮር የመፃፍ ክሒል ትምህርት ማተኮር የመፃፍ ክሒል ማሥተማሪያ ሥልቶች ና ለሒደታዊ የመፃፍ ክሒል ትምህርት አተገባበር ማተኮር እና የመፃፍ ሥራዎችን ከፋፍሎ በመሥጠት መቆጣጠር ና ማሥተካከል አሥፈላጊ መሆኑን ያመለክታል።

በግልና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚያሥተምሩ መምህራን የመፃፍ ክሒል ትምህርት አተገባበር ደረጃቸው በጣም ከፍተኛ ባይሆንም መካከላቸው ግን ልዩነት እንዳለና በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የተሻለ አተገባበር እንዳላቸው አጠቃላይ የግምገማ ውጤቱ ያመለክታል።

በጥናቱ ተተኳሪ ከሆኑት መምህራን ጋር የሚያስተምሩበትን ዘዴ በተመለከተ ያለዉን አስተያየት ለመፈተሽ በክፍል ምልከታ የተገኘዉ መረጃ እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

በመጀመሪያ የዕለቱን ትምህርት በማስተዋወቅ ከሚሰጧቸው ርዕሶች ውስጥ እነርሱ የሚስማማቸውን እንዲመርጡ በማድረግ ወይም እነርሱ በመረጡት ርዕስ ዙሪያ በቂ ዕውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ እርስ በርሳቸው እንዲወያዩና እንዲረዳዱ ከርዕሶቻቸው ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጽሑፎችን እንዲያነቡ፣ ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ያደርጋሉ። በአጠቃላይ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅና ከክፍል ምልከታ የተገኘው ምላሽ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ ከሚሰጧቸው ርዕሶች ውስጥ ተማሪዎች የሚስማማቸውን እንዲመርጡ ወይም ራሳቸው በመረጡት ርዕስ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ እርስ በርሳቸው እዲወያዩ የሚያበረታቷቸው መሆናቸዉ ሞዴል ጽሑፎችንም በመስጠት ድርሰት እንዲጽፉ የሚያደርጓቸው መሆኑን ነው። በዚህም የተገኘው መረጃ የመምህራኑን የማስተማር ትኩረት በተማሪዎች በሚሰጧቸው ሞዴል በመመሥረት ድርሰት የሚጽፉ መሆናቸውን ነው። ከዚህ ውጤት የምንረዳው መምህራን የሚጠቀሙበት የማስተማሪያ ዘዴ ውጤታዊ የመጻፍ ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን ነው። ምክንያቱም በዚህ ዘዴ ተማሪዎቹ ድርሰት ሲጽፉ የነበረው ከራሳቸው ሀሳብ አፍልቀው የዐረፍተ ነገርንም ሆነ የአንቀጽ አጻጻፍ ስርዓትን ጠብቀው በራሳቸው የሚጽፉ ሳይሆን የተሰጣቸውን ሞዴል ጽሑፍ ወይም ድርሰት በመገልበጥና የአጻጻፍ

ቅርጹን በማጤን መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተማሪዎች ለሚጽፏቸው ድርሰቶች ምሳሌ ይሆናሉ ወይም ጥሩ ተጽፈዋል ተብለው የሚታሰቡ ጽሑፎችን በሞዴልነት አቅርቦ ሰዋሰዋዊ ህጎችንና አጻጻፋቸውን በማሳየት ተማሪዎች እነዚያኑ አስመስለው እንዲጽፉ የሚያለማምድ መሆኑን Nunan (1989፣36) እና Richards (1990፣106) አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች መምህራኑ በሚያቀርቡላቸው ሞዴል ጽሑፍ መሠረት ልምምድ ያደርጋሉ፡፡ መምህራኑም ሞዴሉን መሠረት እያደረጉ የሞዴሉን አገልግሎትና የአጻጻፍ ስልቶችን በመግለጽ ተማሪዎች የቀረበውን ሞዴል አንብበው ባህርያትን በመገምገም መጠነኛ በሆነ ልዩነት ተመሳሳይ ድርሰት እንዲጽፉ ያበረታታል፡፡ በዚህ ደረጃ የሚካሄዱ ውይይቶች ድርሰትን ለመጻፍ የሚያገለግሉ መር የጽህፈት ተግባራት መሆናቸውንም Raims (1983፣103) እና Pincas (1982፣102) ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ውጤት ተኮር አቀራረብ በቋንቋው ቅርጽ ላይ የሚያተኩር እንዲሁም የመጻፍ ልምምዱ ውጤት ምን ሊሆን እደሚችል በቅድሚያ በመምህሩ የሚወሰን በመሆኑ ከተማሪዎች ለሚቀርብ አዲስ ሃሳብ ትኩረት የማይሰጥ የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ዘዴው ተማሪዎች በሚጽፉት ርዕስ ላይ በራሳቸው ቋንቋና አገላለጽ ተጠቅመው ድርሰት የመጻፍ ልምምድ እንዲያደርጉ አያበረታታቸውም፡፡

ተማሪዎች እንደ የጽሑፉ ዓላማ የተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች እንዲጠቀሙ ማድረጋቸዉን በተመለከተ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህር የድርሰት ዓይነቶችን ካስተማሩ በኃላ እስኪ ይህንን ርዕስ ወስዳችሁ ተራኪ ድርሰት ወይም ስዕላዊ ድርሰትን በመጠቀም አንደ አንቀጽ ጻፉና አቅርቡ ስሉ አዘዋል፡፧በመንግስት ትምህርት ቤትም አንዷ መምህርት እንዲህ ከአራቱ የድርሰት ዓይነቶች አንዱን መርጣችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ በማለት የቤት ሥራ ሰጥተዋል ፡፡ስለዚህ የድርሰት ዓይነቶችን ተጠቅመዉ በመጻፍ ላይ ሁለቱም ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ ደረጃ ተስቷቸዋል፡፡

ተማሪዎች የጻፉትን ጽሑፍ ወይም ድርሰት ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር እንዲያገናዝቡ እና የሚያዉቁትን ነገር ወይም ርዕስ ወስደዉ እንዲጽፉ በመንግስት ትምህርት ቤት ዕድል አልተሰጣቸዉም ፡፡ምክንያቱም በመጽሐፉ ላይ ያለዉን ርዕስ ከዚያዉ መርጣችሁ ጻፉ በማለት ነበር መምህሩ ትዕዛዝ ያስተላለፉት ፡፡በግል ትምህርት ቤት ግን መምህሩ እንዲጽፉ ሲያደርጉ የነበረዉ ተማሪዎች ስለሚያዉቁት ነገር የፈለጉትን ርዕስ ወስደዉ አንቀጽ ወይም ድርሰት እንዲጽፉ ነበር የተደረገዉ፡፡ስለዚህ ከመንግስት ትምህርት ቤት የተሻለ አተገባበር ያለዉ የግል ትምህርት ቤት መሆኑ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል ተማሪዎች ስለጻፉት ርዕስ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይተዉ እንዲያቀርቡ ወይም በአንቀጽ ዉስጥ የአንቀጹ ፍሬ ሀሳብ ወይም ሀይለቃል የትኛዉ እንደሆነ የአንቀጽ ዝርዝር ሀሳቦችስ የትኞቹ እንደሆኑ ለይተዉ እንዲጽፉ ወይም እንዲያደርጉ ሲደረግ የነበረዉ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች ሲተገበር ነበር፡፡ በተጨማሪም በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የተጻፈዉን ድርሰት በማየት ወይም ደጋግሞ በማየት ማድነቅና ማበረታታቱ አለ፡፡ በዚያዉም አንጻር ደግሞ በመንግስት ትምህርት ቤት ዉስጥ ተማሪዎች ሲሳሳቱ ወይም መጻፍ ሲያቅታቸዉ ከማበረታታት ይልቅ ሚቆጡ መምህራን እንዳሉ ለማየት ተችሏል፡፡ እንደ አጠቃላይ ስናየዉ አተገባበራቸዉ ከመንግስት ትምህርት ቤቶች የበለጠ በግል ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ጥሩ አተገባበር ይታያል፡፡ ስለዚህ የግል ትምህርት ቤት ከፍተኛዉን ደረጃ ሲይዝ የመንግስት ትምህርት ቤት ግን መካከለኛዉን ደረጃ እንደሚይዝ ለማየት ተሞክሯል፡፡

ሌላዉ በመጻፍ ክህል ትምህርት የተግባር ጊዜ ክንዉንን በተመለከተ በመጀመሪያ መከናወን አለበት ተብሎ የሚታሰበዉ ተማሪዎች በቅድመ ተግባር ጊዜ ከተረዱት ሀሳብ በመነሳት በየግላቸዉ በቢጋራቸዉ ዉስጥ መካተት ስለሚኖርባቸዉ ርዕሰ ጉዳዮች እንዲያሰላስሉ ማስቻል ነዉ፡፡ይህ ደረጃ ተማሪዎቹ በሚጽፉት አንቀጽ ወይም ድርሰት ዉስጥ በርካታ ይዘቶችን እንዲያነሱ መነሻ ይሆናቸዋል፡፡ከዚህ አኳያ የተገኘዉ ዉጤት በግልም ሆነ በመንግስት ትምህርት ቤቶች ያተገባበር ደረጃዉ ምን እንደምመስል ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በሌላ አገላለጽ ተማሪዎቹ ስለሚጽፉት ርዕሰ ጉዳይ ሀሳብ እንዲያሰላስሉ መምህራኑ የሚያደርጓቸዉ ሁኔታዎች በግል ትምህርት ቤት ከፍተኛ ሲሆን በመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ መካከለኛ ደረጃ ላይ እደሚገኝ ያመለክታል፡፡ መምራን ተማሪዎቻቸዉን የመጀመሪያ ረቂቅ ከማስጻፋቸዉ አንጻር የተገኘ ዉጤት ሲታይ ከእስማማለሁ እስከ በጣም እስማማለሁ የተመዘገበ ነው፡፡ በሌሎቹ መለኪያዎች ማለትም ተማሪዎቹ ያዘጋጁትን ረቂቅ ከሌላዉ ጥንድ ጋር ተቀያይረዉ ሀሳብ ወይም አስተያየት እንዲለዋወጡ ከማስቻል ፤የጻፉትን ረቂቅ አሻሽለዉ ረቂቁን በድጋሚ እንዲጽፉ ከማድረግ እንዲሁም ያዘጋጁትን ጽሑፍ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ ከማቅረብ አንጻር የተገኙ ዉጤቶች ሲታዩ አተገባበራቸዉ በግል ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ ሲሆን በመንግስት ትምህርት ቤቶች ደግሞ ዝቅተኛ ደረጃን ይዘዋል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ከተግባቦታዊ አዉዶች ወደ ቅርጽ በመምጣት ሰዋሰዋዊ ሂደቶችን የሚያከናዉኑበት ደረጃ ነዉ፡፡ ተማሪዎች ከጻፏቸዉ አንቀጾች ወይም ድርሰቶች በመነሳት ከቃል፤ከሀረግ ፤ከዐ.ነገርና መሰል ከሆኑ ሰዋሰዋዊ ጉዳዮች አንጻር ልዩ ልዩ

ተግባራትን ያከናዉናሉ፡፡በመሆኑም በዙህ ደረጃ መምህሩ ተማሪዎቹን ቃል፤ሐረግ፤ዐ.ነገር ወዘተ እንዲያወጡበማድረግ ስለምንነቱ እንዲያብራሩና ተጨማሪ ምሳሌዎትን እንዲሰጡ ዕድል ሊሰጣቸዉ ይገባል፡፤ እነዚህ ከላይ የመምህሩን የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር በተመለከተ በተማሪዎችና በክፍል ምልከታው የተሰጡት አስተያየቶች የሚያመላክቱት ተማሪዎች የመምህሩን ትዕዛዝና መመሪያ በመከተል የመጻፍ ሥራውን የሚያከናውኑ መሆናቸውን ነው፡፡ በዚህ ተማሪዎቹ በመጻፍ ሂደት ላይ እያሉ ትኩረት የሚሰጡት መምህሩ የሚያስገነዝባቸውን የአጻጻፍ መመሪያ የጠበቀ ጉዳይ እንጂ የራሳቸውን ልምድ በመጠቀም ለመጻፍ እንዳልሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ መምህሩ ተማሪዎች ለመጻፍ በሚፈልጉበት በማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ ላይ አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅና በማቀናበር እንዲጽፉ ዕድል መስጠት ነበረበት፡፡ ስለዚህ በድርሰት ወይም በአንቀጽ መጻፍ ትምህርት ወቅት ተማሪዎች የመምህራንን ትዕዛዝና መመሪያ በመከተል አስፈላጊውንድርሰት እንዲጽፉ ማድረግ ሳይሆን የድርሰቱን ሥራ በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው እንዲሰሩ ማበረታታት ነው፡፡ Raims (1983፣144) በሂደት ተኮር የሚያስተምሩ መምህራን ክፍሉ ጥሩ ወይም ምቹ የመጻፊያ አውድ እዲሆን ማመቻቸትና ተማሪዎቻቸውን ማገዝ ነው፡፡ መምህራኑ በዚህ አተገባበር ያላቸውን ሚና ተማሪዎች በሚጽፏቸው ረቂቆች ወይም ድርሰቶች ላይ ሃሳብ ማመንጨት፣ ማቀድ፣ ማርቀቅና መከለስ እንዲችሉ በቂ ጊዜ መስጠት ነው፡፡ በተጨማሪም የመጻፍ ስልት የመፍጠር ሂደት እንዲሆንላቸው ተማሪዎቻቸውን ማገዝ ነው በማለት አስረድተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡ የተጠኚ መምህራን የቅደመ መጻፍ ትምህርት አተገባበር በክፍል ምልከታየተገኘዉ ዉጤት በቁጥርና በፐርሰንት**

| የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤት | የተጠኚ መምህራን ብዛት | የጥያቄ ብዛት | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በጣም ዝቅተኛ | | ዝቅተኛ | | መካከለኛ | | ከፍተኛ | | በጣም ከፍተኛ | |
| | | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| የግል | 1 | | - | - | - | - | 2 | 25 | 4 | 50 | 2 | 25 |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 8 | - | - | - | - | 2 | 25 | 3 | 37.5 | 3 | 37.5 |
| የመንግ | 1 | 8 | - | - | 2 | 25 | 2 | 25 | 2 | 25 | 2 | 25 |
| | 1 | 8 | - | - | 1 | 12.5 | 3 | 37.5 | 2 | 25 | 2 | 25 |

ከዚህ ሠንጠረዥ መረዳት የሚቻለው በክፍል ምልከታው የግል ትምህርት ቤት

የሚያስተምሩ መምህራን 4.625% በመንግሰት ትምህርት ቤት የሚያሰስተምሩ መምህራን ደግሞ3.6875% አማካይ ውጤት ያስመዝግቡ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡ በክፍል ምልከታ የተገኘው የግምገማ ውጤት የሚያሳየው የግል ትምህርት ቤት መምህራን የተሻለ የቅድመ መፃፍ ክሂል ትምህርት እንደሚተገብሩ ለማየትተችሏል ፡፡ ይህም የሚያሳየው ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ በፐርሰንት ተሰልቶ ተቀምጧል፡፡ ዉጤቱም የሚያሳየው በግልትምህርት ቤት የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር በመንግስት ትምህርት ቤት የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ጋር ልዩነት አሳይቷል፡፡ በዚህ መሰረት በግል ትምህርት ቤት የቅድመ መፃፍ ጊዜ አተገባበር የተሻለ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 4፡ የተጠኚ መምህራን የመጻፍ ጊዜ ትምህርት አተገባበር በክፍል ምልከታ የተገኘዉ ዉጤት በቁጥርና በፐርሰንት

| የተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤት | የተጠኚ መምህራን ብዛት | የጥያቄ ብዛት | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በጣም ዝቅተኛ | | ዝቅተኛ | | መካከለኛ | | ከፍተኛ | | በጣም ከፍተኛ | |
| | | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| የግል | 1 | 9 | - | - | - | - | 2 | 22.2 | 4 | 44.4 | 3 | 33.3 |
| | 1 | 9 | - | - | - | - | - | - | 5 | 55.5 | 4 | 44.4 |
| የመንግ | 1 | 9 | - | - | - | - | 3 | 33.3 | 4 | 44.4 | 2 | 22.2 |
| | 1 | 9 | - | - | - | - | 4 | 44.4 | 3 | 33.3 | 2 | 22.2 |

ከሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው የመፃፍ ጊዜ ትምህርት አተገባበርን ስናይ የግል ትምህረት ቤት 4.33% ሲሆን መንግሰት ትምህርት ቤት ደግሞ 3.61% መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ በመፃፍ ጊዜ የተሻለ አተገባበር የሚታየው በግል ትምህርት ቤት መሆኑን የተመዘገበው መረጃ ያሳያል፡፡ በዚህም መሰረት በምልከታ የተገኘዉን ዉጤት ወደ ፐርሰንት በመቀየር ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡እንግዲህ በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘዉ ዉጤት የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን

የመጻፍ ጊዜ ትምህርት አተገባበር ከግል ትምህርት ቤት መምህራን የመጻፍ ጊዜ ትምህርት አተገባበር አንሶ በመገኘቱ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡በዚህም መሰረት የግል ትምህርት ቤት የተሻለ አተገባበር እንዳላቸው ከውጤቱ መረዳት ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 5፡ የተጠኚ መምህራን የድህረ መጻፍ ትምህርት አተገባበር በክፍል ምልከታ የተገኘዉ ዉጤት በቁጥርና በፐርሰንት**

| ተጠኚ መምህራን ትምህርት ቤት | የተጠኚ መምህራን ብዛት | የጥያቄ ብዛት | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በጣም ዝቅተኛ | | ዝቅተኛ | | መካከለኛ | | ከፍተኛ | | በጣም ከፍተኛ | |
| | | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| የግል | 1 | 8 | - | - | - | - | 2 | 25 | 3 | 37.5 | 3 | 37.5 |
| | 1 | 8 | - | - | - | - | 2 | 25 | 4 | 50 | 2 | 25 |
| የመንግ | 1 | 8 | - | - | 1 | | 2 | 25 | 3 | 37.5 | 2 | 25 |
| | 1 | 8 | - | - | 1 | | 3 | 37.5 | 3 | 37.5 | 1 | 12.5 |

ከዚህ ሠንጠረዥ መረዳት የሚቻለው በድህረ መፃፍ ተግባር ላይ በግልና በመንግሰት ትምህርት ቤት የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን 4.595% ሲሆን በመንግሰት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ደግሞ 4.25% እንደሆነ አማካይ ውጤቱ ያመለክታል፡፡ ዉጤቱምየሚያመለክተው በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያሰስተምሩ መምህራን ልዩነት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በዚህ መሰረትም በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የድህረ መጻፍ ትምህርት አተገባበር በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ የድህረ መጻፍ ትምህርት አተገባበር የተሻለ የድህረ መፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር እንዳላቸው መረጃው ያመለክታል፡

### 4.1.3. ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ጥናት ውስጥ የጽሑፍ መጠይቅ በሁለተኛነት የተመረጠው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነው፡፡ መጠይቁ የተዘጋጀውም ለተማሪዎች ነው፡፡ መጠይቁም መምህሩ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ድርሰት የሚያጽፉበትን አተገባበር በመመርመር በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከናወኑትን ተግባራት ለማወቅ እንዲሞሉት የቀረበ ነው፡፡ ከመጠይቁ የተገኘው መረጃ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

**የተማሪዎችን ዳራዊ ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎች ትንተና**

በደረጃው የሚማሩ ተማሪዎችን ዳራ ተከትሎ ማስተማር ለውጤታማነት አስፈላጊ ነው፡፡ በክፍል አንድ ለተማሪዎች የቀረቡ መጠይቆችን የተማሪዎችን ዳራዊ ሁኔታ ለማወቅ የሚያስችሉ ነበሩ፡፡ መጠይቆቹም በትክክል ሞልተው ከመለሱት 60 ተማሪዎች የተገኘው መረጃ የሚከተለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሠንጠረዥ 6፡ የጽሑፍ መጠይቅ የሞሉ ተማሪዎች ዳራዊ መግለጫ

| ትምህርት ቤት | ፆታ | ብዛት | አፍ መፍቻ ቋንቋ |
|---|---|---|---|
| የግል | ወ | 14 | አማርኛ/አፋን ኦሮሞ |
| | ሴ | 16 | አማርኛ/አፋን ኦሮሞ |
| | ድ | 30 | |
| የመንግስት | ወ | 13 | አማርኛ/አፋን ኦሮሞ |
| | ሴ | 17 | አማርኛ/አፋን ኦሮሞ |
| | ድ | 30 | |

ከዚህ በላይ ከቀረበው መረጃ እንደሚታየው የግል ትምህርት ቤቶች 14 ወንዶችና 16 ሴት ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተው የመለሱ ሲሆን፣ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ደግሞ 13 ወንዶችና 17 ሴት ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቁን በመሙላት የተሳተፉ ናቸው፡፡ በመረጃው መሠረትም በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የጽሑፍ መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረጉት ተማሪዎች ከፆታ፣ ከዕድሜና ከአፍ መፍቻ ቋንቋ አኳያ ተቀራራቢነት የሚታይባቸውና በክፍሉ ዉስጥ ደረጃ ያላቸዉ ተማሪዎች በመሆኑ በጥናቱ ውጤት ላይ የሚያሳዩት አሉታዊ ተፅዕኖ እንደማይኖር መገመት ይቻላል

**ሠንጠረዥ 7፡በቅድመ መፃፍ ጊዜከውጤታዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር አኳያ ለተማሪዎች ከቀረቡ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ትንተና**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም | መወሰን ያስአግረኛል | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ |
| 1 | የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ያስተዋዉቃሉ | የግል | - | 3 | - | 9 | 18 |
| | | የመንግ | - | 8 | - | 12 | 10 |
| 2 | የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ያስተዋዉቃሉ | የግል | 4 | 2 | - | 10 | 14 |
| | | የመንግ | 9 | 10 | - | 8 | 3 |
| 3 | ተማሪዎች የመጻፍ ፍላጎት እንዲኖራቸዉ የቀደመ እዉቀታቸዉን በመቀስቀስና በማነሳሳት ወደ ጽሑፍ እንዲገቡ ያደርጋሉ | የግል | 2 | 8 | - | 8 | 12 |
| | | የመንግ | 4 | 12 | - | 9 | 5 |
| 4 | ተማሪዎች ለምን እንደሚጽፉና እንዴት መጻፍ እንዳለበት ተገቢ የሆነ ፍንጭ ይሰጣሉ | የግል | - | 5 | - | 10 | 15 |
| | | የመንግ | 5 | 10 | - | 7 | 8 |
| 5 | ተማሪዎች ከርዕሱ ተነስተዉ የጽሑፉን ይዘት እንዲተነቢዩ ያደርጋሉ | የግል | 4 | 8 | - | 8 | 10 |
| | | የመንግ | 6 | 12 | - | 8 | 4 |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም | መወሰን ያስቸግረኛል | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ |
| 6 | በርዕሳቸዉ ላይ ቢጋር ወይም አስተዋጽኦ እንዲያዘጋጁ ያደርጋሉ | የግል | - | 4 | - | 10 | 16 |
| | | የመንግ | - | 10 | - | 9 | 11 |
| 7 | የጽሑፉ ይዘት ወይም ርዕስ ከተማሪዎች የክፍል ደረጃና የቀደመ እዉቀት ጋር አዛምደዉ ያቀርባሉ | የግል | 2 | 6 | - | 10 | 12 |
| | | የመንግ | 4 | 7 | - | 9 | 10 |
| 8 | ተማሪዎች ለሚጽፉት ጽሑፍ የጊዜ ገደብ ይሰጣሉ | የግል | 3 | 5 | - | 9 | 13 |
| | | የመንግ | 4 | 6 | - | 10 | 10 |

**ከውጤታዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር አንጻር መምህሩ የሚጠቀምበትን የማስተማሪያ ዘዴ ለማወቅ በቀረቡ መጠይቆች የተሰጡ ምላሾችን የሚያሳይ**

ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው መምህራን የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ለተማሪዎች ስለማስተዋወቃቸው ለቀረበው ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 27 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 22 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 3 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 8 የሚሆኑት ተማሪዎች ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

እንዲሁም መምህራን የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ለተማሪዎች ስለማስተዋወቃቸው ለቀረበው ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 24 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 11 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 6 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 19 የሚሆኑት ተማሪዎች ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ተማሪዎች የመጻፍ ፍላጎት እንዲኖራቸዉ የቀደመ እዉቀታቸዉን በመቀስቀስና በማነሳሳት ወደ ጽሑፍ እንዲገቡ በማድረግ ረገድ ከግል ትምህርት ቤት 28 ከመንግስት ትምህርት ቤት14 የሚሆኑት ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 10 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 16 የሚሆኑት ተማሪዎች አፍራሽ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ተማሪዎች ለምን እንደሚጽፉና እንዴት መጻፍ እንዳለበት ተገቢ የሆነ ፍንጭ መስጠት በሚለዉ ላይ ከግል ትምህርት ቤት25 ከመንግስት ትምህርት ቤት 15 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 5 ከመንግስት ትምህርት ደግሞ 15 የሚሆኑት አፍራሽ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከሠንጠረዡእንደሚንመለከተዉ ተማሪዎች ከርዕሱ ተነስተዉ የጽሑፉን ይዘት እንዲገምቱ በማድረግ ላይ ከግል ትምህርት ቤት 18ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 12የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 12 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 18የሚሆኑት ተማሪዎች አፍራሽ መልስ ሰጥተዋል ፡፡

የማስተማር ዘዴ በራሱ ውጤት ባይሆንም ውጤት ለማስገኘት የሚያስችል በመሆኑ መምህራን ዘዴውን ምንነት አውቀው ለሚያስተምሩት ክሂል መዳበር በሚጠቅም መልኩ ቢጠቀሙ የተፈለገውን ባህርይ ማምጣት እንደሚቻል Larson Freeman (1986:1) ይጠቁማሉ፡፡

## ሠንጠረዥ 8፡ በመፃፍ ጊዜ ከሂደታዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር አኳያ ለተማሪዎች ከቀረቡ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ትንተና

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም | መወሰን ያስቸግረኛል | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ |
| 9 | ተማሪዎች በቅድመ ጽፈት ጊዜ ከተረዱት ሀሳብ በመነሳት በየግላቸዉ በቢጋር ዉስጥ መካተት ያለባቸዉን ጉዳዮች እንዲያሰላስሉ ማድረግ | የግል | 3 | 6 | - | 10 | 11 |
| | | የመንግ | 5 | 10 | - | 11 | 4 |
| 10 | ተማሪዎች በግል ያመነጩትን ሃሳብ በጥንድ ካወያዩ በኃላ ቢጋር እንዲያዘጋጁ ያደርጋሉ፡፧ | የግል | 2 | 7 | - | 9 | 12 |
| | | የመንግ | 6 | 9 | - | 7 | 8 |
| 11 | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ረቂቅ ከሌላዉ ጥንድ ጋር ተወያይተዉ ሀሳብ ወይም አስተያየት እንዲለዋወጡበት ያደርጋሉ፡፡ | የግል | 7<br>- | 10 | - | 10 | 3 |
| | | የመንግ | 11 | 12 | - | 5 | 2 |
| 12 | ከሌሎች ጥንድ ተማሪዎች ከተሰጣቸዉ አስተያየት በመነሳትረቂቁን በድጋሚ እንዲጽፉ ያደርጋሉ፡፡ | የግል | 5 | 7 | - | 10 | 6 |
| | | የመንግ | 8 | 8 | - | 12 | 2 |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም | መወሰን ያስቸግረኛል | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ |
| 13 | እንደየጽሑፉ ዓላማ የተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች እንዲጠቀሙ ያደርጋሉ፡፡ | የግል | 5 | 7 | - | 10 | 8 |
| | | የመንግ | 7 | 9 | - | 11 | 3 |
| 14 | ተማሪዎች የጻፉትን ድርሰት ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር እንዲያገናዝቡ ያደርጋሉ፡፡ | የግል | 3 | 7 | - | 12 | 8 |
| | | የመንግ | 5 | 5 | - | 12 | 8 |
| 15 | ተማሪዎች የጻፉትን ጽሑፍ/ድርሰት ማየትና አስተያየት በመስጠት እንደገና አሻሽለዉ እንዲጽፉ ያደርጋሉ፡፡ | የግል | 4 | 6 | - | 13 | 9 |
| | | የመንግ | 5 | 8 | - | 10 | 7 |
| 16 | ሲጽፉ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይተዉ እንዲጽፉ ያደርጋሉ፡፡ | የግል | 7 | 8 | - | 10 | 5 |
| | | የመንግ | 8 | 9 | - | 12 | 5 |
| 17 | ተማሪዎች የጻፉትን ድርሰት በድጋሚ በማየት ያበረታታሉ/ያደንቃሉ፡፡ | የግል | 1 | 2 | - | 19 | 8 |
| | | የመንግ | 2 | 5 | - | 20 | 3 |

**ከሂደታዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር አንጻር መምህሩ የሚጠቀምበትን የማስተማሪያ ዘዴ ለማወቅ በቀረቡ መጠይቆች የተሰጡ ምላሾችን የሚያሳይ**

ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው መምህራን ተማሪዎች ቢጋር ወይም አስተዋፅኦ እንዲያዘጋጁ ስለማድረጋቸው ለቀረበው ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 21 ፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 15 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ፣ ከግል ትምህርት ቤት 9፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 15 የሚሆኑት ተማሪዎች ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው መምህራን ተማሪዎች መጻፍን በማርቀቅ ሂደት እንዲለማመዱ ስለማድረጋቸው ለቀረበው ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 13፤ ከመንግስት

ትምህርት ቤት ደግሞ 7 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ፣ ከግል ትምህርት ቤት 17፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 23 የሚሆኑት ተማሪዎች ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

እንዲሁም መምህራን ተማሪዎች ድርሰት ወይም አንቀጽ እንዲጽፉ በቂ ጊዜ ስለመስጠታቸው ለቀረበው ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት ፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ፣ ከግል ትምህርት ቤት አንድ፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ አራት የሚሆኑት ተማሪዎች ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው በግልም ይሁን በመንግስት ትምህርት ቤት ቢጋር ወይም አስተዋፅኦ እንያዘጋጁ፣ መጻፍን በማርቀቅ ሂደት ድርሰት ወይም አንቀጽ እንዲጽፉ በቂ ጊዜ ከመስጠት አኳያ ተመሳሳይነት የሚታይባቸው መሆኑን ከተማሪዎች መጠይቅና ከክፍል ምልከታው የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ከላይ የቀረበዉ ሰንጠረዠ የሚያሰየዉ ተማሪዎች በቅድመ ጽህፈት ጊዜ ከተረዱት ሀሳብ በመነሳት በየግላቸዉ በቢጋር ዉስጥ መካተት ያለባቸዉን ጉዳዮች እንዲያሰላስሉ ያደርጋሉ በሚል ለቀረበዉ ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 21 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 15 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ስሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 9 ከመንግስት ትምህርት ቤት 15 የሚሆኑት ተማሪዎች አፍራሽ መልስ ሰጥተዋል፡፡እንዲሁም ተማሪዎች በግል ያመነጨትን ሀሳብ በትንድ ካወያዩ በኃላ ቢጋር እንዲያዘጋጁ ያደርጋሉ ለሚለዉ ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 21 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 15 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 9 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 15 የሚሆኑት ተማሪዎች ሳይስማሙ ቀርተዋል፡፡

ሌላዉ ተማሪዎች ያዘጋጁትን ረቂቅ ከለላዉ ጥንድ ጋር ተወያይተዉ ሀሳብ ወይም አስተያየት እንዲለዋወጡበት ስለማድረጋቸዉ ለተጠየቀዉ ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 13 ከመንግስት ትምህርት ቤት 7 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 17 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 23 የሚሆኑት ተማሪዎች ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም ከሌሎች ጥንድ ተማሪዎች ከተሰጣቸዉ አስተያየት በመነሳት ረቂቁን በድጋሚ እንዲጽፉ ያደርጋሉ?ለሚለዉ ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 16 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 14 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 12 ከመንግስት ትምህርት ቤት 16 የሚሆኑት ተማሪዎች አፍራሽ መልስ ሰጥተዋል፡፡እንደየጽሑፉ

ዓላማ የተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች እንዲጠቀሙ ያደርጋሉ?ለሚለዉ ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 18 ከመንግስት ትምህርት ቤት 14 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 12 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 16 የሚሆኑት ተማሪዎች አፍራሽ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ሌላዉ ተማሪዎች የጻፉትን ድርሰት ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር እንዲያገናዝቡ ያደርጋሉ? ለሚለዉ ከግል ትምህርት ቤት 20 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 20 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 10 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 10 የሚሆኑት ተማሪዎች አፍራሽመልስ ሰጥተዋል፡፤እንዲሁም ተማሪዎች የጻፉትን ጽሑፍ ወይም ድርሰት በማየትና አስተያየት በመስጠት እንደገና አሻሽለዉ እንዲጽፉ ያደርጋሉ?ለሚለዉ ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 21 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 17 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 10 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 13 የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ ሳይስማሙ ቀርተዋል፡፡ ተማሪዎች ሲጽፉ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይተዉ እንዲጽፉ ያደርጋሉ?ተብሎ ለቀረበዉ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 15 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ17 የሚሆኑት በጥያቄዉ አለመስማማትን አሳይተዋል፡፡ በተጨማሪም የጻፉትን ድርሰት በድጋሚ በማየት ያበረታታሉ የጻፉትን ድርሰት በድጋሚ በማየት ያበረታታሉ?ያደንቃሉ?ሲባሉ ከግል ትምህርት ቤት 27 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 23 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል ትምህርት ቤት 3 ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 7 የሚሆኑት ተማሪዎች አፍራሽ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው መምህራን ሁሉም ተማሪዎች መጻፍ አለመጻቸውን በመከታተል ስለመቆጣጠራቸው ለቀረበው ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት ሃያ አራት ፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ ሃያ የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ፣ ከግል ትምህርት ቤት ስድስት፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ አስር የሚሆኑት ተማሪዎች ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

እንዲሁም መምህራን ተማሪዎች የጻፉትን ድርሰት እርስ በርሳቸው እንዲተራረሙ ስለማድረጋቸው ለቀረበው ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት ሃያ ሦስት ፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ ሃያ የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ፣ ከግል ትምህርት ቤት ሰባት ፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ አስር የሚሆኑት ተማሪዎች ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በሰንጠረዡ በቀረበው መረጃ መሠረት ተማሪዎች መጻፍ አለመጻፋቸውን ከመከታተልና የጻፉትን ድርሰት እርስ በርሳቸው እንዲተራረሙ ከማድረግ አኳያ የተሻለ አተገባበር የሚታየው በግል ትምህርት ቤት መሆኑን ከተማሪዎች መጠይቅና ከክፍል ምልከታ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ተማሪዎች በርዕሶቻቸው ዙሪያ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ ተዛማጅነት ያላቸውን ጽሑፎች እንዲያነቡ፣ የሚያውቁ ሰዎችን እንዲጠይቁ የሚያደርግ መሆኑንና የተማሪዎችን በመጻፍ ሂደት ላይ እያሉ የሚፈልጉትን ድጋፍ የሚያደርግላቸው መሆኑን ቢገልጽም በመንግስት ትምህርት ቤት ይህ አተገባበር ዝቅተኛ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከላይ ከተማሪዎችና ከክፍል ምልከታ የተገኙ ምላሾች የሚያመለክቱት መምህራን ተማሪዎች መጻፍ አለመጻፋቸውን እና እርስ በርሳቸው እንዲወያዩ በመረጡት ርዕስ ድርሰት መጻፍ ከመጀመራቸው በፊት ሃሳብ በማመንጨት፣ በማደራጀት፣ በማርቀቅና፣ በመከለስና በማረም ሂደት አልፈው እንዲጽፉ የሚያስተምራቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህም ሄጅ (1991፣11) መምህራን ተማሪዎቻቸው እንዲያቅዱ፣ እንዲያረቁና እንዲከልሱ የሚያስችላቸውን የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ክንውንን በመፍጠር የክፍል ውስጥ ጊዜን ለመጻፍ ተግባራት መገልገል አለባቸው በማለት ይገልጻሉ፡፡ መምህራን ተማሪዎችን ያለምንም ተፅዕኖ ነጻ ሆነው በራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ በሚፈልጉት መንገድ እንዲጽፉ በማድረግ የመጻፍ ስልታቸውን መጠበቅ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎችን በማበረታታት፣ መንገድ በማሳየት፣ ከተማሪዎች ጋር አብሮ በመተባበር የማገዝ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንዲሁም የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ የመግባባትና የመተማመን መንፈስ የሰፈነበት እንዲሆን በማድረግ የተማሪዎችን የመጻፍ ስልት ለመጠበቅ የሚያስችል የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር መጠቀም ይገባቸዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 9፡ በድህረ መፃፍ ጊዜ ከሂደታዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር አኳያ ለተማሪዎች ከቀረቡ መጠይቆችየተገኙ መረጃዎች ትንተና**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም | መወሰን ያስቸግረኛል | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ |
| 18 | ተማሪዎች የጻፉትን ጽሑፍ መሰረት በማድረግ ሀሳብ እንዲሰጡ (በጻፉት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ እንዲወያዩና እንዲከራከሩ) ያደርጋሉ ፡፡ | የግል | - | 7 | - | 15 | 8 |
| | | የመንግ | 3 | 8 | - | 10 | 9 |
| 19 | ተማሪዎች ሲጽፉ ያስቸገራቸዉን ቃላትና ዐረጋት ያስረዳሉ፡፡ | የግል | 2 | 5 | - | 13 | 10 |
| | | የመንግ | 5 | 7 | - | 9 | 9 |
| 20 | የጻፉትን ጽሑፍ ፍሬ ሀሳብእንዲናገሩ ጣደርጋሉ፡፡ | የግል | - | 6 | - | 19 | 5 |
| | | የመንግ | - | 9 | - | 11 | 10 |
| 21 | መምህሯ/ሩ ጽሀፈትን የተመለከቱ ይዘቶችን ከክፍል ዉጪ ሰርተዉና ተለማምደዉ እንዲመጡ ያግዛሉ፡፡ | የግል | 2 | 5 | - | 16 | 7 |
| | | የመንግ | 4 | 7 | - | 10 | 9 |
| 22 | ጽሑፉ ካለቀ በኃላ ተማሪዎች ተጠይቀዉ ሲመልሱ ገንቢ የሆነ አስተያየት በመስጠት ተሳትፎዋቸዉን ያበረታታሉ | የግል | - | 6 | - | 10 | 14 |
| | | የመንግ | - | 5 | - | 15 | 10 |
| 23 | ከጽሑፉ በፊትና በኃላ ተማሪዎች ጽሑፉን በግልጽ እንዲረዱ ግልጽ መመሪያዎችን ይሰጣሉ፡፡ | የግል | 2 | 7 | - | 11 | 10 |
| | | የመንግ | 3 | 9 | - | 10 | 8 |
| 24 | መምህረሯ/ሩ ተማሪዎች በጻፉት ጽሑፍ ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን | የግል | 5 | 10 | - | 9 | 6 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | እንዴት ማዉጣት እንዳለባቸዉ ያስማምዳሉ፡፡ | የመን ግ | 8 | 12 | - | 8 | 2 |
| 25 | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ጽሑፍ በንግግር ወይም በንባበ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እዲያቀርቡ ዕድል መስጠት | የግል | 5 | 8 | - | 10 | 7 |
| | | የመን ግ | 7 | 9 | - | 9 | 7 |

**ከሂደታዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር አንጻር መምህሩ የሚጠቀምበትን የማስተማሪያ ዘዴ ለማወቅ በቀረቡ መጠይቆች የተሰጡ ምላሾችን የሚያሳይ**

ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው መምህራን በተማሪዎች ጽሑፋዊ ሥራዎች ላይ አስተያየት በመስጠት ስለማበረታታታቸው ለቀረበው ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 24 ፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 25 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ፣ ከግል ትምህርት ቤት 6፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 5 የሚሆኑት ተማሪዎች ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

መምህራን ተማሪዎች በተሰጣቸው አስተያየት መሠረት እንደገና አሻሽለው እንዲጽፉ ስለማድረጋቸው ለቀረበው ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 23 ፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 19 የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ፣ ከግል ትምህርት ቤት 7፤ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 11 የሚሆኑት ተማሪዎች ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ስለዚህ መምህራን በተማሪዎች ጽሑፋዊ ሥራዎች ላይ አስተያየት በመስጠት ማበረታታታቸውና በተሰጣቸው አስተያየት መሠረት እንደገና አሻሽለው እንዲጽፉ ከማድረግ አኳያ የተሻለ አተገባበር የሚታየው በግል ትምህርት ቤት መሆኑን ከተማሪዎች መጠይቅና ከክፍል ምልከታ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

የተሻለ ጽሑፍ የሚጽፉ ተማሪዎች የሚገኙት በግል ትምህርት ቤት ሲሆን ይህም የሆነበት ምክንያት ተማሪዎቹ መምህሩ ድርሰታቸውን አርሞ ይሰጣቸው የነበረው የእርማት አስተያየት ማስተካከል የሚገባቸውን አስተካክለው እንዲጽፉና ሌሎች ሙከራዎችንም እንዲያደርጉ ድጋፍ እንዳደረጉላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ በመንግስት ትምህርት ቤት ግን ድርሰት ከማጻፍና

ከማስነበብ ውጭ ሌላ ተግባር እንደማይከናወን በተማሪዎቹ የጽኹሑፍ መጠይቅና በክፍል ምልከታ ለማየት ተችሏል፡፡ ለተማሪዎች ከሚሰጡ ምጋቤ ምላሽ ገጽታዎች የአሉታዊ አስተያየቶች መብዛት ተማሪዎች ለመጻፍ ያላቸውን ተነሳሽነት ከመቀነሱም በላይ ጥሩ ድርሰትንም እንዳይጽፉ የሚያደርጋቸው መሆኑን አንከር (2000) አስረድተዋል፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ የሚደረግ እርማት ደግሞ ተማሪዎችን ለጭንቀት የሚዳርግ፣ የተማሪዎችን የመጻፍ ስሜት የሚያቀዘቅዝና ተማሪዎቹ ከእርማቱ ለመጠቀም ፍላጎት እንዳይኖራቸው እንደሚያደርግ መገመት ይቻላል፡፡ ተማሪዎች በሚጽፉት ድርሰት ከመምህራቸውና ከጓደኞቻቸው የሚያስፈልጋቸውን ምላሽ ሲያገኙ በድርሰቶቻቸው ጥራት ላይ መሻሻል ሊመጣ ይችላል፡፡ እንዲሁም የተማሪዎችን ተግባራዊ ተሳትፎ የሚጠይቅ ከመምህራቸውና ከጓደኞቻቸው ምላሽ ማግኘት የሚችሉበት አመች ሁኔታ ቢኖር ተማሪዎች ለድርሰት ትምህርቱ ተነሳሽ ሆነው የተዋጣለት ድርሰት መጻፍ ይችሉ ነበር፡፡ ይህንን አስመልክተው ሂሉክስ (1986፣240) ከመምህር ድጋፍ በተጨማሪ የጓደኛ ድጋፍ ቢጨመር በተናጠል ከሚደረገው እርማት ይበልጥ ውጤታማ ለሆነና ተማሪዎችንም ለተሻለ ሥራ እንደሚያነሳሳ ገልጸዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 10 :የቅድመ መፃፍ ጊዜ የተማሪዎች ግምገማ  በፐርሰንት**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | `` | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ |
| 1 | የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ያስተዋዉቃሉ | የግል | - | 5 | 15 | 30 |
| | | የመንግ | - | 13.33 | 20 | 16.67 |
| 2 | የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ያስተዋዉቃሉ | የግል | 6.67 | 3.33 | 16.67 | 23.33 |
| | | የመንግ | 15 | 16.67 | 13.33 | 5 |
| 3 | ተማሪዎች የመጻፍ ፍላጎት እንዲኖራቸዉ የቀደመ ዕዉቀታቸዉን በመቀስቀስና በማነሳሳት ወደ ጽሑፍ እንደገቡ ያደርጋሉ | የግል | 3.33 | 13.33 | 13.33 | 20 |
| | | የመንግ | 6.67 | 20 | 15 | 8.33 |
| 4 | 3.33ተማሪዎች ለምን እንደሚጽፉና እንዴት መጻፍ | የግል | - | 8.33 | 16.67 | 25 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | እንዳለበት ተገቢ የሆነ ፍንጭ ይሰጣሉ | የመንግ | 8.33 | 16.67 | 11.67 | 13.33 |
| 5 | ተማሪዎች ከርዕሱ ተነስተዉ የጽሑፉን ይዘት እንዲተነቢዩ ያደርጋሉ | የግል | 6.67 | 13.33 | 13.33 | 16.67 |
| | | የመንግ | 10 | 25 | 13.33 | 6.67 |
| 6 | በርዕሳቸዉ ላይቢ.ጋር/አስተዋጽኦ እንዲያዘጋጁ ያደርጋሉ | የግል | - | 6.67 | 16.67 | 26.67 |
| | | የመንግ | - | 16.67 | 15 | 18.33 |
| 7 | የጽሑፍ ይዘት/ርዕስ ከተማሪዎች የክፍል ደረጃና የቀደመ እዉቀት ጋር አዛምደዉ ያቀርባሉ | የግል | 3.33 | 10 | 16.67 | 20 |
| | | የመንግ | 6.67 | 11.67 | 15 | 16.67 |
| 8 | ተማሪዎች ለሚጽፉት ጽሑፍ የጊዜ ገደብ ይሰጣሉ | የግል | 5 | 8.33 | 15 | 16.67 |
| | | የመንግ | 6.67 | 10 | 15 | 21.67 |

የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ማስተዋወቅን በተመለከተ ከግል ትምህርት ቤት 45%ቱ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 36.67%ቱ እስማማለሁና በጣም እስማማለሁ ሲሉ ከግል ትምህርት ቤት 5% ከመንግስት ትምህርት ቤት 13.33% የሚሆኑት አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ማስተዋወቅ ለሚለዉ ከግል 40% ከመንግስት ትምህርት ቤት 18.33% እስማማለሁና በጣም እስማማለሁ ሲሉ ከግል ትምህርት ቤት 10% ከመንግስትትምህርት ቤት 31% የሚሆኑት አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ተማሪዎችን የመጻፍ ፍላጎት መቀስቀስን ስናይ ከግል ትምህርት ቤት 33.33% ከመንግስት ትምህርት ቤት 23.33% የሚሆኑት ሲስማሙ ከግል ትምህርት ቤት 16.66 ከመንግስት ትምህርት ቤት 26.67% የሚሆኑት ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡ለተማሪዎች ስለሚጽፉት ነገር ተገቢ ፍንጭ መስጠት ሲናይ ከግል ትምህርት ቤት 33.33% ከመንግስት ትምህርት ቤት 23.33% ሲስማሙ ከግል ትምህርት ቤት 8.33 ከመንንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 25% ሳይስማሙ ቀርተዋል፡፡

ሌላዉ ተማሪዎች ይዘቱን ይተነቢያሉ ለሚለዉ ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 29.97% ከመንግስት ትምህርት ቤት 19.67%ሲስማሙ ከግል 20% ከመንግስት 25% በጥያቄዉ ሳይስማሙ ቀርተዋል፡፡ቢ.ጋር እንዲያዘጋጁ ማድረግን በተመለከተ ከግል 43.34% ከመንግስት 33.33% ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል 6.67% ከመንግስት 16.67% የሚሆኑት

አለመስማማታቸዉን ገልጸዋላ፡፡ሌላዉ የጽሑፉን ይዘት ከተማሪዎች የክፍል ደረጃ ጋርአዛምዶ ማቅረብን በተመለከተ ከግል 36.67% ከመንግስት 31.67%የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ ከግል 13.33% ከመንግስት 18.34% የሚሆኑት በጥያቄዉ ሳይስማሙ ቀርተዋል፡፡ተማሪዎች ለሚጽፉት ጽሑፍ የጊዜ ገደብን መስጠትን በተመለከተ ከግል ትምህርት ቤት 36.67% ከመንግስት ትምህርት ቤት 33.34% የሚሆኑት መስማማታቸዉን ሲገልጹ ከግል 13.33% ከመንግስት 16.67% የሚሆኑት አፍራሽ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 11፡በመጻፍ ጊዜ ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ግምገማ በፐርሰንት**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ |
| 9 | ተማሪዎች በቅድመ ጽህፈት ጊዜ ከተረዱት ሀሳብ በመነሳት በየግላቸዉ በቢጋር ዉስጥ መካተት ያለባቸዉን ጉዳዮች እንዲያሰላስሉ ያደርጋሉ | የግል | 5 | 10 | 16.67 | 18.33 |
| | | የመንግ | 8.33 | 16.67 | 18.33 | 6.67 |
| 10 | ተማሪዎች በግል ያመነጩትን ሀሳብ በጥንድ ካወያዩ በኃላ ቢጋር እንዲያዘጋጁ ያደርጋሉ | የግል | 3.33 | 11.67 | 15 | 13.33 |
| | | የመንግ | 10 | 15 | 11.67 | 5 |
| 11 | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ረቂቅ ከሌላዉ ጥንድ ጋር ተወያይተዉ ሀሳብ ወይም አስተያየት እንዲለዋወጡበት ያደርጋሉ | የግል | 11.67 | 16.67 | 16.67 | 5 |
| | | የመንግ | 18.33 | 20 | 8.33 | 3.33 |
| 12 | ከሌሎች ጥንድ ተማሪዎች ከተሰጣቸዉ አስተያየት በመነሳት ረቂቁን በድጋሚ እንዲጽፉ ያደርጋሉ | የግል | 8.33 | 11.67 | 11.67 | 10 |
| | | የመንግ | 13.33 | 13.33 | 20 | 3.33 |
| 13 | እንደየጽሑፉ ዓላማ የተለያዩ ዓይነቶች እንዲጠቀሙ ያደርጋሉ | የግል | 8.33 | 11.67 | 16.67 | 13.33 |
| | | የመንግ | 11.67 | 15 | 18.33 | 5 |
| 14 | ተማሪዎች የጻፉትን ድርሰት ከሕይወት ልምዳቸዉ | የግል | 5 | 11.67 | 20 | 13.33 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ጋር እንዲያገናዝቡ ያደርጋሉ | የመንግ | 8.33 | 8.33 | 20 | 13.33 |
| 15 | ተማሪዎች የጻፉትን ጽሑፍ ወይም ድርሰት በማየትና አስተያየት በመስጠት እንደገና አሻሽለዉ እንዲጽሑፉ ያደርጋሉ | የግል | 6.67 | 10 | 21.67 | 15 |
| | | የመንግ | 8.33 | 13.33 | 16.67 | 11.67 |
| 16 | ሲጽፉ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይተዉ እንዲጽፉ ያደርጋሉ | የግል | 11.67 | 13.33 | 16.67 | 8.33 |
| | | የመንግ | 13.33 | 15 | 20 | 8.33 |
| 17 | ተማሪዎችየጻፉትንድርሰት በድጋሚ በማየት ያበረታታሉወይም ያደንቃሉ | የግል | 1.67 | 3.33 | 31.67 | 13.33 |
| | | የመንግ | 3.33 | 8.33 | 33.33 | 5 |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለዉ ተማሪዎች በቅድመ ጽህፈት ጊዜ በቢጋር ዉስጥ መካተት ያለባቸዉ ጉዳዮች እንዲያሰላስሉ ማድረግን ስናይ ከግል ትምህርት ቤት 35% ከመንግስት ትምህርት ቤት 25% የሚሆኑት ሲስማሙ ከግል 15% ከመንግስት 25% የሚሆኑት አፍራሽ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ተማሪዎች በግል ያመነጩትን ሀሳብ በግል እንዲወያዩና ቢጋር እንዲያዘጋጁ የደርጋሉ የሚለዉን ጥያቄ ስናይ ከግል 35% ከመንግስት 25% የሚሆኑት በሀሳቡ ሲስማሙ ከግል 15% ከመንግስት 25% አለመስማማታቸዉን ገልጸዋል፡፡ ተማሪዎች ያዘጋጁትን ረቂቅ ከሌላዉ ጥንድ ጋር እንዲወያዩበት ያደርጋሉ ለሚለዉ ጥያቄ ከግል 21.67% ከመንግስት 11.66%በሀሳቡ ሲስማሙ ከግል 28.34% ከመንግስት 38.33%የሚሆኑት አፍራሽመልስ ሰጥተዋል፡፡የድርሰት ዓይነቶችን እንዲጠቀሙ ያደርጋሉ ለሚለዉ ጥያቄ ከግል 30% ከመንግስት 23.33% በሀሳቡ ሲስማሙ ከግል 20% ከመንግስት 26.67% በሀሳቡ ሳይስማሙ ቀርተዋል፡፡ጽሑፋቸዉን ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር እንዲያገናዝቡ ያደርጋሉ ለዚህ ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 33.33% ከመንግስት ትምህርት ቤት 33.33% የሚሆኑት ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል 16.67% ከመንግስት 16.66% የሚሆኑት አፍራሽ መልስ ሰጥተዋል፡፡

እንዲሁም የጻፉትን ጽሑፍ አይተዉ አስተያየት በመስጠት አሻሽለዉ እንዲጽፉ ያደርጋሉ ለሚለዉ ከግል 36.67% ከመንግስት 28.34% የሚሆኑት ትክክለኛ መልስ ሲሰጡ ከግል 16.67% ከመንግስት 21.66% የሚሆኑት ደግሞ አፍራሽ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ሲጽፉ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይተዉ እዲጽፉ ያደርጋሉ ለሚለዉ ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 28.34%ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 28.33% ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል 25% ከመንግስት 28% የሚሆኑት ደግሞ በሀሳቡ ሳይስማሙ ቀርተዋል፡፡ተማሪዎች የጻፉትን

ድርሰት በድጋሚ በማየት ማድነቅን ስናይ ከግል 34% ከመንግስት 38.33% እስማማለሁ ብለዉ ሲመልሱ ከግል 5% ከመንግስት 9% የሚሆኑት ደግሞ አለመስማማታቸዉን ገልጸዋል፡፡

**ሠንጠረዥ12፤ የድህረ መጻፍ ጊዜ ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ግምገማ በፐርሰንት**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ |
| 18 | ተማሪዎች የጻፉትን ጽሑፍ መሰረት በማድረግ ሀሳብ እንዲሰጡ (በጻፉት ርዕ ጉዳይ ዙሪያ እንዲወያዩና ዕንዲከራከሩ)ያደርጋሉ | የግል | - | 11.67 | 25 | 11.67 |
| | | የመንግ | 5 | 13.33 | 16.67 | 15 |
| 19 | ተማሪዎች ሲጽፉ ያስቸገራቸዉን ቃላትና ዐረጋት ያስረዳሉ | የግል | 3.33 | 8.33 | 21.67 | 16.67 |
| | | የመንግ | 8.33 | 11.67 | 15 | 15 |
| 20 | የጻፉትን ጽሑፍ ፍሬ ሀሳብ እንዲናገሩ ያደርጋሉ | የግል | - | 10 | 31.67 | 8.33 |
| | | የመንግ | - | 15 | 18.33 | 16.67 |
| 21 | መምህሯ/ሩ ጽህፈትን የተመለከቱ ይዘቶችን ከክፍል ዉጪ ሰርተዉና ተለማምደዉእንዲበጡ ያግዛሉ | የግል | 3.33 | 8.33 | 26.67 | 11.67 |
| | | የመንግ | 6.67 | 11.67 | 16.67 | 15 |
| 22 | ጽሑፉ ካለቀ በኃላ ተማሪዎች ተጠይቀዉ ሲመልሱ ገንቢ የሆነ አስተያየት በመስጠት ተሳትፋዋቸዉን ያብታታሉ | የግል | - | 10 | 16.67 | 23.33 |
| | | የመንግ | - | 8.33 | 25 | 16.67 |
| 23 | ከጽሑፉ በፊትና በኃላ ተማሪዎች ጽሑፉን በግልጽ እንዲረዱ ግልጽመመሪያዎችንይሰጣሉ | የግል | 3.33 | 11.67 | 18.33 | 16.67 |
| | | የመንግ | 5 | 15 | 16.67 | 13.33 |
| 24 | መምህሯ/ሩ ተማሪዎች በጻፉት ጽሑፍ ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን እንዴት ማዉጣት እንዳለባቸዉ ያለማምዳሉ | የግል | 8.33 | 16.67 | 15 | 10 |
| | | የመንግ | 13.33 | 20 | 13.33 | 3.33 |
| 25 | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ጽሑፍ በንግግር ወይም በንባብ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያቀርቡ ዕድል ይሰጣሉ | የግል | 8.33 | 13.33 | 16.67 | 11.67 |
| | | የመንግ | 8.33 | 15 | 15 | 11.67 |

ከሡንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለዉ ተማሪዎች የጻፉትን ጽሑፍ መሰረት በማድረግ ሀሳብ እንዲሰጡ ያደርጋሉ ለሚለዉ ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት 36.67% ከመንግስት ትምህርት ቤት 31.67% የሚሆኑት መስማማታቸዉን ሲገልጹ ከግል 14.67% ከመንግስት 18.33% የሚሆኑት ተማሪዎች አፍራሽ መልስ ሰጥተዋል፡፡ተማሪዎች ሲጽፉ ያስቸገራቸዉን ቃላትና ሀረጋት ያስረዳሉ ለሚለዉ ጥያቄ ከግል 38.34% ከመንግስት 30% የሚሆኑት ተማሪዎች ሲስማሙ ከግል 11.66% ከመነግስት 20% የሚሆኑት ደግሞ አለመስማማታቸዉን ገልጠዋል፡፡ተማሪዎች የጻፉትን ፍሬ ሀሳብ እንዲናገሩ በማድረግ ላይ ከግል 40% ከመንግስት 35% የሚሆኑት ተማሪዎች እስማማለሁ የሚል መልስ ሲሰጡ ከግል 10% ከመንግስት 15% የሚሆኑት ደግሞ ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፧ተማሪዎች ከክፍል ዉጪ ጽሁፈትን እንዲለማመዱ ያደርጋሉ ለሚለዉ ጥያቄ ከግል 38.34% ከመንግስት 31.67% የሚሆኑት ተማሪዎች መስማማታቸዉን ሲገልጹ ከግል 11.66% ከመንግስት 18.34% የሚሆኑ ደግሞ አፍራሽመልስ ሰጥተዋል፡፡ለተማሪዎች ገንቢ አስተያየት መስጠትና ተሳትፎዋቸዉን መበረታታትን በተመለከተ ከግል 40% ከመንግስት 41.67% የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል 10% ከመንግስት 3.33% የሚሆኑት ደግሞ ተቃራኒ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በተጨማሪም ለተማሪዎች ግልጽ መመሪያ መስጠትን በተመለከተ ከግል ትምህርት ቤት 35% ከመነግስት ትምህርት ቤት 30% የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል 15% ከመንግስት 20% የሚሆኑት ደግሞ በሀሳቡ ሳይስማሙ ቀርተዋል፡፡ተማሪዎች በጻፉት ጽሑፍ ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን እንዴት ማዉጣት እንዳለባቸዉ ያለማምዳሉ ለሚለዉ ከግል 25% ከመንግስት 16.67% የሚሆኑት ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ ሲስጡ ከግል 25% ከመንግስት 33.33%የሚሆኑት ደግሞ ሳይስማሙ ቀርተዋል፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች ያዘጋጁትን ጽሑፍ በንግግር ወይም በንባብ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያቀርቡ ዕድል ይሰጣሉ ለሚለዉ ከግል 28.34% ከመንግስት 26.67% የሚሆኑት ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጡ ከግል 21.66% ከመንግስት 21.33% የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ አፍራሽ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይመረጃው እንደሚያመለክተው መምህራኑ የመፃፍ ክሒል ትምህርትን ሒደት ስኬታማ ለማድረግ የሚጠቀሙት አተገባበር ምን እንደሚመሥል በግልፅ ያሣያል:: ከምልከታውና ከተማሪዎች ግምገማ ውጤት መረዳት የሚቻለው የክፍል ውስጥ አላባውያን የሆኑት መሠረት በማድረግ በግል ትምህርት ቤት የሚያሥተምሩ መምህራን መፃፍን ለመማር የሚያሥችሉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር መቻልቸዉን ያሳያል፡፡

## ሠንጠረዥ13፡ በቅድመ መፃፍ ትምህርት አተገባበር የተማሪዎችግምገማ በመቶኛ (በፐርሰንት)

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | አማራጭ መልሶች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አልስማማም | | አልስማማም | | እስማማለሁ | | በጣም እስማማለሁ | |
| | | | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት |
| 1 | የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ያስተዋዉቃሉ? | የግል | | | 3 | 5 | 9 | 15 | 18 | 30 |
| | | የመንግስት | | | 8 | 13.33 | 12 | 20 | 10 | 10.67 |
| 2 | የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ያስተዋዉቃሉ? | የግል | 4 | 6.67 | 2 | 3.33 | 10 | 16.67 | 14 | 23.33 |
| | | የመንግ | 9 | 15 | 10 | 16.67 | 8 | 13.33 | 3 | 5 |
| 3 | ተማሪዎች የመጻፍ ፍላጎት እንዲኖራቸዉ የቀደመ እዉቀታቸዉን በመቀስቀስ ወደ ጽሑፍ እንዲገቡ ያደርጋሉ? | የግል | 26 | 3.33 | 8 | 13.33 | 8 | 13.33 | 12 | 20 |
| | | የመንግስት | 4 | 6.67 | 12 | 20 | 9 | 15 | 5 | 8.33 |
| 4 | ተማሪዎች ለምን እንደምጽፉና እንዴት መጻፍ እንዳለበት ተገቢዉ የሆነ ፍንጭ ይሰጣሉ? | የግል | - | - | 5 | 8.33 | 10 | 16.67 | 15 | 25 |
| | | የመንግስት | 5 | 8.33 | 10 | 16.67 | 8 | 13.33 | 10 | 16.67 |
| 5 | ተማሪዎች ከርዕሱ ተነስተዉ የጽሑፉን ይዘት እንዲተነቢዩ ያደርጋሉ? | የግል | 4 | 6.67 | 8 | 13.33 | 8 | 13.33 | 10 | 16.67 |
| | | የመንግስት | 6 | 10 | 12 | 20 | 8 | 13.33 | 4 | 6.67 |
| 6 | በርዕሳቸዉ ላይ ቢጋር ወይም አስተዋጽኦ እንዲያዘጋጁ ያደርጋሉ? | የግል | - | - | 4 | 6.67 | 10 | 16.67 | 16 | 26.67 |
| | | የመንግስት | - | - | 10 | 16.67 | 9 | 15 | 11 | 18.33 |
| 7 | የጽሑፉ ይዘት ወይም ርዕስ ከተማሪዎች የክፍል ደረጃና የቀደመ እዉቀትጋር አዛምደዉ ያቀርባሉ? | የግል | 2 | 3.33 | 6 | 10 | 10 | 16.67 | 12 | 20 |
| | | የመንግስት | 4 | 6.67 | 7 | 11.67 | 9 | 15 | 10 | 16.67 |
| 8 | ተማሪዎች ለሚጽፉት ጽሑፍ የጊዜ ገደብ ይሰጣሉ? | የግል | 3 | 5 | 5 | 8.33 | 9 | 15 | 13 | 21.67 |
| | | የመንግስት | 4 | 6.67 | 6 | 10 | 10 | 16.67 | 10 | 16.67 |

ከዚህ ሠንጠረዥ መረዳት የሚቻለው የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ፣የመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን የተሻለ ዉጤት ያስመዘገቡ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡

በተማሪዎች የተገኘው ግምገማ ውጤት የሚያሳየው የግል ትምህርት ቤት መምህራን የተሻለ የቅድመ መጻፍ ክሂል ድምር እንደሚተገብሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይህም የሚያሳየው ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ ወደ ፐርሰንት በመቀየር ተሰልቶ ተቀምጧል፡፡ የመቶኛዉ ውጤት የሚያሣየው በግል ትምህርት ቤት የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር የተሻለ መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ በቅድመ መፃፍ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር በምልከታና ከተማሪዎች ግምገማ ውጤት እንደሚያሳየው በሁለቱም የግል ትምህርት ቤት የተሻለ አተገባበር እንዳለ ከመረጃው መረዳት ተችሏል፡፡

ውጤት ተኮር የመፃፍ ክሒል ትምህርት ማተኮር የመፃፍ ክሒል ማሥተማሪያ ሥልቶች ና ለሒደታዊ የመፃፍ ክሒል ትምህርት አተገባበር ማተኮር እና የመፃፍ ሥራዎችን ከፋፍሎ በመሥጠት መቆጣጠርና ማሥተካከል አሥፈላጊ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በግልና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚያሥተምሩ መምህራን የመፃፍ ክሒል ትምህርት አተገባበር ደረጃቸው በጣም ከፍተኛ ባይሆንም መካከላቸው ግን ልዩነት እንዳለና በግል ትምህርት ቤት የሚያሥተምሩመምህራን የተሻለ አተገባበር እንዳላቸው አጠቃላይ የግምገማ ውጤቱ ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ በቅድመ መፃፍ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር በምልከታና ከተማሪዎች ግምገማ ውጤት እንደሚያሳየው በሁለቱም የግል ትምህርት ቤት የተሻለ አተገባበር እንዳለ ከመረጃው መረዳት ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ14፡ በመፃፍ ጊዜ ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ግምገማ በመቶኛ (በፐርሰንት)

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አልስማማም | | አልስማማም | | እስማማለሁ | | በጣም እስማማለሁ | |
| | | | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት |
| 9 | ተማሪዎች በቅድመ ጸሀፊት ጊዜ ከተረዱት ሀሳብ በመነሳት በየግላቸዉ በቢጋር ዉስጥ መካተት ያለባቸዉን ጉዳዮች እንዲያሰላስሉ ያደርጋሉ? | የግል | 3 | 5 | 6 | 10 | 10 | 16.67 | 11 | 18.33 |
| | | የመንግስት | 5 | 8.33 | 10 | 16.67 | 11 | 18.33 | 4 | 6.67 |
| 10 | ተማሪዎች በግል ያመነጩትን ሀሳብ በጥንድ ካወያዩ በኃላ ቢጋር እንዲያዘጋጁ ያደርጋሉ? | የግል | 2 | 3.33 | 7 | 11.67 | 9 | 15 | 12 | 20 |
| | | የመንግስት | 6 | 10 | 9 | 15 | 7 | 11.67 | 8 | 13.33 |
| 11 | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ረቂቅ ከሌላዉ ጥንድ ጋር ተወያይተዉ ሀሳብ ወይም አስተያየት እንዲለዋወጡበት ያደርጋሉ? | የግል | 7 | 11.67 | 10 | 16.67 | 10 | 16.67 | 3 | 5 |
| | | የመንግስት | 11 | 18.33 | 12 | 20 | 5 | 8.33 | 2 | 3.33 |
| 12 | ከሌሎች ጥንድ ተማሪዎች ከተሰጣቸዉ አስተያየት በመነሳት ረቂቁን በድጋሚ እንዲጽፉ ያደርጋሉ? | የግል | 5 | 8.33 | 7 | 11.67 | 10 | 16.67 | 6 | 10 |
| | | የመንግስት | 8 | 13.33 | 8 | 13.33 | 12 | 20 | 2 | 3.33 |
| 13 | እንደየጽሑፉ ዓላማ የተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች እንዲጠቀሙ ያደርጋሉ? | የግል | 5 | 8.33 | 7 | 11.67 | 10 | 16.67 | 8 | 13.33 |
| | | የመንግ | 7 | 11.67 | 9 | 15 | 11 | 18.33 | 3 | 5 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ተማሪዎች የጻፉትን ድርሰት ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር እንዲያገናዝቡ ያደርጋሉ? | የግል | 3 | 5 | 7 | 11.67 | 12 | 20 | 8 | 13.33 |
| | | የመንግ | 5 | 8.33 | 5 | 8.33 | 12 | 20 | 8 | 13.33 |
| 15 | ተማሪዎች የጻፉትን ጽሑፍ ወይም ድርሰት በማየትና አስተያየተ በመስጠት እንደገና አሻሽለዉ እንዲጽፉ ያደርጋሉ? | የግል | 4 | 6.67 | 6 | 10 | 13 | 21.67 | 9 | 15 |
| | | የመንግስት | 5 | 8.33 | 8 | 13.33 | 10 | 16.67 | 7 | 11.67 |
| 16 | ሲጽፉ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይተዉ እንዲጽፉ ያደርጋሉ? | የግል | 7 | 11.67 | 8 | 13.33 | 10 | 16.67 | 5 | 8.33 |
| | | የመንግስት | 8 | 13.33 | 9 | 15 | 12 | 20 | 5 | 8.33 |
| 17 | ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት በድጋሚ በማየት ያበረታታሉ ወይም ያደንቃሉ? | የግል | 1 | 1.67 | 2 | 3.33 | 19 | 31.67 | 8 | 13.33 |
| | | የመንግስት | 2 | 3.33 | 5 | 8.33 | 20 | 33.33 | 3 | 5 |

ከዚህ ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው የመፃፍጊዜ ትምህርት አተገባበር አማካይ ውጤት የግል ትምህርት ቤት ከመንግስት ትምህርት ቤት የተሻለ መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ በመፃፍጊዜ የተሻለ አተገባበር የሚታየው በግል ትምህርት ቤት መሆኑን የተመዘገበው መረጃ ያሳያል። በዚህም መሠረት የግል ትምህርት ቤት የመፃፍጊዜ ትምህረት አተገባበር እንዳላቸው ከውጤቱ መረዳት ይቻላል።

በዚህ መሰረትም በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የተሻለ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር እንዳላቸው መረጃው ያመለክታል።

**ሠንጠረዥ 15፡ የድህረ መፃፍ ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ግምገማ በመቶኛ (በፐርሰንት)**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አልስማማም | | አልስማማም | | እስማማለሁ | | በጣም እስማማለሁ | |
| | | | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት |
| 18 | ተማሪዎች የጻፉትን ጽሑፍ መሰረት በማድረግ ሀሳብ እንዲሰጡ (በጻፉት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ እንዲወያዩና እንዲከራከሩ) ያደርጋሉ? | የግል | - | - | 7 | 11.67 | 15 | 25 | 7 | 11.67 |
| | | የመንግስት | 3 | 5 | 8 | 13.33 | 10 | 16.67 | 9 | 15 |
| 19 | ተማሪዎች ሲጽፉ ያስቸገራቸዉን ቃላትና ዐረጋትያስረዳሉ? | የግል | 2 | 3.33 | 5 | 8.33 | 13 | 21.67 | 10 | 16.67 |
| | | የመንግስት | 5 | 8.33 | 7 | 11.67 | 9 | 15 | 9 | 15 |
| 20 | የተጻፉትን ጽሑፍ ፍሬ ሀሳብ እንዲናገሩ ያደርጋሉ? | የግል | -- | - | 6 | 10 | 19 | 31.67 | 5 | 8.33 |
| | | የመንግስት | - | - | 9 | 15 | 11 | 18.33 | 10 | 16.67 |
| 21 | መምህሯ/ሩ ጽህፈትን የተመለከቱ ይዘቶችን ከክፍል ዉጪ ሰርተዉና ተለማምደዉ እንዲመጡ ያግዛሉ? | የግል | 2 | 3.33 | 5 | 8.33 | 16 | 26.67 | 7 | 11.67 |
| | | የመንግስት | 4 | 6.67 | 7 | 11.67 | 10 | 16.67 | 9 | 15 |
| 22 | ጽሑፉ ካለቀ በኃላ ተማሪዎች ተጤቀዉ ሲመልሱ ገንቢ የሆነ አስተያየት በመስጠት ተሳትፎዋቸዉን ያበረታታሉ? | የግል | - | - | 6 | 10 | 10 | 16.67 | 14 | 23.33 |
| | | የመንግስት | - | - | 5 | 8.33 | 15 | 25 | 10 | 16.67 |
| **23** | ከጽሑፉ በፊትና በኃላ ተማሪዎች ጽሑፉን በግልጽ እንዲረዱ ግልጽ መመሪዎችን ይሰጣሉ? | የግል | 2 | 3.33 | 7 | 11.67 | 11 | 18.33 | 10 | 16.67 |
| | | የመንግ | 3 | 5 | 9 | 15 | 10 | 16.67 | 8 | 13.33 |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ትምህርት ቤት | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፈጽሞ አላስማማም | | አልስማማም | | እስማማለሁ | | በጣም እስማማለሁ | |
| | | | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | በፐርሰንት |
| 24 | መምህሯ/ሩ ተማሪዎች በጻፉት ጽሑፍ ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን እንዴት ማዉጣት እንዳለባቸዉ ያለማምዳሉ? | የግል | 5 | 8.33 | 10 | 16.67 | 9 | 15 | 6 | 10 |
| | | የመንግስት | 8 | 13.33 | 12 | 20 | 8 | 13.33 | 2 | 3.33 |
| 25 | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ጽሑፍ በንግግር ወይም በንባብ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያቀርቡ ዕድል ይሰጣሉ? | የግል | 5 | 8.33 | 8 | 13.33 | 10 | 16.67 | 7 | 11.67 |
| | | የመግስት | 5 | 8.33 | 9 | 15 | 9 | 15 | 7 | 11.67 |

ከሠንጠረዡ መረዳት የሚቻለው በድህረ መፃፍ ትምህርት አተገባበር በግልና በመንግሰት ትምህርት ቤት የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር በተመለከተ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራንበመንግስት ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን የተሻለ እንደሆነ አማካይ ውጤቱ ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረትም በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የተሻለ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር አንዳላቸው ከመረጃውያሳያል፡፡

### 4.1.4. ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

**የመፃፍ ክሒል ትምህርትን የሚያዳብሩ ማለማመጃዎችን በክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ**ለውጤታማ የክፍል ውስጥ የመፃፍ ክሒል ትምህርት መምህራን የተለያየ የመፃፍ ችሎታን የሚያዳብሩ ማለማመጃዎችን በክፍል ውስጥ በማቅረብ ተማሪዎች የጽሑፍ ችሎታ እንዲኖራቸው ማድረግ ይቻላል። በመሆኑም በዚህ የመፃፍ ክሒል ችሎታን የሚያዳብሩ ማለማመጃዎች አተገባበር ሥር የተለያዩ ፅሁፎችን በመስጠት ለምሳሌ ግጥምን ወደ ሥድ ፅሁፍ መቀየር ፡የዕለት ተዕለት ገጠመኝ ፡ደብዳቤ፡ልቦለድ ወዘተ የመሣሠሉትን ማቅረብ ይቻላል።

መረጃው እንደሚያመለክተው መምህራኑ የመፃፍ ክሒል ትምህርትን ሒደት ስኬታማ ለማድረግ የሚጠቀሙት አተገባበር ምን እንደሚመሥል በግልፅ ያሣያል:: ከምልከታውና ከተማሪዎች ግምገማ ውጤት መረዳት የሚቻለው የክፍል ውስጥ አሳባውያን የሆኑት መሠረት በማድረግ በግል ትምህርት ቤት የሚያሥተምሩ መምህራን መፃፍን ለመማር የሚያሥችሉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ውጤት ተኮር የመፃፍ ክሒል ትምህርት ማተኮር የመፃፍ ክሒል ማሥተማሪያ ሥልቶች ና ለሒደታዊ የመፃፍ ክሒል ትምህርት አተገባበር ማተኮር እና የመፃፍ ሥራዎችን ከፋፍሎ በመሥጠት መቆጣጠር ና ማሥተካከል አሥፈላጊ መሆኑን ያመለክታል::

በግልና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚያሥተምሩ መምህራን የመፃፍ ክሒል ትምህርት አተገባበር ደረጃቸው በጣም ከፍተኛ ባይሆንም መካከላቸው ግን ልዩነት እንዳለና በግል ትምህርት ቤት የሚያሥተምሩመምህራን የተሻለ አተገባበር እንዳላቸው አጠቃላይ የግምገማ ውጤቱ ያመለክታል::

### 4.1.5 ለመምህራን የቀረቡ ቃለ መጠይቆችና የተገኙ ምላሾች

በዚህ ንዑስ ክፍል ለተጠኚ መምህራን የቀረቡ አምስት ጥያቄዎችና መልሶቻቸዉ ቀርበዋል፡፡ለተጠኚ መምህራን ለእያንዳንዳቸዉ አምስት አምስት ጥያቄዎች ቀርቦላቸዉ ለአምስቱም ጥያቄዎች የሰጡትን መልሶች እንደሚከተለዉ ተጠቅሰዋል፡፡

**1.የመጻፍ ክሂልን ሲያስተምሩ ምን ምን ተግባራትን ያከናውናሉ?**ተብሎ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ ሲመልሱሁለቱ የግል ትምህርት ቤት መምህራን ምላሽ ሲሰጡ የተለያዩ ጽሑፎችን ከርዕሱ ይዘትጋር የሚዛመደዉን ሰብስበን ለተማሪዎች በሚመች ሁኔታ አቀናጅተን እናቀርባለን፡፡በሰሌዳ ላይ ጽሑፍ እንጽፍና ተማሪዎች እንዲጽፉ እናደርጋለን፡፡ከዚያም ተማሪዎች በግላቸዉ እንዲጽፉ በግላቸዉ የጻፉትን በቡድን እንዲተራረሙና ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያቀረቡ እናደርጋለን፡፡እንዲሁም ጅምር ሀሳብን በመስጠት አስፋፍተዉ እንዲጽፉ እናደርጋለን፡፡ርዕስ በማስመረጥም አስተዋጽኦ አንዲነድፉ፤አንቀጽ እንዲገነቡና አጫጭር ድርሰቶችን እንዲጽፉ እናበረታታለን፡፡ ከዚያም የጻፉትን መላልሰዉ እንዲያነቡና እንዲለማመዱ እናደርጋለን ብለዋል፡፡በተጨማሪም ቃላትን አራርቀዉ እንዲጽፉና ያማረ እጅ ጽሑፍእንዲኖራቸዉ እንመክራለንበማለት መልሰዋል፡፡

ሁለቱየመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ደግሞ የሰጡት ምላሽ በመጀመሪያ ተማሪዎች ከሚሰጧቸው ርዕስ ውስጥ እነሱ የሚስማማቸውን እንዲመርጡ በማድረግ ወይም እነሱ በመረጡት ርዕስ ዙሪያ በቂ ዕውቀትና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ እርስ በርሳቸው እንዲወያዩና እንዲረዳዱ ከርዕሶቻቸው ጋርም ተዛማጅ የሆኑ ጽሑፎችን እንዲያነቡ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው እንዲረዱና ያልገባቸውን እንዲጠይቁ እናደርጋለን፡፡ በተጨማሪም ሞዴል ጽሑፎችን በመስጠት ድርሰት በመጻፍ እንዲለማመዱ እናበረታታለን በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

**ጥያቄ 2፡ የመጻፍ ክሂልን ሲያስተምሩ በአዎንታ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?**በሚል ለቀረበላቸዉ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን እንዳሉት ተማሪዎች ሀሳባቸዉን በተወሰኑ ቃላትና በተሰጣቸዉ ጊዜ ጽፈዉ ማጠናቀቃቸዉና ለመጻፍና ለመሞከር ፍላጎት ያላቸዉ መሆኑንበአዎንታዊ መልኩ ሲገልጹ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚስተምሩ መምህራን ደግሞ በሳምንት ያለን የክፍለ ጊዜ ጥበት ድርሰት እንዲጽፉና እንዲለማመዱ ጊዜ የለንም በማለት ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎችየድርሰት መጻፊያ ደብተር ያላቸው መሆኑ፣ የተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ መሆኑ፣ ሳምንታዊ የክፍለ ጊዜ ብዛት ሁለት መሆኑ፣ ሁልጊዜም እየተከታተልን ደብተራቸውን በማየትና አስተያት በመስጠት የጻፉትን ጽሑፍ እርስ በርሳቸው እንዲተራረሙ በማድረግና እንደገና አሻሽለው እንዲጽፉ ለማድረግ እንሞክራለን በማለት የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህራን አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ደግሞ ሳምንታዊ የክፍለ ጊዜ ብዛት አንድ ብቻ ቢሆንም ቤታቸዉ ገብተዉ ድርሰት እንዲጽፉና እንዲለማመዱ ወደ ክፍልም ሲመጡ የጻፉትን እንዲያነቡ ለማድረግ እንሞክራለን በማለት አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ጥያቄ 3፡ ተማሪዎች የሚጽፉትን ቅንጫቢ ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር እንዲገናዝቡ በማድረግ ላይ ያሉት አስተሳሰብ ምን ይመስላል?** ተብሎ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ ሲመልሱ አራቱም መምህራን ተማሪዎች የሚጽፉትን ሀሳብ ወይም ርዕስ ማወቃቸዉና ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር ማጣመር ተጨባጭነት እንዲኖረዉና ተነሳሽነት እንዲኖራቸዉ ያደርጋል ብለዋል፡፡ተማሪዎች የሚያዉቁትን ነገር መጻፍ የበለጠ ግልጽ ይሆንላቸዋል ፡፡ስለዚህ ተማሪዎች የሚጽፉትን ነገር ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር ቢያገናዝቡ የተሻለ ግንዛቤን ይጨብጣሉ ፤ የእዉቀት አድማሳቸዉም ይሰፋል በማለት ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡

**ጥያቄ 4፡ የመጻፍ ክሂልን ሲያስተምሩ በአሉታ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?**ተብሎ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ እንደ መምህራኑ ገለጻ በአብዛኛዉ ተማሪዎቹ ሁለተኛ ቋንቋቸዉ ከመሆኑ አንጻር በሚፈለገዉ ልክ የመጻፍ ፍላጎት የላቸዉም፡፡ ሲጽፉም ደግሞ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋቸዉ የመሳብ ሁኔታ ይታይባቸዋል ብለዋል፡፡

ሌላዉበግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህራን የሰጡት ምላሽ አንዳንድ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ሥራ በቸልተኝነት የማለፍ ሁኔታ ይታይባቸዋል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ያለው የተሰጣቸውን ተግባራት በጥሩ ሁኔታ ያከናውናሉ፡፡ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህራን የሰጡት ምላሽ በክፍል ውስጥ የተማሪ ቁጥር መብዛት፣ ተማሪዎች የራሳቸው የሆነ የድርሰት መጻፊያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ፣ ተማሪዎች ለትምህርት ዓይነቱ ያላቸው ዝቅተኛ ግምት ወዘተ በነዚህ ምክንያቶች በመንግስት ትምህርት ቤት ያለው የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል ብለዋል፡፡

**ጥያቄ 5፡ስለ መጻፍ ክሂል ትምህርት አጠቃላይ ሀሳብ ወይም አስተያየት ካለዎት?**በሚል ለቀረበላቸዉ ጥያቄ መምህራኑ ሲመልሱ  ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህረትን ከአምስተኛ ክፍል እንደመጀመራቸዉ መጠን ችሎታዉን በፍጥነት በማዳበር ላይ ችግር አለባቸዉ፡፡ምክንቱም የአማርኛ ቋንቋ ለአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸዉ ነዉ፡፡ስለዚህ እነዚህን ተማሪዎች ለመርዳት በመጀመሪያ የመጻፍ ክህልን ስናስተምር ተማሪዎችን በየችሎታቸዉ ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነዉ፡፡በመቀጠልም ተለይተዉ የታወቁ ተማሪዎች እንደየደረጃቸዉ ጽሑፎችንበማዘጋጀት ደጋግመዉ እንዲለማመዱና ኪህሉን እንዲያዳብሩ መርዳት ወይም ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡በተጨማሪም ከክፍል ዉጪ የተለያዩ ርዕሶችን ወስደዉ ሰርተዉና ተለማምደዉ እንዲመጡ በማድረግና እርስ በርሳቸዉ እንዲተራረሙ በማድረግ ችሎታቸዉን አንዲያዳብሩ መርዳት ይቻላል ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የግል ትምህርት ቤት የሚያሥተምሩ መምህራን የተሻለ የመፃፍ ክሒል ትምህርት አተገባበር መኖሩን ሲሆን፡ ይህም እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች መካከል መምህራኑ የጠቀሱት ማስረጃ በየቀኑ ራሱን የቻለ የመፃፍ ክሒል ትምህርት ክፍለ ጊዜ ሥላላቸው መፃፍ አለመፃፋቸውን ደግሞ ወላጆችም ቁጥጥር ሥለሚያደርጉ የተለያዩ ፅሁፎችን በመፃፍ ይለማመዳሉ፡፡ በየክፍለ ጊዜው የሁሉንም ደብተር እርማትና አሥተያየት በመሥጠት እንደሚሠሩ ከመምህራኑ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡በተቃራኒው ደግሞ የመንግስት ትምህርት ቤት የሚያሥተምሩት መምህራን የሰጡት ምላሽ ተማሪዎች ለትምህርቱ የሚሰጡት ዝቅተኛ አመለካከት ሥለሆነ ተገደው ፃፉ ተብለው ሲታዘዙም ከሚፅፉት የማይፅፉት ይበልጣሉ፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ የፃፉተማሪዎችን ደብተር አርመንማክበብ እንጂ አስተያየትም ሆነ የርስ በርስ እርማት አንሰጥም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የክፍለ ጊዜ ማነስ፣የተማሪ ቁጥር መብዛት፤የአማርኛ ቋንቋ ለተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸዉ ስለሆነ ለትምህርቴ ፍላጎት ማጣት ወዘተ አስተያየት ከመስጠት ያግዳል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

## 4.2 የዉጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር በግልና በመንግሰት ትምህርት ቤት ምን እንደሚመስል መፈተሸ ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ መምህራን የመፃፍ ክሂልን ትምህርት አተገባበር ምን አንደሚመስል በክፍል ውስጥ የመፃፍ ክሂልን የሚያስተምሩበት የትምህርት አቀራረብ መፈተሽ መምህራን የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚከተሏቸው

መርሆዎችን መፈተሽና በመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ወቅት የትኞቹ የተሻሉእንደሆኑ በማነፃፀር ማየት ነው፡፡ ዓላማዎቹን ለመፈተሽም መረጃዎቹበምልከታ፣ በፅሁፍ ፣መጠይቅ እና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡የተሰበሰቡበት መረጃዎች በአይነታዊና መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ተተንትነዋል፡፡ የተገኙት ውጤቶችም ተጠቅሰዋል፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል ደግሞ በ4.1 ሥር በተናጠል የተፈተሹት መረጃዎች በጋራ የተገኙት ውጤቶች ከእያንዳንዱ ዝርዝር ዓላማ አንፃር ምን ገፅታ እንዳላቸው ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

1. የመምህራን የክፍል ዉስጥ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ምን ይመስላል?ዓላማውን ለመፈተሽ መረጃው በአይነታዊና መጠናዊ የመንተንተኛ ስልት ተተንትኗል፡፡ የተገኘው ውጤት እንዳሳየውም መምህራን ከስህተት የፀዳ ፅሁፍ እንደዲፅፉ ተማሪዎችን የሚያበረታቷቸው መሆኑንና ሞዴል ፁሑፎችንም በመስጠት የመፃፍ ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያደርጉ መሆኑን ነው፡፡

 እንዲሁም የተለያዩ የመፃፊያ መለማመጃ ተግባራትን በመስጠት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆነው መፃፍን እንደዲለማመዱ አመቺ ሁኔታዎችን ለተማሪዎች የሚፈጥሩላቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ውጤት መረዳት የሚቻለው መምህራን መፃፍ ለማስተማር የሚጠቀሙበት አቀራረብ ውጤታዊ አቀራረብ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች መፃፍን ለመጀመር ርዕስ መምረጥ ፣ሃሳብ በማመንጨት፣ እቅድ በማዘጋጀት፣ በማርቀቅና በመከለስ ሳይሆን የተሰጣቸውን የፅሁፍ ሞዴል በመገለባበጥና የአፃፃፍ ቅርፁንም በማየት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

 ከዚህ ወጤት የምንረዳው መምህራን የሚጠቀሙበት የማስተማሪያ ዘዴ ዉጤታዊ የመፃፍ ክሂልን የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ዘዴ ተማሪዎቹ ድርሰት ሲፅፉ የነበረው ከራሳቸው ሀሳብ አፍልቀው የዓረፍተ ነገርንም ሆነ የአንቀፅ አፃፃፍ ስርዓትን ጠብቀው በራሳቸው የሚፅፉ ሳይሆን የተሰጣቸውን ሞዴል ፅሁፍ ወይም ድርሰት በመገልበጥና የአፃፃፍ ቅርጹን በማጤን መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተማሪዎች ድርሰቶች ምሳሌ ይሆናሉ ወይም ጥሩ ይፅፋሉ ተብለው የሚታሰቡ ፅሁፎችን በሞዴልነት አቅርቦ ሰዋሰዋዊ ህጎችንና አፃፃፋቸውን በማሳየት ተማሪዎች እነዚያኑ አስመስለው እንድፅፉ የሚያለማምዱ መሆኑን Nunan (1989፣36) እና Richards (1990፣106) አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች መምህሩን በሚያቀርቡላቸው ሞዴል ፅሁፍ መሰረት ልምምድ ያደርጋሉ፡፡ መምህሩም ሞዴሉን መሰረት እያደረገ የሞዴሉን አገልግሎትና አፃፃፍ ስልቶችን

በመግለፅ ተማሪዎች የቀረበውን ሞዴል አንብበው ባህሪያትን በመገምገም መጠነኛ በሆነ ልዩነት ተመሳሳይ ድርሰት እንድፅፉ ያበረታታል፡፡ በዚህ ደረጃ የሚካሄዱ ዉይይቶች ድርሰትን ለመፃፍ የሚያገለግሉ መር ፅህፈት ተግባራት መሆናቸውንም Raims (1983፣1030 እና Pincas (1982፣102) ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ውጤት ተኮር አቀራረብ በቋንቋው ቅርፅ ላይ ስለሚያታኩር እንዲሁም የመፃፍ ልምምዱ ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል በቅድሚያ በመምህሩ የሚወሰን በመሆኑ ከተማሪዎች ለሚቀርብ አዲስ ሃሳብ ትኩረት የማይሰጥ የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ዘዴው ተማሪዎች በሚፅፉት ርዕስ ላይ በራሳቸው ቋንቋና አገላለፅ ተጠቅመው ድርሰት የመፃፍ ልምምድ እንዲደርጉ አያበረታታቸውም ፡፡

እንዲሁምመምህራን ከክፍል ውጪ የሚሰሩ የመጻፍ ተግባራትን ብዙም የማይሰጡ መሆኑንና በክፍል ውስጥ ለሚሰጡ ተግባራትም ቢሆን በቂ ጊዜ በመመደብ ተማሪዎች መፃፍን እንዲለማመዱ የማያደርጉ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጣል፡፡ ይህም Raimes(1983) መፃፍ በስሜት የሚከናወንና በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቅ ስራ አለመሆኑን፣ በአንፃሩ ጊዜ የሚፈጅ ፣ከፍተኛ ጥረትን የሚጠይቅ፣ ሃሳብን መቀበል፣መጠየቅና መመርመር እንዲሁም በትኩረት ማሰብም የሚያሻው የአፅምሮና የአካል ስራ መሆኑን ከተሰጡት ብያኔዎች መገንዘብ ከሚለው ሃሳብ ጋር ተቃርኗል፡፡ በተጨማሪም መምህራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰሩ የመፃፍ ተግባራት ተማሪዎች በግልና በጥንድ እርማት እንዲያደርጉ የማያበረታቱ መሆኑን፣ እንዲሁም የተማሪዎችን ፅሁፍ ለማረም አሰቸጋሪ ተግባር አድርገው የሚቆጥሩ መሆኑን ውጤቱ ያሳያል፡፡

2. መምህራን በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የመፃፍ ክሂልን ትምህርት በንፅፅር ሲያስተምሩ የሚከተሏቸው መርሆዎች ምን ምን ናቸው?

መርሆዎችን በተመለከተ ከምልከታው ሆነ ከቃለ መጠይቁ የተገኙት መረጃዎች የሚያመለክቱት መምህራን መፃፍን ሲያስተምሩ የተወሰኑ መርሆዎችን የሚተገብሩ መሆኑን ነው፡፡ በተለይም ተማሪዎች መጻፍ ከመጀመራቸው በፊት የመፃፍ አላማን እንዲያውቁና ተነሳሽነት እንዲኖራቸው መምህራን ጥረት የሚያደርጉ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህንንም ለማሳካት በክፍል ውስጥ የሚሰጡ መለማመጃዎች የሚያነሳሱና በጥንድም ሆነበቡድን ለተማሪዎች ውይይት ለማድረግ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥሩላቸው

ጥናቱ ያሳያል፡፡ይህም ሃሳብ ፀሐፊም መፃፍን መለማመድ አለበት(Graham2012) ከሚለው ሀሳብ ጋር
ተቃራኒ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል የትኞቹ የተሸለ የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር እንዳላቸው መፈተሽ እንደሆነ በምዕራፍ አንድ ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ለአንድ የመማር ማስተማር ሂደት ስኬታማ መሆን ከመምህሩ የትምህርት ዓይነት በተጨማሪ ወሳኝና ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን በርካታ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል kiros (2006፡2) እንደሚሉት፣ ተማሪዎች በጽህፈት አማካኝነት ሃሳባቸውን በተገቢ መንገድ ለመግለጽ የሚያስችላቸውን ዕውቀትና ችሎታ እንዲያዳብሩ ለማድረግ የመምህሩ የትምህርት አተገባበር ወሳኝነት አለው፡፡ በተመሳሳይ በድሉ (1996፣52) እንደሚሉት፣ የክፍል ውስጥ የጽህፈት ትምህርት መምህራን መማር የሚቻልበትን ሁኔታ ከማመቻቸት በተጨማሪ የትምህርት አቀራረባቸው በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ በሌላ በኩል በክፍል ውስጥ ከመማር ማስተማር ሂደቱ ጋር በተያያዘ በርካታ ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች ተቋቁሞ የመማር ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ ለማድረግ መምህራን ያላቸውን የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ተመሳሳይነት አይታይበትም፡፡ የዚህ ምክንያት ደግሞ መምህራን የሚከተሏቸው የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበሮች መምህራን ለተማሪዎቻቸው ካላቸው የአመለካከት ልዩነት፣ የተማሪ ቁጥር መብዛትና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ በእነዚህ ችግሮች የተነሳ የመምህራን የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር የተሻሉት በግል ወይስ በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው? የሚለውን በንጽጽር በመፈተሽ የልዩነቱን ምክንያቶች ለመጠቆም ጥናት ተካሂዷል፡፡የመጻፍ ክሂል ትምህርት ምንነት፣ ጠቃሚነት፣ ዓላማ፣ አተገባበርና የመሳሰሉት፣ እንዲሁም ከዚህ ቀደም በተለያዩ ምሁራን የተጠኑ ሀገርኛ ጥናቶችን በሚመለከት በመስኩ ምሁራን ያረጋገጧቸውን ንድፈ ሃሳባዊ ጉዳዮች በምዕራፍ ሁለት ቀርበዋል፡፡

ለጥናቱ የተሟላ መረጃ ያስገኛሉ የተባሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የክፍል ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠይቅ እና ቃለመጠይቅ) የአተናተን ስልታቸው የተገለጸው በምዕራፍ ሦስት ነበር፡፡

በእነዚህ መሳሪያዎች የተገኙት መረጃዎችም በምዕራፍ አራት ተተንትነው በጥናቱ ዓላማ ለተነሱት ጉዳዮች ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች በ2013 ዓ.ም በመቱ ከተማ በሚገኙ የግልና የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ የተጠኝ መምህራን ትምህርት ቤቶች የተመረጡት በዕጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ሲሆን፣ ከግል ትምህርት ቤት፣ፈተንሳ ኢሉና ፈለገ ጥበብ ከመንግስት ትምህርት ቤት ቢሻሪና ቱሉቤ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡ ከተመረጡት ትምህርት ቤቶች ከእያንዳንዱ በተመሳሳይ መልኩ ሁለት ሁለት በድምሩ አራት (4) መምህራን የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት የበለጠ አስተማማኝ ለማድረግ ሲባልም ተጨማሪ ስድሳ (60) ተማሪዎች በመረጃ ምንጭነት ተመርጠዋል፡፡

የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ሆነው ያገለገሉ የክፍል ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ መሆናቸውን ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ አካል በሆነው በገላጭ ዘዴ ተብራርተዋል፡፡በተጨማሪም በመጠናዊ የምርምር ዘዴ ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡

ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ወደ መቶኛ እየተለወጡ ተገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል የመምህራን የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበርን ለመፈተሽ ከተዘጋጁት የክፍል ምልከታ ቅፆች እና ከተማሪዎች ግምገማ የተገኙት መረጃዎች አማካይ ውጤታቸው ተሰልቶ ተመዝግበዋል፡፡ የመምህራን የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥምበመቶኛ የተሰላዉን አማካዩን በማዉጣትና ደረጃ በመስጠት ተቀምጧል፡፡ በመምህራን የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ሂደት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በርካታ ተለውጦዎች እንዳሉ ቀደም ሲል ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሠረት በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በቀረበላቸው ቃለመጠይቅ እንደገለጹት የተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን የመማር ፍላጎታቸው ዝቅ ያለ ነው፡፡ ከክፍል ምልከታና ከተማሪዎች ግምገማ የተገኘው መረጃም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ በመሆኑ በመጻፍ ክሂል ትምህርት ችሎታቸዉም ዝቅ ያለ ነው፡፡ የዚህ ምክንያቶች፡-

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸዉ ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን በመጻፍ ክሂል ትምህርት ላይም ዝቅተኛ ዉጤት እንዲኖራቸዉ አድርጓል፡፡ለዚህ እንደምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉ ነጥቦች አሉ፡፡እነሱም፡-መምህራን የመጻፍ ትምህርት ክሂል መለማመጃ ተግባራት አለመስጠት፣መምህራን በመጻፍ ክሂል ትምህርት ወቅት ከሂደታዊ አተገባሮች ይልቅ ለውጤት ተኮር አተገባበር ትኩረት መስጠት፣ተማሪዎች በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚሰሯቸው የመጻፍ ሥራዎች አስተያየት አለመስጠት፣መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመጻፍ ተነሳሽነት ለመቀስቀስ ስለመጻፍ ትምህርት ጠቀሜታ ገለጻ አለመስጠት፣መምህራን የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ደረጃ ፈትሸው ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት ሁኔታ አለማመቻቸት፣የሚሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎቻቸው አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት የተሻለ በመሆኑ በክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ላይ ተፅዕኖዉም ውስን እደሆነና የተማሪዎችን ፍላጎት ከመጠበቅ ረገድም የተሻሉ እንደሆኑ የተገኘው የመረጃ ውጤት ያመለክታል፡፡

ሌላው በመምህራን የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድረው የተማሪች ቁጥር መብዛት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በግልና በመንስት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራን የተገኘው ምላሽና ከክፍል ምልከታዉ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው በአንድ ክፍል ውስጥ ብዛት ያላቸውን ተማሪዎች የመጻፍ ስራዎች ማለማመድ አስቸጋሪ እንደሆነ ነው፡፡ መምህራን የመጻፍ ስራዎችን የሚሰጡት በግል የሚሰሩ ሳይሆኑ በቡድን የሚሰሩ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያትም መምህራን የእያንዳንዱን ተማሪ የመጻፍ ችሎታ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ይቸገራሉ የሚል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በክፍል ምልከታው ጊዜ በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በአንድ ክፍል ውስጥ የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ከሠላሳ (30) የማይበልጡ በመሆናቸው በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራን የተሻለ የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የክፍል ምልከታውና የተማሪዎች ግምገማ፣ ውጤቶች እንዳረጋገጡት የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ረገድ በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር ሲነጻጸሩ የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት በሚያቀርቡበት ጊዜ ስራዎችን በግል፣ በጥንድ በቡድንና በህብረት በማደራጀት ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥረት ሲያደርጉ ታይተዋል፡፡

በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ደግሞ በግል ትምህርት ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን በበለጠ በውጤት ተኮር የመጻፍ ትምህርት ላይ ሲያተኩሩ ታይተዋል፡፡

የክፍል ምልከታው፣ የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቆች እና የመምህራን ቃለመጠይቅ እደሚጠቁሙት፣ በክፍል የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ደረጃ በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራን ይልቅ በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የተሻለ ደረጃ እንዳላቸው ጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የተሻለ የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር እንዲኖራቸው ያስቻሏቸው ምክንያቶች፡-

- የተሻለ የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባር ሂደቶችን መከተላቸው፣
- ተማሪዎች የመጻፍ ክሂላቸዉን እንዲያዳብሩ የተለያዩ ነገሮችን እንዲጽፉና እንዲለማመዱ ማድረጋቸዉ ለምሳሌ፡-ደብዳቤ እንዲጽፉ፤ግጥምን እንዲጽፉና የጻፉትን ግጥም ደግሞ ወደ ስድ ጽሑፍ እንዲቀይሩ ማድረጋቸዉ፤
- የተለያዩ በግልና በቡድን የሚሰሩ ሥራዎችን በመስጠትና ለሰሯቸዉ ሥራዎች ደግሞ ተገቢዉን አስተያየትና ማጠናከሪያ መስጠታቸዉ፤
- የመጻፍ ክሂል ትምህርት መለማመጃ ተግባራትን ለተማሪዎች ሲያቀርቡ በአብዛኛዉ የተማሪዎች ችሎታና ፍላጎትን ያገናዘቡ መሆናቸዉ፤
- የተማሪዎችን ለመጻፍ ያላቸዉን ተነሳሽነት መቀስቀሳቸዉ፤
- የተማሪዎች ብዛት ከመንግስት ትምህርት ቤቶች ካሉት ተማሪዎች በቁጥር የተሻለ ወይም ያነሰ ሆኖ መገኘቱ፤
- ስከታማ የሆኑ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ማሰተማሪያ ስልቶችን መጠቀማቸዉና የመሳሰሉት ምክንያቶች መሆናቸዉን የጥናቱ ዉጤት ይጠቁማል፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች የመፃፍ ተግባራትን በክፍል ሊያስገባቸው የሚገባቸውን መስፈርቶች በተለይም የቃላት አጠቃቀም፣ የሰዋሰው ህግጋትና የፅሁፍ ሃሳብ ፍሰትን መጠበቅ ያለባቸው መሆኑን መምህራን ከሚከተሉት መርሆዎች ሌላው ነው፡፡በመሆኑም መምህራን የመፃፍ መርሆዎችን ተከትለው ትምህርቱን አላቀረቡም፣ እንዲሁም መፃፍን ከክፍል ውጪ ለማለማመድ የሚረዱ አመቺ ሁኔታዎች አለመፍጠራቸው የጥናቱ ውጤት

አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም Graham(2012) ለተማሪዎች የመፃፍ ምቹ ሁኔታ ማመቻቸትን አስፈላጊነት ሲገልፁ «ምንጊዜም መፃፍ የሚዳብረው በቀን በቀን ልምምድ ነው፡፡ አንድ ሰው በጣም ጥሩ የቅርጫት ኳስ ተጫዋች መሆን ከፈለገ ስለቅርጫት ኳስ ማንበብና መወያየት ብቻ ሳይሆን ኳስን ወደ ቅርጫቱ አነጣጥሮ መወርወር አለበት፡፡ ስለዚህ አንድ የቅርጫት ኳስ ተጫዋች አጨዋወቱን መለማመድ እንዳለበት ሁሉ ፀሀፊም መፃፍን መልመድ አለበት» ከሚለው ሀሳብ ጋር ተቃርኗል፡፡

በአጠቃላይ ከውጤት ትንተናው መገንዘብ እንደሚቻለው በጥናቱ ውስጥ የተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂልን በማስተማር የተጠቀሙበት የማስተማር ስልትና በክፍል ውስጥ ያከናወኗቸው ተግባራት አንድ የመፃፍ ክሂል መምህር ሊያደርጋቸው የሚገባ ክንዋኔዎችን የሚያሟሉ ሆነው አልተገኙም፡፡ በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ያደርጉ ምሁራን የመፃፍ ክሂል መምህራን ማሟላት አለበት ብለው ከሰጡት ነጥብ መካከል ተጠኝ መምህራኑ ያላሟሏቸው በርካታ በመሆናቸው በመፃፍ ሂደት ውስጥ ሊወጧቸው የሚገባቸውን ሚናዎች ያለ መገንዘብ ችግር እንዳለ መገመት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓላማ በመቱ ከተማ በሚገኙ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ዉስጥ 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽህፈት ክህል ትምህርት አተገባበር በንጽጽር መፈተሽና የትኞቹ የተሻለ የክፍል ዉስጥ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር እንዳላቸዉ ንጽጽራዊ ጥናት ማድረግ ነዉ፡፡በዚህም መሰረት በጥናቱ መልስ እንዲገኝባቸዉ የተነሱት ጥያቄዎች ጠሚከተሉት ናቸዉ፡፡

1.የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንየመፃፍ ክሂል አተገባበር ምን ይመስላል

2.የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል አተገባበር ምን ይመስላል

3.የየትኞቹ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበርን በተሻለ ሁኔታ ይተገብራሉ

የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄ መመለስ ይቻል ዘንድ ምልከታ፤የፅሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ በመሆን አገልግለዋል፡፡አጥኚዋ በመቱ ከተማ ከሚገኙ ስድስት የመንግስትና ሶስት የግል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ሁለት የግልና ሁለት የመንግስት ትምህርት ቤቶችን በዕጣ የንሞና ዘዴ ከመረጠች በኋላ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች በ2013 ዓ.ም የ8ኛክፍልን በማስተማር ላይ ከሚገኙት ስድስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ሶስት የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል ከመንግስት ትምህርት ቤት ሁለት ከግል ትምህርት ቤት ሁለት በድምሩ አራት መምህራንን በጠቅላይ የናሙና ዘዴ ማርጣ የጥናቱ ተሳታፊ አድርጋቸዋለች፡፡ የጥናቱን ዉጤት የበለጠ አስተማማኝ ለማድርግ ሲባልም ተጨማሪ ስልሳ (60) ተማሪዎች በሚጃ ምንጭነት ተማርጠዋል፡፡

የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሆነዉ ያገለገሉ የክፍል ምልከታ፤ የፅሁፍ መጠይቅና ቃለ መተይቅ መሆናቸዉን ከላይ ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡በመሆኑም በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ

መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች በአይነታዊ የምርምር ዘዴ አካል በሆነዉ በገላጭ ዘዴ ተብራርተወል፡፡በተጨማሪም በመጠናዊ የምርምር ዘዴ ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

ከተማሪዎች የፅየተገኙ መረጃዎች ወደ መቶኛ እየተለወጡ ተገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል የመምህራን የክፍል ዉስጥ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበርን ለመፈተሽ ከተዘጋጁት የክፍል ምልከታ ቅፆችና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ዉጤታቸዉ ተሰልቶ ተመዝግቧል፡፡የመምህራን የክፍል ዉስጥ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር ልዩነት መኖሩን ሁፍ መጠይቅ ለማረጋገጥም አጥኚዋ በመቶኛ የተሰላዉን ደረጃ በመስጠት አስቀምጣለች፡፡

በአጠቃላይ የክፍል ምልከታዉ፤የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ና የመምህራን ቃለ መጠይቅ እንደሚጠቁሙት የመፃፍ ክሂል ትምህርት አተገባበር በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ መምህራን ይልቅ በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የተሻለ አተገባበር እንዳላቸዉ ጥናቱ አመላክቷል፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

የጥናቱን ዉጤትናጥ ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በድህረ መፃፍ አተገባበር የተገኘዉ ዉጤት ጉልህ ልዩነት ባይኖርም በቅድመ መፃፍ እና በመፃፍ ጊዜ አተገባበር ግን ጉልህ ልዩነት አለ፡፡ ይህም  የመንግስት ትምህርት ቤት የአማርኛ የቋንቋ መምህራን የድህረ መፃፍ ትምህርት አተገባበራቸዉ የተሻለ ቢሆንም የቅድመ መፃፍ እና የመፃፍ ጊዜን ግን እንደማይተገብሩት ለመረዳት ተችሏል፡፡

የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ  መምህራን የቅድመ መፃፍ፤የመፃፍ ጊዜና የድህረ መፃፍ አተገባበራቸዉ መካከል ጉልህ ልዩነት የለም፡፡ ይህም የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቅድመ መፃፍ፤የመፃፍ ጊዜና የድህረ መፃፍ ተግባራትን በተሻለ ሁኔታ እንደ ሚተገብሩት የጥናቱ ዉጤት ያሳያል፡፡

ሌላዉ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ተጠኚ መምህራን በቅድመ መፃፍ፤ በመፃፍ ጊዜና በድህረ መፃፍ አተገባበራቸዉ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን

መረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም በቅድመ መፃፍ ፤በመፃፍ ጊዜና በድህረ መፃፍ አተገባበራቸዉ የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከመንግስት ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ መምህራን የተሻሉ እንደሆኑ ለማውቅ ተችሏል፡፡

## 5.3. አስተያየት

የጥናቱን ውጤት መሠረት በማድረግ አጥኚዋ የሚከተሉትን አስተያቶች በመፍትሄነት አቅርባለች፡፡ እነዚህም፡-

በጥናቱ ለማየት እንደ ተሞከረዉ የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚ መምህራን የቅድመ እና የመፃፍ ጊዜ ተግባራትን በአግባቡ ሲተገብሩት አልተስተዋለም፡፡ መምህራን የቅድመና የፅህፈት ጊዜ ተግባራትን እንደ ድህረ መፃፍ ተግባራት ቢተገብሩትና ለተማሪዎቻቸዉ ቢያሰሯቸዉ የተሻለ ይሆናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የግልም ሆነ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተጠኚ መምህራን የድህረ መፃፍ ተግባራትን የበለጠ ለመከወን ተጨማሪ ጥያቄዎች፤ዉይይት፤ክወና፤ስዕል፤ሙዚቃና ሌሎች ንግግሮችን ማዘጋጀት፤አዲስ ሀሳብ እንዲፅፉ ማድረግ ፤ቅንጫቢን እንደገና መናገር ቢችሉና እንደ ፅሁፉ ርዕስና ዓላማ ለተማሪዎቹ የተለያዩ የፅሁፍ አይነቶችን (ስልቶችን ) እንዲጠቀሙ ቢያደርጉ፡፡

በአጠቃላይ በምልከታዉ፤በፅሁፍ መጠይቁና ከቃለ መጠይቁ እንደተገለፀዉ በሁሉም የመፃፍ ክህል ትምህርት አተገባበር ላይ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን የተሻሉ ሆነዉ ተገኝተዋል፡ ፡በመሆኑም የፅህፈት ትምህርት በምን አይነት መልኩ መተግበር እንዳለበት ለማወቅና የተሻለዉን ለመከተል በግልና በመንግስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል የልምድ ልዉዉጥና ዉይይት ቢካሄድና ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ቢተኮርባቸዉ የመፃፍ ትምህርቱ በተሻለ መልኩ ሊተገበር ይችላል፡፡

በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አተገባበር ጥናት ባልተደረገባቸዉ ክሂሎችና የዕዉቀት ዘርፎች ጥናት ቢደረግ

# ዋቢ ጽሑፎች


ማረው አለሙ። (1998)። <u>የአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ዘዴ</u>።አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ሰለሞን ዮሀንስ። (1991)። "የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጂና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ"

ሰይድይመር።(1993)።"በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን የጽህፈት

ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ ዘዴትግበራ።"አዲስ አበባ፣አበባዩኒቨርሲቲየሂዩማኒቲስየቋንቋዎችጥናት፣የጆርናሊዝምናየኮሚኒኬሽንኮሌጅ፣የአማርኛቋንቋ፣ሥነጽሑናፎክሎርትምህርትክፍልድህረምረቃመረሐ-ግብር፣ (ያልታተመ)።

ሰዩም ከበደ። (1988 )።"ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ለ9ኛ ክፍል ማስተማር ያለዉ ተግባራዊነት"

በድሉ ዋቅጅራ። (2007)። <u>በስነጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር</u>፡፡(ሁለተኛ ዕትም)፣አዲስ አበባ፣ ንግድማተሚያ ድርጅት።

ኢሳያስ ይልማ።(2002)።"የጽሑፍ ክሂልን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የትምህርት

አደረጃጀታቸው10+2የሆኑተማሪዎችበአማርኛደብዳቤለመፃፍያላቸውብቃትበጎባናሮቤመሰናዶትምህርት ቤትናሙናነት"።አዲስአበባ፣በአዲስ አበባዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎ ጥናት፣ የጆርናሊዝምእና ኮምንኬሽን ኮሌጅ የአማርኛቋንቋ ና ስነ ጽሁፍፎክለር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር (ያልታተመ )

ያለዉ እንዳወቅ። (2001)።<u>የምርምርመሠረታዊ መርሆዎችናአተገባበር</u>። (ሁለተኛእትም)፣አዲስአበባ፣ንግድማተሚያድርጅት።

ጌታቸውቸርነት፡፡(2001)፡፡“በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ሴት ና ወንድተማሪዎችየጽህ ፈትክሂልችሎታንጽጽራዊ ጥናት”፡፡ አዲስአበባ፣በአዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲ፣የቋንቋ ዎች ጥናት፣የጆርናሊዝም ና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍ ና ፎክሎር ት ምህርትክፍልድህረ-ምረቃ መረሐ-ግብር፣(ያልታተመ)፡፡

*Anker, W. (2000). ‘’<u>Erron and corrective feedback</u>: updated theory and classroom practice”. Forum 38/4.21-21*

*Best, W. and James, K. (1993). Research in education (17th ed) NewDelhi prentice hall of Indian p.ltd.*

Braddock,lioyd Jones,R,schoers,l.(1963).Research in writing composition ,urbana il:national councils of teachers of English.

*Byren, D. (1988). Teaching writing skills. Singapore: language group Ltd.*

Byren,D.(1983).Teaching writing skills.london: long man group ltd.

*Bayren. (1991). Teaching wrting skills. London: Long man group Ltd.*

*Chomsky, N. (1957). Syntactic structures The Hague: Mouton*

*Chomsky, N. (1965). Aspects of the theory of syntax Cambridge MA MLT press*

*David, E. (2005). Doing reading in the real world London SAGE publications.*

*Fallick, F and Brown, B. (1983). Statistic for behavioral science: Homewood lll ionois: The Dorsey press.*

Flower,l,and Hayes,J.R.(1981).college composition and communication. College composition and communication.vol.32,365-387.

Harmer,J.(1991).The practice of English language teaching .london :long man teachers of English.

Heaton ,J .B(1990). English Language Test. (3rd Edition), London: Longman Group, UK limited.

*Hedge, T. (1991). Writing. Oxford: Oxford University Press.*

*Hillocks, T. (1986). Research on writing composition: New direction for teaching. Urbana Ill: NCRE/ER/C.*

*Hyland, K and Hyland, F. (2006). Feed back on 2nd language students' writing language teaching.*

*Kumar, R. (2005). Research methodology (2nd ed). California SAGE publications.*

*Larson, F.D. (1986). Techniques and principles in language teaching.Oxford: Oxford University Press.*

Lingren,H.c.(1983).An introduction to social psychologies:Newyork: John willey and sons INC.

Makino,T.y.(1993).learners self correction in EFL written compositions.

Mc Domough,Jand show,c.(1993).materials and methods in ELt:Ateachersguide .oxford:Black well.

*Nunan, D. (1989). ''A client centered approach to teacher development ELT journal'' 43/2*

*Nunan, D. (1989). Designing tasks for the communicative classroom. Cambridge: university press.*

*Nunan, D (1989). Designing tasks for the communicative classroom. Cambrodge:Cambridge university press.*

*Norrish ,J. (1990).Language Learners and their Errors. London : Macmillan Publishers Ltd.*

*Phil, M. (2013) teaching writing: Analysis of the writing tasks, east west University in Bangladish.*

*Pincas, A. (1982). Teaching English writing. London: macmillan publishers*

*Richards, J. C. (1990). The language teaching matrix. Cambridge: university press.*

*Richards, J.C. (1990). The language teaching matrix.Cambridge university press.*

*Raimas, A. (1983). Teqniques in the teaching writing. Oxford: university press.*

*Robert,k.(2003).Case study Research,design and methods (3rd.ed).sage publication.*

*Sommerr and Barbaras (1980). A practical Guide to Behavioral research tools and techniques, New York: Oxford University Press.*

*Ur, P. (1996). A course in language teaching. Cambridge: Cambridge university press.*

*Byner, D. (1991). Teaching writing skills. London: longman group ltd.teachers of English.*

Widdowson,H,G.(1978).Teaching languages communication.Oxford: oxford university press.

Zamel, V.(1985).”Responding to student Writing” TESOL Quarterly. 191, (PP.79-101).

# አባሪዎች

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## የክፍል ዉስጥ የምልከታ ቅፅ

"የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት ትምህርት አተገባበር ንፅፅራዊጥናት(በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት)" በሚል ርዕስ ለሚካሄደዉ ጥናት መምህራን በክፍል ዉስጥ ትምህርቱን ሲያከናዉኑ ለመከታተያነት የተዘጋጀ የምልከታ መከታተያ ቅፅ።

**ክፍል አንድ**

**አጠቃላይ መረጃ**

1. የትምህርት ቤቱ ስም ______________________________
2. የመምህሯ/ሩ መለያ ኮድ ______________________________
3. የትምህርት ደረጃ ______________________________
4. ምልከታዉ የተካሄደበት ክፍል ______________________________
5. የትምህርቱ ርዕስ ______________________________
6. የምልከታ ጊዜ ______________________________
7. የአንዱ ክፍለጊዜርዝማኔ ______________________________
8. መምህሯ/ሩ ዕለታዊ/ሳምንታዊ እቅድ ነበራቸዉ __________ አልነበራቸዉም _______
9. የተማሪ ብዛት ወንድ ___________ ሴት ___________ ድምር __________
10. የአገልግሎት ዘመን ______________________________
11. ፆታ ______________________________
12. ቀን ______________________________

## ክፍል ሁለት

ከዚህ በላይ እያንዳንዳቸዉ አምስት አማራጮች ያሏቸዉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳነዱ ጥያቄ የሚሰጠዉ አንድ ምላሽ ብቻ ነዉ፡፡ ጥያቄዎቹን በማንበብ መልስ ነዉ የምትለዉን/ይዉን መመዘኛ መርጠሽ/ህ በተሰጠዉ ሳጥን ዉስጥ የ “X” ምልክት በመጠቀም መልስ/ሺ፡፡

የመገምገሚያ ነጥቦች 1 = በጣም ዝቅተኛ 2 = ዝቅተኛ 3 = መካከለኛ 4 = ከፍተኛ 5 = በጣም ከፍተኛ

| ተ.ቁ | መምህሩ/ሯ በክፍል ዉስጥ ፅህፈትን በሚያስተምሩበት ወቅት የሚያከናዉኗቸዉ ተግባራት | የዉጤት ድግግሞሽ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | **II. የቅድመ መፃፍ ትምህርት ተግባር** | | | | | |
| 1 | የእለቱን ትምህርት ርዕስ ማስተዋወቅ | | | | | |
| 2 | የእለቱን ትምህርት አላማ ማስተዋወቅ | | | | | |
| 3 | ተማሪዎች የመፃፍ ፍላጎት እንዲኖራቸዉ የቀደመ እዉቀታቸዉን በመቀስቀስና በማነሳሳት ወደ ፅሁፍ እነዲገቡ ማድረግ | | | | | |
| 4 | ተማሪዎች ለምን እነደሚጽፉና እንዴት መፃፍ እንዳለበት ተገቢ የሆነ ፍንጭ መስጠት | | | | | |
| 5 | ተማሪዎች ከርዕሱ ተነስተዉ የፅሁፉን ይዘት እነዲተነቢዩ ማድረግ | | | | | |
| 6 | በርዕሳቸዉ ላይ ቢጋር/አስተዋፅኦ እነዲያዘጋጁ ማድረግ | | | | | |
| 7 | የፅሁፉ ይዘት/ርዕስ ከተማሪዎች የክፍል ደረጃና የቀደመ እዉቀት ጋር አዛምዶ ማቅረብ | | | | | |
| 8 | ተማሪዎች ለሚፅፉት ፅሁፍ የጊዜ ገደብ መስጠት | | | | | |
| | **II የፅሁፍ ጊዜ ትምህርት ተግባራት** | | | | | |
| 9 | ተማሪዎች በቅድመ ፅህፈት ጊዜ ከተረዱት ሃሳብ በመነሳት በየግላቸዉ በቢጋር ዉስጥ መካተት ያለባቸዉን ጉዳዮች እንዲያሰላስሉ ማድረግ | | | | | |
| 10 | ተማሪዎች በግል ያመነጩትን ሃሳብ በጥንድ ካወያዩ በኋላ ቢጋር | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | እንዲያዘጋጁ ማድረግ | | | | | |
| 11 | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ረቂቅ ከሌላዉ ጥንድ ጋር ተወያይተዉ ሀሳብ ወይም አስተያየት እንዲለዋወጡበት ማድረግ | | | | | |
| 12 | ከሌሎች ጥንድ ተማሪዎች ከተሰጣቸዉ አስተያየት በመነሳት ረቂቁን በድጋሚ እንዲፅፉ ማድረግ | | | | | |
| 13 | እንደየ ፅሁፉዓላማ የተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች እንዲጠቀሙ ማድረግ | | | | | |
| 14 | ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር እንዲያገናዝቡ ማድረግ | | | | | |
| 15 | ተማሪዎች የፃፉትን ፅሁፍ/ድርሰት በማየትና አስተያየት በመስጠት እንደገና አሻሽለዉ እንዲፅፉ ማድረግ | | | | | |
| 16 | ሲፅፉ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይተዉ እንዲፅፉ ማድረግ | | | | | |
| 17 | ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት በድጋሚ በማየት ማበረታታትና ማድነቅ | | | | | |
| | **III የድህረ ፅህፈት ትምህርት ተግባራት** | | | | | |
| 18 | ተማሪዎች የፃፉትን ፅሁፍ መሰረት በማድረግ ሀሳብ እንዲሰጡ (በፃፉት ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ እንዲወያዩና እንዲከራከሩ) ማድረግ | | | | | |
| 19 | ተማሪዎች ሲፅፉ ያስቸገራቸዉን ቃላትና ሀረጋት ማስረዳት | | | | | |
| 20 | የፃፉትን ፅሁፍ ፍሬ ሀሳብ እነዲናገሩ ማድረግ | | | | | |
| 21 | መምህሯ/ሩ ፅህፈትን የተመለከቱ ይዘቶችን ከክፍል ዉጪ ሰርተዉና ተለማምደዉ እነዲመጡ ማገዝ | | | | | |
| 22 | ፅሁፉ ካለቀ በኂላ ተማሪዎች ተጠይቀዉ ሲመልሱ ገንቢ የሆነ አስተያየት መስጠትና ተሳትፎዋቸዉን ማበረታታት | | | | | |
| 23 | ከፅሁፉ በፊትና በኂላ ተማሪዎች ፅሁፉን በግልፅ እነዲረዱ ግልፅ መመሪያዎችን መስጠት | | | | | |
| 24 | መምህሯ/ሩ ተማሪዎች በፃፉት ፅሁፍ ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን እንዴት ማዉጣት እንዳለባቸዉ ማለማመድ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 25 | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ፅሁፍ በንግግር ወይም በንባብ ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እንዲያቀርቡ ዕድል መስጠት | | | | | |

የእለቱ ግምገማ ዘገባ ማጠቃሊያ_____________________________________________

_______________________________________________________________

ቅፁን የሞላዉ/ችዉ ባለሙያ ስም ______________________________________

ፍርማ __________________ ቀን ___________________

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

8ኛ ክፍል የሚያሥተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቃለመጠይቅ

1. የመፃፍ ክሂልን ሲያስተምሩ ምን ምን ተግባራትን ያከናዉናሉ?
2. የመፃፍ ክሂልን ሲያስተምሩ አዎንታዊ ተፅዕኖ የሚያመጡ ጉዳዮች ምንድናቸዉ?
3. ተማሪዎች የሚፅፉትን ቅንጫቢ ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር እንዲያገናዝቡ በማድረግ ላይ ያሎት አስተሳሰብ?
4. የመፃፍ ክሂልን ሲያስተምሩ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ይኖራሉ?
5. ስለመፃፍ ክሂል ትምህርት አጠቃላይ ሀሳብ ወይም አስተያየት ካሎት!

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ

ይህ የፅሁፍ መጠይቅ የተዘጋጀዉ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል ቋንቋ መምህራን የክፍል ዉስጥ የመፃፍ ትምህርት አተገባበራቸዉን ለማነፃፀር ሲባል የተዘጋጀ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነዉ፡ ስለዚህ ከእናንተ የሚገኘዉ መረጃ ለዚህ ጥናት መሳካት ትልቅ አስተዋፅኦ ስላለዉ መጠይቁን በጥንቃቄ አንብባቸሁ ተገቢዉን መልስ በመመለስ ቀና ትብብራችሁን እንዲታደረጉልኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡በተጨማሪም ዉድ የሆነዉን የትምህርት ጊዜያችሁንመስዋዕት በማድረግ ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር ሁሉ በቅድሚያ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለዉ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም

መጠይቁን ከጓደኛ ጋርተመካከሮ መሙላት ወይም ከሌላ ሰዉ ኮርጆ መሙላት የተከለከለ ነዉ፡፡

**ክፍል ሁለት**

**አጠቃላይ መረጃ**

***መመሪያ*** 1፡ ከዚህ በታች ላሉት የፅሁፍ መጠይቆች ትክክለኛዉን መረጃ ፃፍ/ፊ!

ያታ _____ ወንድ _____ ሴት _____

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ____________________ ሁለተኛ ቋንቋ______________________

የምትማርበት/የምትማሪበት ትምህርት ቤት ስም____________________

***መመሪያ 2፡*** ከዚህ በታች 5 መመዘኛ ያሏቸዉ ጥያቄዎች ቀርበዋል ለእያንዳነዱ ጥያቄ የምሰጠዉ ምላሽ 1 ጊዜ ብቻ ነዉ፡፡ ጥያቄዎቹን በማንበብ ትክክለኛ መልስ ነዉ የምትለዉን/የምቲይዉን መመዘኛ መርጠህ/ሽ በተሰጠዉ ሰንጠረዥ ዉስጥ የ "X" ምልክት በመጠቀም መልስ/ሺ

የመመዘኛ መግለጫ 1 = ፍፅሞ አልስማማም 2 = አልስማማም 3 = መወሰን ያስቸግራል 4 እስማማለሁ 5 = በጣም እስማማለሁ

| ተ.ቁ | የመገምገሚያ ነጥቦች | ዉጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | **የቅድመ መፃፍ ትምህርት ተግባራት** | | | | | |
| 1. | የእለቱን ትምህርት ርዕስ ያስተዋዉቃሉ? | | | | | |
| 2. | የእለቱን ትምህርት አላማ ያስተዋዉቃሉ? | | | | | |
| 3. | ተማሪዎች የመፃፍ ፍላጎት እንዲኖራቸዉ የቀደመ እዉቀታቸዉን በመቀስቀስና በማነሳሳት ወደ ፅሁፍ እነዲገቡ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 4. | ተማሪዎች ለምን እነደሚጽፉና እንዴት መፃፍ እንዳለበት ተገቢ የሆነ ፍንጭ ይሰጣሉ? | | | | | |
| 5. | ተማሪዎች ከርዕሱ ተነስተዉ የፅሁፉን ይዘት እነዲተነቢዩ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 6. | በርዕሳቸዉ ላይ ቢጋር/አስተዋጽዖ እነዲያዘጋጁ ያደርጋሉ | | | | | |
| 7. | የፅሁፉ ይዘት/ርዕስ ከተማሪዎች የክፍል ደረጃና የቀደመ እዉቀት ጋር አዛምደዉ ያቀርባሉ? | | | | | |
| 8. | ተማሪዎች ለሚፅፉትፅሁፍ የጊዜ ገደብ ይሰጣሉ? | | | | | |
| | **የፅሁፍ ጊዜ ትምህርት ተግባራት** | | | | | |
| 9. | ተማሪዎች በቅድመ ፅህፈት ጊዜ ከተረዱት ሃሳብ በመነሳት በየግላቸዉ በቢጋር ዉስጥ መካተት ያለባቸዉን ጉዳዮች እንዲያሰላስሉ ያደርጋሉ? | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10. | ተማሪዎች በግል ያመነጩትን ሃሳብ በጥንድ ካወያዩ በኂላ ቢጋር እንዲያዘጋጁ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 11. | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ረቂቅ ከሌላዉ ጥንድ ጋር ተወያይተዉ ሀሳብ ወይም አስተያየት እንዲለዋወጡበት ያደርጋሉ? | | | | | |
| 12. | ከሌሎች ጥንድ ተማሪዎች ከተሰጣቸዉ አስተያየት በመነሳት ረቂቁንበድጋሚ እንዲፅፉ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 13. | እንደየ ፅሁፉ ግላማ የተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች እንዲጠቀሙ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 14. | ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት ከሕይወት ልምዳቸዉ ጋር እንዲያገናዝቡ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 15. | ተማሪዎች የፃፉትን ፅሁፍ/ድርሰት በማየትና አስተያየት በመስጠት እንደገና አሻሽለዉ እንዲፅፉ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 16. | ሲፅፉ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይተዉ እንዲፅፉ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 17. | ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰት በድጋሚ በማየት ያበረታታሉ/ያደንቃሉ? | | | | | |
| | **የድህረ ፅህፈት ትምህርት ተግባራት** | | | | | |
| 18. | ተማሪዎች የፃፉትን ፅሁፍ መሰረት በማድረግ ሀሳብ እንዲሰጡ (በፃፉት ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ እንዲወያዩና እንዲከራከሩ) ያደርጋሉ? | | | | | |
| 19. | ተማሪዎች ሲፅፉ ያስቸገራቸዉን ቃላትና ሀረጋት ያስረዳሉ? | | | | | |
| 20. | የፃፉትን ፅሁፍ ፍሬ ሀሳብ እነዲናገሩ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 21. | መምህሯ/ሩ ፅህፈትን የተመለከቱ ይዘቶችን ከክፍል ዉጪ ሰርተዉና ተለማምደዉ እነዲመጡ ያግዛሉ? | | | | | |
| 22. | ፅሁፉ ካለቀ በኂላ ተማሪዎች ተጠይቀዉ ሲመልሱ ገንቢ የሆነ አስተያየት በመስጠት ተሳትፎዋቸዉን ያበረታታሉ? | | | | | |
| 23. | ከፅሁፉ በፊትና በኂላ ተማሪዎች ፅሁፉን በግልፅ እነዲረዱ ግልፅ መመሪያዎችን ይሰጣሉ? | | | | | |
| 24. | መምህሯ/ሩ ተማሪዎች በፃፉት ፅሁፍ ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን እንዴት ማዉጣት እንዳለባቸዉ ያለማምዳሉ? | | | | | |
| 25. | ተማሪዎች ያዘጋጁትን ፅሁፍ በንግግር ወይም በንባብ ለክፍል | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ጓደኞቻቸዉ እንዲያቀርቡ ዕድል ይሰጣሉ? | | | | | |

ይህንን መጠይቅ በመሙላት ስለተባበርከኝ ስለተባበርሽኝ አመሰግናለሁ!

አጥኚዋ